አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራዊ ጥናት

በ

እሸቴ መብራት

መጋቢት 2003 ዓ.ም

# የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማነልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራዊ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

ለተግባራዊ ሥነ ልሳን አማርኛን ለማስተማር
ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

እሸቴ መብራት

መጋቢት 2003 ዓ.ም

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ
## የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
## የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን ማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራዊ ጥናት

በ

እሸቴ መብራት

CLEARED FROM

...ተና ቦርድ አባላት፡-

| ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| | | 22/07/03 |
| አማካሪ | | |
| | | 22/07/03 |
| ፈታኝ | | |

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# ምስጋና

ለዚህ ጥናት መሳካት ውድ ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው በየጊዜው ሳይሰለቹ ስህተቶችን በማረም፣ የአሰራር ስልቶችን በመጠቆምና በማበረታታት ክትትላቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ዶክተር ጌታሁን አማረ ምስጋናዬ እጅግ የላቀ ነው፡፡

ተግባራዊ ጥናቱን ለማከናወን ለአንድ ወር ትርፍ ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው ትምህርቱን በመከታተል፣ ላቀረብኩላቸው ፈተናና ቃለ መጠይቅ ተገቢ ነው ያሉትን ምላሽ በመስጠት ለተባበሩኝ ለወረታ መሰናዶና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ "H" እና የ10ኛ "E" ክፍል ተማሪዎች በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ለጥናቱ የሚያስፈልገውን ወጭ በመሸፈን ለተባበረኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ትብብራቸው ላልተለየኝ ለወረታ መሰናዶና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተዳደር፣ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን በመስጠትና የስታትስቲክስ መረጃዎችን ትንታኔ ገምግሞ አስተያየት በመስጠት ድጋፍ ላደረገልኝ ለአቶ ስለሽ ደምሴ፤ ፈተናዎችንና መማሪያውን ገምግመው አስተያየታቸውን በመስጠት ለተባበሩኝ የትምህርቱ ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል መምህራን፣ ፈተናው ሲሰጥ በመፈተንና የፈተና ወረቀቶችን በማረም ለተባበሩኝ መምህራን ከፍተኛ የሆነ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በመስጠትና ረቂቁን በማረም ድጋፍ ላደረገልኝ ለአቶ ማረው ዓለሙ፣ የስታትስቲክስ ስሌቶችን በመስራት ለተባበረኝ ለአቶ ታደሰ አወቀ፣ እንዲሁም ለአቶ ስጦታው ብርሐኑና ለወይዘሮ የትናየት አየለ፤ የህትመት ስራውን ላገዙኝ አቶ አዳነ አንዳርጌ፣ በተለያየ መልኩ ድጋፋቸው ላልተለየኝ ለአቶ ታደሰ ምህረቴና ለወይዘሮ ሂሩት ደምሴ፣ ለጥናቱ ስኬታማነት ቤተሰባዊ ድጋፋቸው ላልተለየኝ ቤተሰቦቸ ለወይዘሮ አስካል ደምሴ፣ ዕዮን፣ ናሆምና ይቤላ ከልብ የመነጨ ምስጋናየ ይድረስልኝ፡፡

በአጠቃላይ ሩጫየን የጀመርኩት ከረፈደ ቢሆንም ለዚህ ስኬት እንድበቃ ቅዱስ ፈቃዱ ስሆነልኝ ልዑል እግዚአብሔር፣ ከእናቱና ከቅዱሳኖቹ ጋር ክብርና ምስጋና ይገባዋል!!! አሜን፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ---------- i

አህጽሮተ ጥናት ---------- v

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ---------- 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ---------- 1

1.2 የጥናቱ ዓላማ ---------- 3

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ---------- 4

1.4 የጥናቱ ወሰን ---------- 5

1.5 የቁልፍ ፅንሰ ሀሳቦች አጠቃቀም ብያኔ ---------- 5

ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳን ---------- 7

2.1 የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ጥምረትና መደጋገፍ ---------- 7

2.2 ማንበብና መፃፍን በውህደት የማቅረብ አስፈላጊነት ---------- 10

2.3 ማንበብና መፃፍን በጥምረት የማስተማሪያ ዘዴዎች ---------- 13

ምዕራፍ ሦስት፡- የአጠናን ዘዴ ---------- 20

3.1 ተጠኚዎች ---------- 20

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ---------- 21

3.2.1 ፈተና ---------- 22

3.2.1.1 ቅድመ ትምህርት ፈተና ---------- 22

3.2.1.2 ድህረ ትምህርት ፈተና ---------- 23

3.2.2 ቃለ መጠይቅ ---------- 25

3.2.3 የትምህርት ዕቅድ ---------- 26

3.2.4 የመማሪያ/ማስተማሪያ አዘገጃጀት፣ የትምህርቱ አሰጣጥና የትግበራው ሂደት ---------- 27

3.2.5 በክፍል ውስጥ ክንውን የተደረገ የቪዲዮ ምልከታ ---------- 31

3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ ---------- 31

ምዕራፍ አራት፡- የመረጃዎች ትንተናና የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ----------------34

4.1 የመረጃዎች ትንተናና የጥናቱ ውጤት ----------------34

4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ----------------41

ምዕራፍ አምስት፡- የጥናቱ ግኝት ማጠቃለያና አስተያየት ----------------47

5.1 የጥናቱ ግኝት ማጠቃለያ ----------------47

5.2 አስተያየት ----------------50

ዋቢዎች ----------------51

# አባሪዎች

አባሪ አንድ፡- ቅድመ ትምህርት ፈተና ----------------------------------------54

አባሪ ሁለት፡- ድህረ ትምህርት ፈተና -----------------------------------------61

አባሪ ሦስት፡- ቅድመ ትምህርት ቃለ መጠይቅ ------------------------------66

አባሪ አራት፡- ድህረ ትምህርት ቃለ መጠይቅ --------------------------------67

አባሪ አምስት፡- ከቅድመ ትምህርት ቃለ መጠይቅ የተወሰደ ናሙና ----68

አባሪ ስድስት፡- ከድህረ ትምህርት ቃለ መጠይቅ የተወሰደ ናሙና ------71

አባሪ ሰባት፡- ለሙከራ ቡድኑ ማስተማሪያነት የተዘጋጀ ዕቅድ ------------74

አባሪ ስምንት፡- ለጥብቅ ቡድኑ ማስተማሪያነት የተዘጋጀ ዕቅድ -----------85

አባሪ ዘጠኝ፡- ለሙከራ ቡድኑ ማስተማሪያነት የተዘጋጀ መማሪያ-----------86

አባሪ አስር፡- የሙከራ ቡድኑ የክፍል ውስጥ ክንውን የምልከታ ናሙና-104

አባሪ አሥራ አንድ፡- የሙከራ ቡድኑ ቅድመ ትምህርት የፈተና ውጤት መግለጫ ----------------------------------------------106

አባሪ አሥራ ሁለት፡- የሙከራ ቡድኑ ድህረ ትምህርት የፈተና ውጤት መግለጫ ----------------------------------------------106

አባሪ አሥራ ሦስት፡- የጥብቅ ቡድኑ ቅድመ ትምህርት የፈተና ውጤት መግለጫ---------------------------------------------- 108

አባሪ አሥራ አራት፡- የጥብቅ ቡድኑ ድህረ ትምህርት የፈተና ውጤት መግለጫ----------------------------------------------108

አባሪ አሥራ አምስት፡- ጥናቱን ለማካሄድ ከጥናቱ ተሳታፊዎች ጋር የተካሄደ ስምምነት መፈራረሚያ ፎርም ------- 110

አባሪ አሥራ ስድስት፡- የፎቶግራፍ መረጃዎች -------------------------- 112

# አህጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራዊ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በወረታ አጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2003 ዓ.ም ከሚማሩት 2800 የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል 104 ተማሪዎችን ያሳተፈ ነው፡፡ በዕጣ ናሙና 10ኛ "H" በሙከራ 10ኛ "E" በጥብቅ ቡድንነት ተመድበዋል፡፡ ለጥናቱ መረጃ የተሰበሰበባቸው መሣሪያዎች ፈተና፣ ምልከታና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ ሁለቱም ቡድኖች የማንበብና የመፃፍ ችሎታቸውን የሚለካ ቅድመ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል፡፡ ከሙከራ ቡድኑ መካከል ለ6 ተማሪዎች ቅድመና ድህረ ቃለ መጠይቅ ተደርጓል፡፡ ጥብቅ ቡድኑ ከሌሎች የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ጋር በተለመደው የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ በአጥኚው እዲማር ተደርጓል፡፡ የሙከራ ቡድኑም የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት ለማስተማር በተዘጋጀው መማሪያ በአጥኚው በሳምንት ሁለት ቀን ለአንድ ወር ተምሯል፡፡ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የየዕለቱ የትምህርት ክንውን ሂደትና ተራክቦ በቪዲዮ እየተቀረጸ ተመዝግቧል፡፡ ከትምህርቱ በኋላ ለቡድኖቹ ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷል፡፡ በቡድኖቹ መካከል ያለውን ልዩነት ለማረጋገጥ የፈተናው ውጤት በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶና ተነፃፅሮ ተተንትኗል፡፡ በመረጃ ትንተናው መሠረት በሙከራና በጥብቅ ቡድኖቹ መካከል (25.88) የአማካይ ውጤት ልዩነት እንዳለ የስታትስቲክስ ስሌቱ አመላክቷል፡፡ ይህ ውጤት አስተማማኝ መሆኑ ከተማሪዎቹ የተገኘው የቃለ መጠይቅ ምላሽና የክንውን ምልከታው ተመሳሳይነት አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ካላቸው ትስስርና ዝምድና አንፃር በተናጠል ከማቅረብ ይልቅ በውህደት ቢቀርቡ ለክሂሎቹ መጎልበት የላቀ ሚና እንዳለው ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ስለዚህ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ትኩረት ሊሰጡበት ይገባል፡፡ እንዲሁም የሥርዓተ ትምህርቱንና የመማሪያ/ማስተማሪያ መጻሀፍት ሲያዘጋጁና የክፍል ውስጥ ልምምዱም ሲተገበር ሁለቱን ክሂሎች በውህደት ለማስተማር በሚያስችል መልኩ ቢሆን ለቋንቋው ትምህርት እድገት ጉልህ ድርሻ እንዳለው አጥኚው ይጠቁማል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰንና የቁልፍ ዕንሰ ሀሳቦ አጠቃቀም ብያኔዎች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ውስብስብ የሆነውን የማስተማር ሥራ ቀላል ለማድረግ ከ2000 ዓመት በላይ እድሜ ካስቆጠረው ከሰዋስው ወትርጉም የማስተማር ዘዴ ጀምሮ በርካታ ሙከራና ለውጦች ተካሂደዋል፡፡ በመሆኑም Squire (1984) ባደረገው ጥናታዊ አስሳ ቋንቋን ለማስተማር ሲታሰብ በዋናነት የሚነሳው ጉዳይ "ምንና እንዴት እናስተምር?" የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ይህም የይዘት መረጣና የማስተማሪያ ስልት መወሰንን ይመለከታል፡፡ በተለይም ከይዘት መረጣ በኋላ የማስተማሪያ ዘዴውን መወሰን በጣም ወሳኙና ትኩረት የሚሻው ጉዳይ ነው፡፡ ተማሪዎች በእያንዳንዱ የቋንቋ ክሂል ላይ ብቃት አግኝተው የሚገለገሉበትን ቋንቋ እንዲያሳለብቱ ለማድረግ በጥንቃቄ የታቀደ የቋንቋ ትምህርት ያስፈልጋል፡፡ ይህም የቋንቋ ክሂሎችን አደራጅቶ በአግባቡ ማስተማር የሚያስችል የአቀራረብ ስልት መርጦ ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል፡፡

ሞገስ (1999) ባደረገው ጥናት Beerdgew (2003)ን ዋቢ በመጥቀስ እንደገለጸው "በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ዓመታት ማንበብና መፃፍ በሙያ ተኮር (subject centered) ሥርዓተ ትምህርት አቀራረብ እንደ ተለያዩ አሳባውያን ተደርገው ይወሰዱ ነበር፡፡ በማንበብና በመፃፍ ትስስር ላይ ጥናትና ምርምር ማካሄድ የተለመደ አልነበረም፡፡" በተጨማሪም "በ1970ዎቹና 1980ዎቹ ዓመታት ላይ ግን በሁለቱ ክሂሎች መካከል ያለውን ዝምድና ለማጥናት ጥረት ተደርጓል፡፡ ምርምሮቹ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎች በውህደት ከቀረቡና በልምምድ ከተተገበሩ ለክሂሎቹ መጎልበት ጥሩ ሊሆን እንደሚችል ይገልፃል፡፡" ሞገስ (1999)፡፡

በማንበብ ወይም በመፃፍ ተግባር በተገቢው መንገድ በቋንቋ የመገልገል ችሎታ ካለ በሌላኛው ተግባርም በብቃት መጠቀም ይቻላል Gary (1995)። በመሆኑም ማንበብና መፃፍ እርስ በእርሳቸው ተሳስረውና ተደጋግፈው ሊከወኑ እንደሚችሉ ይታሰባል። አንደኛው ተግባር መፃፍ ካለ ሌላኛው ተግባር ማንበብ ሊኖር ይችላል። ሁለቱም በአንድ አይነት ተግባር የሚከናወኑ መሆናቸው በአንዴና በተመሳሳይ ጊዜ ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ።

በሌሎች አገሮች በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች በማንበብና በመፃፍ ክሂሎች መካከል ጥብቅ ትስስር መኖሩንና በውህደት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ያስረዳሉ (እነ Harp 1996)። በመሆኑም ሁለቱን ክሂሎች ከትስስራቸው አንፃር በውህደት ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ ጉልህ ሚና ሊኖረው ይችላል በባል ምክንያታዊ ሊሆን እንደሚችልም ያስገነዝባሉ።

ነገር ግን በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክሂሎቹ አቀራረብ ከዚህ የተለየ ይመስላል። ለዚህም ከመርሀ ትምህርቱ አወቃቀር ጀምሮ እስከ ክፍል ውስጥ ትግበራው ድረስ ክሂሎቹን በማስተማር ረገድ ተግባራዊ እየተደረገ ያለውን ፈትሾ ለማወቅ ጥናት ይጠይቃል። አሁን እየተሰራበት ባለው የ10ኛ ክፍል መርሀ ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፍ ላይ በተደረገው አሰሳና ክትትል ክሂሎችን በተናጠል ለማስተማር በሚያስችል መልኩ የተዘጋጁና እየተሰራባቸውም እንዳለ ይገመታል።

አታክልቲ መኮንን (1998) ለሁለተኛ ድግሪ መመረቂያ ጽሁፉ ባደረገው ጥናት የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛ የማስተማሩን ሥነ ዘዴ አተገባበር ፍተሻ አድርጓል። በመሆኑም የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች አቀራረብ በመማሪያ መጽሐፉ አዘገጃጀትና በክፍል ውስጥ አተገባበሩ በተናጠል እንደሆነ ገልጿል። እንዲሁም አበበች (2002) እና ሞገስ (1999) ባደረጉት ጥናት በሀገራችን ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን የማንበብና መፃፍ ክሂሎች በውህደት የሚቀርቡበት አግባብ ትኩረት ያገኘ አይመስልም። ከዚህ ሌላ አጥኚው ለ24 ዓመት የአማርኛ ቋንቋን ሲያስተምር ክሂሎቹን ታስበባትና ታቅዶ በውህደት የሚቀርቡበት ሁኔታ እንዳልነበር ተገንዝቧል።

ከዚህ በመነሳት የችግሩን መንስኤ ለመረዳት የሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን የ9ኛና የ10ኛ ክፍሎችን የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት የክሂሎቹን አቀራረብ ለመፈተሽ

ሞክሯል። በዚህም መሠረት አጥኚው በመጽሐፎቹ ላይ ባደረገው አጠቃላይ ቅኝት በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ (1997) ውስጥ ከቀረቡት 75 መልመጃዎች መካከል፤ 17 ማንበብን፣ 17 መፃፍን፣ 11 መናገርን፣ 11 ሥነ ጽሑፍን፣ 7 ማዳመጥንና 12 ሰዋስውን፣ በ10ኛ ክፍል ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ (1997) ውስጥ ከቀረቡት 82 መልመጃዎች መካከልም፣ 20 ማንበብን፣ 15 መፃፍን፣ 16 መናገርን፣ 12 ሥነ ጽሑፍን፣ 7 ማዳመጥና 12 ሰዋስውን የሚያለማምዱ ሆነው ተገኝተዋል።

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት መረጃዎች ሲታዩ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት ለማስተማር የተዘጋጁ አይመስልም። በሌላ በኩል በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች ባቀረቡት ጽንሰ ሃሳብ ክሂሎቹን አዋህዶ በማስተማር ተግባቦትን ማሳደግ ይቻላል ተብሎ እንደሚታመን ይገልፃሉ። ስለዚህ በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የክሂሎቹን ትስስርና መደጋገፍ መሠረት አድርጎ በተናጠል ወይስ በውህደት ማስተማር የሚለውን መለየት ያስፈልጋል። ከዚህ በመነሳት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ ጥናት የሚጠይቅ በመሆኑ የዚህ ጥናት መነሻ ሆኗል።

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራዊ ጥናት ነው። በመሆኑም የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት የማቅረብ ትምህርት ላይ ያላቸውን ፍላጎት፣ ልምምድና ዕውቀት በተመረጡ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በሙከራዊ ጥናት (True Experiment) ማረጋገጥ ነው።

የማንበብ ክሂል ለመፃፍ ክሂል ወይም የመፃፍ ክሂል ለማንበብ ክሂል ያለው ድጋፍ ምን ያህል የጎላ እንደሚል፣ የምክንያትና የውጤት ግንኙነታቸውንም ለማሳየት የወደፊት ምርምሮችን የሚጠይቅ ነው። ነገር ግን ከጥናቱ ዓላማ በመነሳት ቀጣዮችን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል።

- የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ትስስርና መደጋገፍ ምን ያህል ነው?
- አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በማጣመርና በማቀናጀት ማስተማር ይቻላልን?
- የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት የማስተማር ልምምዱ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን ለማሻሻል ይረዳ ይሆን?

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ለመምህራን፣ ለተማሪዎችና ለትምህርት መማሪያ አዘጋጆች ጠቀሜታ ሊኖረው እንደሚችል ይገመታል። በአንድ ትምህርት ቤትና በሁለት የመማሪያ ክፍል የተካሄደ ጥናት ለሁሉም ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ወካይ ሆኖ ይሠራል ብሎ ማጠቃለል አይቻልም። ነገር ግን ጥናቱ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች በማስገኘት ረገድ አስፈላጊ ይሆናል።

- መምህራንና ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች በውህደት መቅረባቸው ያለውን ጠቀሜታ ተገንዝበው የመማር ማስተማር ዘዴያቸውን ለመቃኘትና ለማስተካከል የሚያስችሉ አማራጮችን ያገኙበታል።
- መምህራንን የሚያሰለጥኑ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ለማንበብና ለመፃፍ ክሂሎች በውህደት አቀራረብ ትኩረት ሰጥተው በምን ዘዴ ትምህርቱ ውስጥ እንዲያካትቱት ያመላክታል።
- የአማርኛ ቋንቋ የመማሪያ/ማስተማሪያ፣ የመምህሩን መምሪያና የመርሀ ትምህርቱን መጽሐፎች የሚያዘጋጁ የትምህርት ባለሙያዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ያላቸውን የጠበቀ ግንኙነትና ትስስር በመረዳት በውህደት ለማስተማር የሚያስችሉ ሆነው እንዲያዘጋጁ ያግዛል።
- በዚህ ርዕስ ዙሪያ/ ለሚሰሩ የወደፊት ተመራማሪዎች የማነሳሳትና ለመነሻም የሚሆን መረጃ የመስጠት አቅም ሊኖረው ይችላል።

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ ላይ አተኩሯል። ስለዚህ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ከሚመለከቱ ጉዳዮች በስተቀር ወደሌላ ዝርዝር የክሂሎች ትምህርት አሰጣጥ አያተኩርም።

ጥናቱ የክሂሎቹን ትስስርና ዝምድና እስከምን ድረስ እንደሆነ ፈትሾ ክሂሎቹን በተናጠል ወይስ በውህደት ማስተማር የተሻለውን መለየት ከጥናቱ ይጠበቃል። በመሆኑም አስፈላጊውን ስነ ትምህርታዊ መመሪያዎች በመከተልና ለአንድ ወር ተግባራዊ ሙከራ በማድረግ ክሂሎቹን በውህደት በማስተማርና በማለማመድ የሚኖረውን ጠቀሜታ ማሳየት ነው።

በዚህ ጥናት ውስጥ በትምህርት ይዘትነት የተካተቱት፣ የቀደመ ዕውቀትን መጠቀም፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ መተንበይና መገመት፣ መከለስና ማጠቃለል፣ ካነበቡት ተነስቶ ማንፀባረቅና ምሰላ ናቸው። በነዚህ ይዘቶች ተመስርቶ ለጥናቱ መሪ ጥያቄዎች መልስ ከመስጠት ሌላ በሌሎች ጉዳዮች ላይ አያተኩርም።

## 1.5 የቁልፍ ፅንሰ ሀሳቦች አጠቃቀም ብያኔ

1. አንብቦ የመረዳት ችሎታ (Reading comprehension ability) ተማሪዎች በራሳቸው ምርምርም ሆነ ለትምህርት የቀረበላቸውን ምንባብ መልዕክት መርምረው፣ ገምግመውና አመዛዝነው ለመረዳት ያላቸውን ችሎታ ለመለካት ወይም ለማወቅ የገባ ስያሜ ነው። ከራሳቸው ማህበራዊ ህይወትም ጋር በማነፃፀር የሚስማሙባቸውንና የማይስማሙባቸውን ያነፀባርቃሉ።

2. የመጻፍ ~~የመፃፃፍ~~ ክሂል (Writing Skill)፦ ድምር ሃሳብን በመጨረሻ የሰዋሰው ሥርዓቱን የጠበቀና ትርጉም ያለው የመፃፍ ሂደት ያከናውናሉ። ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን

ቴክስት ዋና ዋና ሃሳቦችን በመንቀስ አሳጥረው ይፅፉሉ፤ ከቴክስቱ ስወጡ አዳዲስ ቃላትና ሃረጋት ፍቻቸውን በፅሁፍ ይፈልጋሉ።

3. አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎች ውህደት (Reading-Writing Connections) ሁለቱን ክሂሎች ያለምንም ክፍተት በትስስራቸውና በዝምድናቸው ተመስርትና አዋህዶ የማቅረብ ሂደት ነው። ስለዚህ ኡደታዊ በሆነ መልኩ እያነበቡ የሚፃፍበት፣ እየፃፉ ደግሞ የሚነበብበት ሂደት ነው።

6

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

በዚህ ርዕስ ስር የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ጥምረትና መደጋገፍ፣ ማንበብና መፃፍን በውህደት የማቅረብ አስፈላጊነት፣ ማንበብና መፃፍን በጥምረት የማስተማሪያ ዘዴዎችና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ተካተው ቀርበዋል። በአጠቃላይ ከጥናቱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው ድርሳናት ለጥናቱ ከሚሰጡት ጠቀሜታና አስፈላጊነታቸው አንፃር እየተገመገሙ በሚከተለው መንገድ በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

### 2.1 የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ጥምረትና መደጋገፍ

በማንበብና በመፃፍ ክሂሎች መካከል ጥብቅ ትስስርና መደጋገፍ መኖሩንና በውህደት ቢቀርቡ የተሻለ እንደሆነ ምርምር ያደረጉ ባለሙያዎች ይገልፃሉ። እነ Harp (1996) መፃፍ አንብቦ የመረዳት ክሂልን ሊያሳድግ ይችላል። ማንበብ ደግሞ የመፃፍ ክሂልን ሊያጎለብት ይችላል። ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ በሚያነቡበት ጊዜ የአፃፃፍ ስልቱን የጭብጡን ምንነት፣ የታሪክ አወቃቀሩን በመገንዘብ ለሚያቀናብሩት ለራሳቸው ጽሁፍ ይገለገሉበታል። ይህም ሁለቱ ክሂሎች ያላቸውን ትስስር አመላካች እንደሆነ ገልጸዋል።

እነ Langer (2000) እንዳብራሩት አንድ ፀሐፊ እንዲሁ ከመሬት ተነስቶ አይጽፍም። የግድ በተለያዩ ደራሲያን የተፃፉ መጻሕፍትን ማንበብ ይኖርበታል። በተጨማሪ አንድ አንባቢ ከሚያነበው ጽሑፍ መልዕክት ብቻ አይቀበልም። የጽሑፉን መዋቅርና የአቀራረብ ስልቱንም ይገመግማል። ከጽሑፉም ትርጉም ይገነባል። በዚህም የተነሳ አንድ አንባቢ ከሚያነበው ጽሑፍ ከአንድ ደራሲ ከሚጽፈው ጽሑፍ ጋር በአቻነት መወዳደር በመቻሉ ምክንያት ትስስር አላቸው ቢባል ምክንያታዊ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ሁለቱም (ማንበብና መፃፍ) የማቀድ፣ የማርቀቅ፣ የመከለስና የመገምገም መሠረታዊ ተግባሮች ይከናወንባቸዋል። በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ማንበብና መፃፍ በጥብቅ የተቆራኙ ክንዋኔዎች እንደሆኑ ይገመታል። በማንበብና በመፃፍ ሂደት ወቅት አንባቢዎችና ጸሐፊዎች ሀሳባቸውን ለማደራጀት፣ ለማስታወስና ለመግለጽ የሚጠ

ቀሙባቸው ብልሀቶች ተመሳሳይ ናቸው። ጸሐፊዎችና አንባቢዎች ቋንቋን፣ እውነታን፣ ጥበብን፣ መዋቅርንና የመሳሰሉ ተመሳሳይ ዕውቀቶችን ይጠቀማሉ። ከዚህ በመነሳት አጥኚው ማንበብና መፃፍ እንደ አንድ ተመሳሳይ የማቀናበር ክንዋኔ ተደርገው ሊወሰዱ እንደሚችሉ ይገምታል።

ማንበብና መፃፍ ጥብቅ ትስስር ስላላቸው በውህደት ቢቀርቡ የተማሪዎችን በውህደት የማንበብና የመፃፍ ችሎታ ሊያሳድጉ ይችላሉ። የትምህርቱንም ይዘት በተገቢው መንገድ እንዲረዱት ሊያግዛቸው ይችላል። ክሂሎቹ የቀደመ እውቀትንና ነባር ልምድን የሚጠይቁ ተመሳሳይ ክሂሎች በመሆናቸውም ጭምር ነው (Ruddel 1997)።

ሁለቱም ትርጉም የመገንባት ሂደት ስለሚከናወንባቸው ዝምድናቸው ቀጥተኛ እንደሆነ ገልጿል። ማንበብ ለመፃፍ ትርጉም የመስጠት ተግባር ነው። አንባቢው ነባር ዕውቀቱንና የቀደመ ልምዱን በመጠቀም፣ ከጽሑፉ የሚያገኘውን መረጃ፣ የሚወስደውን አቋም፣ የሚያስታውሰውን ወይም የሚገምተውን ማህበራዊ መስተጋብርና ግንኙነት በማዋሃድ ትርጉም ሰጥቶ ሊጽፍ ይችላል።

ብዙ መምህራን ማንበብን ተቀባይ ክሂል (Receptive Skill) ብቻ እንደሆነ አድርገው ይገምታሉ። ይህን ሀሳብ በተመለከተ May (1990) እንዳስረዳው በእርግጥ ማንበብም እንደ መፃፍና መናገር ሃሳብ ማደራጀትና መረዳትን ይጠይቃል። በዚህ ረገድ ክሂሎቹ የሚጋሯቸው አእምሯዊ ሂደቶች አሉ። ማንበብ ሃሳብን ከተፃፈ ነገር ለመረዳት ጥረት የማድረግ ሂደት ነው። መፃፍ ደግሞ መልዕክትን በጽሑፍ በማስፈር አንባቢው ሃሳቡን እንዲረዳው የማድረግ ሂደት ነው። በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች አንብበው የጽሑፉን ሃሳብ ለመተንተን፣ የተገነዘቡትን ለማንጸባረቅ፣ በጥንድና በቡድን ለመረዳዳት ማንበብና መፃፍን በውህደት ሊማሩ ይገባል።

በአጠቃላይ ማንበብ በሌሎች የተፃፉ ዓረፍተ ነገሮችን በመገልገል የሰዎችን አስተሳሰብ ወደ ጠቃሚ ልምድ፣ መርህና ዕውቀት ስለሚመራ እንደመፃፍ ሁሉ አፍላቂ ሂደት ነው። በመሆኑም ማንበብና መፃፍ የጋራ የሆነ ባህሪይ አላቸው ቢባል ምክንያታዊ ይሆናል። ድርሰት መፃፍ ወደ ተሻለ የማንበብ ሂደት ሊመራ ይችላል። ማንበብ ደግሞ ወደ ተሻለ የመፃፍ ችሎታ ሊያሸጋግር ይችላል። ይህ ዓይነቱ የሁለትዮሽ ግንኙነት ማንበቦ የመረዳትና የመፃፍ ግንኙነት በመባል ይታወቃል። ምክንያቱም ፀሐፊውም ሆነ

አንባቢው የሚጨነቅት ለአንድ ጽሑፍ (ሀሳብ) ትርጉም መስጠት ወይም መረዳት መቻል ላይ እንደሆነም አስገንዝቧል።

ማንበብና መፃፍ ሁለቱም ማቀድን፣ ማቀናበርንና መከለስን የሚሻ የጋራ ባህሪይ ይኖራቸዋል። ጥሩ ጸሐፊዎች አንድን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ዕቅድ እንደሚነድፉ ሁሉ ጥሩ አንባቢዎችም ማንበብ በሚፈልጉበት ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ የቀደመ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ዓላማ በመንደፍ ዕቅድ ያዘጋጃሉ። ከሚያነቡት ጽሑፍ በመነሳትም የራሳቸውን ትርጉም ይገነባሉ። ስለሚቀጥለው ሀሳብ ወይም ሁኔት ይተነብያሉ። ባነበቡት ቁጥርም ይከልሳሉ። ስለዚህ ከነዚህ ሦስት መሠረታዊ ተመሳስሎዎች በመነሳት በሁለቱ ክሂሎች መካከል ትስስር አለ ቢባል ምክንያታዊ እንደሆነ (Ruddel 1997) ገልጿል።

Ruddel የማንበብና የመፃፍ ትስስርን በሚመለከት በሚከተለው መንገድ አቅርቦታል፡-




ምስል 1፡- የአእምሮታዊ ሂደት ካርታ፡ (Ruddel 1997፡33)

Conley (1997) የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ከተመሳሳይ ሥነ ልቦናዊ ዕውቀትና አእምሮአዊ ሂደት የሚመነጩና አንድ አይነት ክህሎትን የሚጋሩ እንደሆኑ ገልጿል። የሁለቱም መሠረታዊ ዓላማ የቋንቋውን ሆሂያትና ቃላት በመለየት ማወቅና ለማንበብ ወይም ለመፃፍ መገልገል መቻልን ነው። ተማሪዎች ለሆሄያት፣ ለቃላትና ለሆሄያት ዕውቀት ከተጋለጡ የማንበብና የመፃፍ ችሎታቸው በፍጥነት ሊጎለብት እንደሚችልም ገልጿል።

May (1990) ተማሪዎች ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን በሚጽፉበት ጊዜ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ሊዳብር ይችላል። ይህ ደግሞ ክሂሎቹ ትስስር እንዳላቸው ያስገነዝባል። አንባቢዎችና ፀሐፊዎች የሚሰሯቸው ክንዋኔዎች ልክ በመስታወት ውስጥ እንደሚታይ የአንድ ቁስ አካል ምስልና ራሱን ቁስ አካሉን ያህል ትስስር አላቸው። አንባቢዎችና ፀሐፊዎች ለማንበብና ለመፃፍ በሚዘጋጁበት ጊዜ ሁለቱም ተገቢ አካባቢ ይፈጥራሉ። ለማንበብ ወይም ለመፃፍ የራሳቸውን ዓላማ ይነድፋሉ፣ ፍላጎትም ይኖራቸዋል። የቀደመ ዕውቀታቸውን ይጠቀማሉ። አእምሮአዊ ምስል ይፈጥራሉ። የፀሐፊዎች ፍላጎት ሀሳባቸውን ለሌሎች በማካፈል መረጃ መስጠት ወይም ሰዎችን ማዝናናት ሊሆን ይችላል። ስለዚህ የመግባቢያ መንገዳቸውም የተዘጋጀው ጽሑፍ ነው። የአንባቢዎች ፍላጎት ደግሞ መረጃ ለማግኘት፣ ሀሳብ ለመጋራትና ለመዝናናት ጽሑፍ ማግኘት ነው። በመሆኑም ፀሐፊውና አንባቢው በተዘጋጀው ጽሑፍ ይገናኛሉ።

ከላይ ከቀረቡት ትውረቶች በመነሳት አጥኚው ክሂሎቹን በውህደት ማስተማር የተሻለ ዘዴ እንደሆነ ይገምታል። ስለዚህ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ትስስር መሠረት በማድረግ የክሂሎቹ በውህደት መቅረብ ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ጠቀሜታ በሚመለከት ተመራማሪዎች ያቀረቡት ጽንሰ ሃሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 2.2 ማንበብና መፃፍን በውህደት የማቅረብ አስፈላጊነት

የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ትስስር ቀደም ሲል ለማሳየት ተሞክሯል። የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት አቀራረብና ጠቀሜታውን አስመልክቶ ተመራማሪዎች የተለያዩ ጽንሰ ሃሳቦችን ያቀርባሉ። ለምሳሌ Conley (1997) የማንበብና የመፃፍ ክንዋኔዎችን በውህደት ማስተማር የተማሪዎችን የማንበብና የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ

ጠቃሚ ዘዴ እንደሆነ ይገልፃሉ:: በተጨማሪም ማንበብና መፃፍ በዕለት ተዕለት የመማር ክንዋኔዎች ላይ ትርጉም መገንባት የሚያስችሉ የቋንቋ ሂደቶች እንደሆኑም አስገንዝቧል:: በመሆኑም አንዱ ክሂል ሌላውን ለማዳበር መሠረታዊ ጠቀሜታ ያለውና እርስ በርሳቸውም የሚደጋገፉ በመሆናቸው ጭምር ነው::

በአጠቃላይ የተማሪዎችን የቋንቋ መማር ፍላጎት ሊያሳድግ እንደሚችል ይገመታል:: ስለዚህ የፈጠራ ችሎታቸውን ሊያጎለብት ይችላል:: እንዲሁም የተገኙ ልምዶችን እንዲያጠናክሩ ያግዛል:: ስለዚህ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት ማስተማር ያለው ጠቀሜታ ተማሪዎች የሚያነቡትን ጽሑፍ ለመረዳት ያገዟቸውን ዘዴዎች እየተገነዘቡ በመጡ ቁጥር ሀሳባቸውን በጽሑፍ መግለጽ ይጀምራሉ:: በመሆኑም እነዚያን ዘዴዎች በጽሑፋቸው መገልገል መቻላቸው የፈጠራ ችሎታቸውን ሊያጎለብትላቸው እንደሚችል ገልጿል::

መፃፍ በየዕለቱ የሚከወን ተግባቦታዊ ሂደት ሆኖ ሲዳብር ማንበብም በዚያው መጠን ሊጎለብት ይችላል:: ምክንያቱም በማንበብና በመፃፍ መካከል ያለው መስተጋብር የተመሠረተው በተግባቦት ላይ ስለሆነ ነው:: ስለዚህ ሁለቱም ሂደቶች በተማሪዎች የመግባባት ፍላጎት ሊዳብሩ ይችላሉ:: ማንበብና መፃፍ ተግባቦታዊ ሂደቶች ከሆኑ ደግሞ አንባቢው ከፀሐፊው ስሜት አንፃር ሊያነብ ይችላል:: ስለዚህ አንባቢው ሲያነብ ጸሀፊው በጽሑፉ ያስተላለፈውን መልዕክት ሊረዳ ይችላል:: ፀሐፊውም መልዕክቱን አንባቢው ሊረዳው በሚችል መንገድ ግልጽ አድርጎ ሊያቀርብ ይችላል:: ከዚህ አንፃር ተማሪዎች እራሳቸውን ከአንባቢና ከፀሐፊ ጎራ በመመደብ በጽሑፉ የቋንቋ ቅርጾችና አጠቃቀሞችን በመገልገል ዕውቀትን ሊገነቡ ይችላሉ:: ምክንያቱም ተማሪዎች ማንበብና መፃፍን ማወቅ ይፈልጋሉና:: የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች የዕውቀት ሂደት ተመሳሳይ ሲሆን ጠቀሜታውም የላቀ ነው Conley (1997)::

እነ Harp (1996) እንደገለጹት መፃፍ በተፈጥሮው ተንታኝ ክሂል ነው:: አንዱ የመፃፍ ችሎታቸው ከዳበረ አንድን ጽሑፍ በሚያነቡበት ጊዜ የጽሑፉን ይዘት ከመረዳት በዘለለ የቃላት ትርጉምችግር አያጋጥማቸውም:: መምህራን የመፃፍና የማንበብ ክንዋኔዎችን በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ በማካተት መልመጃዎችን ካቀረቡ የተማሪዎች የማስታወስና የመረዳት ችሎታ ሊጎለብት ይችላል:: በውህደት አንብቦ መ ዳትና የመፃፍ ክሂሎች የግለሰቦችን ወ ጋማዊ መነሳሳት የሚጠይቅ ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊና ስነ ልሳናዊ የሀሳብ

ግንባታ ሂደቶች ናቸው። በተጨማሪም በርካታ የጋራ ዓላማ ያላቸው እውቀትን የማፍለቅና የማስተላለፍ ሂደቶች ናቸው።

የተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ችሎታ የሚዳብረው በየዕለቱ በሚያደርጉት የማንበብና የመፃፍ ልምምድ እንደሆነ Beerdgew (2003) ገልጿል። በዋነኛነት ሁለቱ ክሂሎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በውህደት ከቀረቡ ክሂሎቹ ሊጎለብቱ ይችላሉ። የተማሪዎችን አስተሳሰብም ሊያሳድጉ ይችላሉ። በተጨማሪም በጥንድና በቡድን በሚሰሩ ክንዋኔዎች ላይ ሁሉም ተሳታፊ እንዲሆኑ እድል ይሰጣል። ተማሪዎች ከአንድ በላይ ክሂልን በሚጠ ላይ ሁሉም ተሳታፊ ... ይቅ መልመጃ ላይ እንዲያተኩሩ በማድረግ ቋንቋውን በብቃት እንዲገለገሉበት ማድረግ ይቻላል።

የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች በውህደት መቅረብን በተመለከተ Block (1997) እንዳብ ራራው ተማሪዎች የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን እንዲተነትኑ፣ እንዲተረጉሙና እንዲገመማ ... ሙ ያግዛቸዋል። እንዲሁም የማንበብና የመፃፍ ፍላጎታቸውን በመጨመር በህይወት ዘመናቸው ከሰዎች ጋር ተግባቦትን እንዲፈጥሩ፣ እንዲዝናኑ፣ ሌሎች የትምህርት ዓይነቶችን በተገቢው መንገድ መማር እንዲችሉ፣ ባህለ ብዙነትን እንዲረዱና ወደፊት ሊከሰቱ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ የመተንበይ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ሊያግዛቸው እንደሚችል ገልጿል።

Kennedey (1994) ማንበብና መፃፍ ጎን ለጎን የሚሄዱ፣ የተያያዙና የሚደጋገፉ ከሆነ ሁለቱን ክሂሎች አቀናጅቶ ማቅረብ ውጤታማ ነው ቢባል ተጠየቃዊ ይሆናል። ክሂሎቹ በቅንጅት ከቀረቡ ደግሞ ተማሪዎቹ የማንበብና የመፃፍ ሂደትን፣ ክህሎትንና ብልሀትን በመረዳት ስኬታማ አንባቢና ጸሐፊ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም አንዱን ክሂል በሌላው መማርን ይለምዳሉ። ከዚህ አንፃር ማንበብና መፃፍን በውህደት ማስተማር ጠቀሜታ ውን የጎላ ሊያደርገው ይችላል።

በአጠቃላይ በመፃፍ ሂደታዊ አቀራረብ ተማሪዎች ሃሳባቸውን እንዲያብራሩ መንገድ ይከፍትላቸዋል። ስለዚህ ይዘት ተኮር የማንበብ ሂደትም ጥራት ያለው ድርሰት ለመፃፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦን ያበረክታል። የማንበብና የመፃፍ እድገት የሚመጣው ሁለቱ ክሂሎች በውህደት ሲቀርቡ ይሆናል። ማንበብና መፃፍን በውህደትና በቅንጅት ማቅረብ ማለት የቋንቋውን ክንዋኔ ተግባራዊ ማድረግ እንደሆነም አስገንዝቧል። ስለዚህ አጥኚው

በዘርፉ ተመራማሪዎች ትወራ መሠረት ክሂሎቹ በውህደት መቅረባቸውን ጥቅሙ የጎላ እንደሆነ በመገመቱ ሙከራዊ ጥናቱን አካሂዷል።

## 2.3 ማንበብና መፃፍን በጥምረት ማስተማሪያ ዘዴዎች

የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች በውህደት ከቀረቡ ለቋንቋ ትምህርቱ ዕድገት ያላቸውን ጠቀሜታ፣ ትስስራቸውንና መደጋገፋቸውን በሚመለከት ቀደም ሲል በቀረቡት ትወራዎች ለማሳየት ተሞክሯል። አንብቦ የመረዳትንና የመፃፍን ክሂሎች በውህደት ለማስተማርና ለማለማመድ የተለያዩ ዘዴዎች እንዳሉ የመስኩ ተመራማሪዎች ይገልፃሉ። ለምሳሌ Block (1997) የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ በመኖሩ ምክንያት የወቅቱ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ አብይ ጥያቄ እንደሆነም ያስረዳል። በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አንብቦ መረዳትና ጽሑፍ ማቀናበርን ሊያጎለብቱ የሚችሉ በርካታ ብልሀቶች እንዳሉም ገልጿል። በተለይ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሁሉንም ዓይነት ፅሑፍ አንብቦ ለመረዳትና ማንኛውንም ታሪክ በተሳካና ብዥታን በማይፈጥር መልኩ አቀናብሮ ለመፃፍ ከሚያስችሉ ብልሀቶች ውስጥ ጥያቄ መጠየቅ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ ማጠቃለል፣ መተንበይና መገመት፣ በጥልቀት ማሰብ ይገኙበታል።

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ጥያቄ መጠየቅ በውህደት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ለማሳደግ ጠቀሜታ እንዳለው የተለያዩ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ። ለምሳሌ Airasian (1997) እንዳብራራው በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ጥያቄ የሚያቀርቡ ከሆነ ሀሳባቸውን በቃላት ጽፈው እንዲገልጹ፣ በጥልቀት እንዲያስቡ፣ ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉና እንዲነቃቁ ስለሚያደርግ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ አስረድቷል። የተማሪዎች የጥያቄ አቀራረብ ስልት ምን ይመስላል? ክሂሎቹን ለማሳደግ ከተማሪዎች ምን ይጠበቃል? የሚሉት መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው። ጥያቄ መጠየቅ ከቀደመ እውቀትና ልምድ የሚመነጭ ነው። በመሆኑም የጠያቂውን የማስታወስ ችሎታና ጉዳዩንም የዕለት ተዕለት ተግባር አድርጎ የመያዝ ብቃቱንም የሚመለከት ጉዳይ ነው። ተገቢ ጥያቄ በተገቢ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ላይ ማቅረብ ደግሞ

በተግባራዊ ልምምድ የሚዳብር ችሎታ ነው:: ስለዚህ ተማሪዎች ተገቢ ጥያቄ መጠየቅን መማር አለባቸው ማለት ነው::

ተማሪዎች ወደ ቡድንም ይሁን ወደ ግል ሥራ ከመግባታቸው በፊት ዝርዝር ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን የማቅረብ ኃላፊነት እንዳለባቸው መምህራን ዕውቅናው እንዲኖራቸው ማድረግ ይጠበቅባቸዋል Gary (1995):: በተጨማሪም ተማሪዎች እያነበቡ ወይም እየፃፉ እያሉና ካነበቡ ወይም ከፃፉ በኋላ እንዲያሚሉ በማድረግ ምን አውቃለሁ? ለማወቅ የምፈልገው ምንድን ነው? ያወቅሁት ምንድን ነው? ወይም ምን ተምሬያለሁ? የሚሉ ጥያቄዎችን ሲያነሱ ግንዛቤያቸውን ያጎለብትላቸዋል:: እንዲሁም እነ Cole (1994) እንዳስረዱት ጥያቄ የመጠየቅ ችሎታን ለማጎልበት ነፃ ተዛምዶና አሰሳ (free association and skim) መጠቀም ሌላው አማራጭ ነው ይላሉ:: ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ተማሪዎች እያነበቡ ወይም እየፃፉ እያሉ አዲስ ጉዳይ ሲያጋጥማቸው በአእምሯቸው የሚታሰባቸውን እንዲጽፉ ማድረግ ነው:: በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት መምህራን ተማሪዎቻቸውን ሲያነቡና ሲጽፉ ጥያቄ እንዲያቀርቡ ሊያበረታቷቸው ይገባል:: ተማሪዎቹ ከተበረታቱ የመማር አቅማቸው ይጎለብታል:: እንዲሁም ከመምህሩ ጋር የሚኖራቸው መስተጋብር ይጠነክራል::

Block (1997) ጥያቄ መጠየቅን በሚመለከት ያቀረበው ጽንሰ ሃሳብ ተማሪዎች አዳዲስ ሀሳቦችን ቀደም ብለው ከሚያውቁት ጋር አጣጥመው እንዲያደራጁ ይረዳቸዋል:: ጥያቄ የመጠየቅ ተግባር በራሱ ዕውቀትን የማዳበር ክንውን ነው:: ከዚህ በመነሳት አጥኚው ተማሪዎች ሲያነቡና ሲጽፉ በርካታ ጥያቄዎችን በጠየቁ ቁጥር ትምህርቱን የመረዳት ችሎታቸው እየጎለበተ ሊሄድ እንደሚችል ያምናል:: ስለዚህ ተማሪዎች ጥሩ ጥያቄ አቅራቢዎች እንዲሆኑ ሊለማመዱ እንደሚገባም ያስገነዝባል::

አንብቦ መረዳትና ጽሑፍ ማቀናበርን በውህደት ለማስተማር ከሚያገለግሉት ብልሀቶች መካከል ማብራራትና መተርጎም (explaining and interpreting) ተጠቃሾች እንደሆኑ (Block 1997) ያስረዳል:: በእነዚህ ብልሃቶች ተማሪዎች ያነበቡትን ነገር በመፃፍ እንዲያብራሩና ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ የመረዳት ችሎታቸውን ለመገንዘብ የሚሞከርባቸው ዘዴዎች ናቸው:: ተማሪዎች እነዚህን ብልሃቶች ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ስለአነባቡት ጽሑፍ ዝርዝር ማብራሪያ፣ ትርጉምና ትንተና በጽሑፍ መስጠት የሚችሉበት ዕድል ይፈጥርላቸዋል::

ከዚህ ሌላ Ramonda (1997) እንዳብራራው ተማሪዎች ያነበቡትን ጽሑፍ ፍሬ ሀሳብ ለምን በዚያ መንገድ እንደተረዱትና ፍሬ ሀሳቡ ይህ ነው ብለው ለማጠቃለል ያበቋቸው መረጃዎች ምን እንደሆኑ ምክንያታቸውን ዘርዝረው እንዲጽፉ ቢደረግ ጥሩ እንደሆነ ገልጿል:: በሌላ መንገድ የዘነጓቸውን ጠቃሚ ዝርዝር መረጃዎች ያስታውሳሉ:: ዝርዝር ጉዳዮችን ማስታወስ ደግሞ ምን፣ መቼ፣ የት፣ ለምንና እንዴት ከዋናው ሀሳብ ወይም ጭብጥ ጋር እንደሚገናኝ ለማወቅ ይረዳል:: ይህም በተራው ጭብጡን አስመልክቶ መደምደሚያ ላይ ያደርሳል:: ይህን በማድረግ በውህደት የማንበብና የመፃፍ ችሎታቸውን ማጎልበት እንደሚቻል አስገንዝቧል::

Gary (1995) ይህንን ሀሳብ በመጋራት ተማሪዎች ከመጀመሪያው ንባብ በኋላ በሚያዘጋጁት የውይይት ክንዋኔዎች ሀሳባቸውን እንዲለዋወጡ የሚገፋፉ መሆን ይኖርባቸዋል:: ከእነዚህ ክንዋኔዎች በኋላ ተማሪዎች ስለጽሑፉ ያላቸውን ግንዛቤ ይተነብያሉ፣ ትርጉም ይሰጣሉ፣ ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችን ይመረምራሉ:: ሌላው ደግሞ ተማሪዎች ላነበቡት ወይም ለፃፉት ነገር ማጠቃለያ መስጠት ከቻሉ ላነበቡት ወይም ለፃፉት ይዘት በቂ መረጃ ያላቸው መሆኑን ይጠቁማል:: ይህም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ እንደ መሠረታዊ የአንብቦ መረዳትና የጽሑፍ ማቀናበር ችሎታን ማጎልበቻ ብልሀት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል::

ማጠቃለልን (summarizing) በሚመለከት Block and Mangeri (1995) ያቀረቡት ጽንሰ ሃሳብ ተማሪዎች ከሚያነቡት ጽሑፍ በአእምሯቸው የታሰባቸውን በጽሑፍ የሚያጠ ቃልሉ ከሆነ፣ የማስታወስ ወይም ዕውቀትን ይዞ የመቆየት ችሎታቸው 16% ያህል እንደሚጨምር ገልጸዋል:: ስለዚህ ተማሪዎች በሚያነቡበት ወቅት በየደረጃው በጽሑፍ ማጠቃለያ እየሰጡ መሄድ የሚያስችሏቸውን ብልሃቶች መማር ይገባቸዋል::

መተንበይና መገመት(inferring and predicting) ከጽሑፍ አንብቦ የተገኘን መረጃ ከቀደመ ዕውቀቱ ወይም ገጠመኙ ጋር አዛምዶ የተለየ ትርጉም የሚሰጥበት ወይም ስለሚያነበው ሃሳብ ምክንያታዊ ግምገማ ወይም ዳኝነት ለመስጠት አማራጮችን የሚጠቀምበት ልዩ ስልት ነው Barrs (2000):: መተንበይን በሚመለከትም የሰጠው ማብራሪያ በቋንቋ ትምህርት አንድን ጽሑፍ በማንበብ ላይ እያሉ የገፀ ባህሪያትን ማንነት፣ ድርጊት፣ ተንኮልና ሴራ በመረዳት ከወዲሁ ንባባቸውን ሳይጨርሱ ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን

ሁኔታ በመተንበይ መደምደሚያ ላይ ይደርሳሉ። ይህም ሁኔታ የሚያመለክተው ደግሞ ተማሪዎቹ ጽሑፉን በአግባቡ መረዳታቸውን በመፃፍ የሚገልጹበት እንደሆነ ገልጿል።

Ramonda (1997) ምስላን (imaging) በሚመለከት ያቀረበው ጽንሰ ሃሳብ በተነበበው ጽሑፍ ውስጥ የተገለጹ ትዕይንቶችን፣ ድርጊቶችን፣ ክስተቶችንና ገፀባህሪያትን ምስል በህሊና ውስጥ የመቅረጽ ሂደት ነው። ተማሪዎች የሚያነቡትና የሚጽፉት ምስል እየፈጠሩ ይሆናል። በዚህ ጊዜ የተማሪዎች ትኩረት ከቋንቋው ባሻገር በቋንቋው በሚገለጸው ጉዳይ ላይ ስለሚሆን በውህደት የማንበብና የመፃፍ ችሎታቸውን ሊያጎለብትላቸው ይችላል። ይህንንም ለአንባቢዎችና ለጸሐፊዎች ማስተማር አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት እያነበቡ ወይም እየፃፉ እያሉ በንቃት እንዲያስቡ ስለሚያስችላቸው እንደሆነም ገልጿል።

ምስል ከሳች ጽሑፎችን እንዲያነቡ ማድረግና እያነበቡ እያሉ በአእምሯቸው የመጣውን ምስል እንዲጽፉ በማድረግ ማለማመድ ይቻላል። የክፍል መምህሩ ይህን ስልት ተማሪዎቹ እንዲያውቁት ማድግ አለባቸው። በሚያነቡበት ወይም በሚጽፉበት ጊዜ የገፀ ባህሪያቱን ወይም የታሪኩን ምንነትና እንዴትነት አስቀድመው በአእምሯቸው በመሳል ሊያጋጥም ወይም ሊሆን ከሚችለው ነገር ጋር በማዛመድ እንዳይረሱት ያደርጋቸዋል። የጽሑፉን ታሪክና አላባውያን በአእምሮ በመሳል በውህደት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት አስረድቷል። ተማሪዎች በሚያነቡበት ወይም አንድን ጽሑፍ በሚያቀናብሩበት ወቅት አእምሯዊ ምስላን ይጠቀማሉ። ስለዚህ ውስጣዊ ስሜታቸውን ከገሃዱ ዓለም ጋር በማዋሃድ አእምሯዊ ብቃታቸውን ለማሳደግ የላቀ ጠቀሜታ እንዳለው (Block 1997) አስገንዝቧል።

የክፍል ተማሪዎችን ምናባዊ እይታ ለማሳደግ ተማሪዎቹ ምስል ከሳች የሆኑ ታሪኮችን፣ ስሞችን፣ ቃላትንና የመሳሰሉትን እንዲያውቁና እነዚያን ሲያነቡ በአእምሮአቸው ምን ምስል እንደተቀረጸ አብራርተው እንዲጽፉ በማድረግ፣ ችሎታቸውን ማጎልበት ከክፍል መምህሩ የሚጠበቅ ተግባር ነው በማለት (Mayo 2000) አስረድቷል። መምህሩም ይህን ተግባር በሚያለማምዱበት ወቅት ተማሪዎቹ ምናባዊ ምስሉን ለመግለጽ ቁልፍ ቃላቱ የትኞቹ እንደሆኑ እርስ በእርሳቸው በመወያየት እንዲለዩ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ሌላው ስልት ደግሞ ተማሪዎቹ የቀረበላቸውን ምንባብ በእርምጃ እንዲያነቡ ማድረግና በማንባብ ላይ እያሉ በአእምሮአቸው የመጣላቸውን ምስል

እንዲጽፉ ማድረግ ይቻላል። በመቀጠል እጃቸውን በማውጣት የፃፉትን እንዲያነቡ በማድረግ ክሂሎቹን ማዳበር ይቻላል። ከዚህ በመነሳት አጥኚው የመስኩ ተመራማሪዎች ክሂሎቹን በውህደት ለማስተማር ያቀረቧቸውን ብልሃቶች በመተግበር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና ጽሑፍ የማቀናበር ክሂሎችን ማጎልበት መቻል ወይም አለመቻሉን ለማረጋገጥ ይህን ሙከራዊ ጥናት አካሂዷል።

ከዚህ ሌላ የጥልቅ አስተሳሰብ ብልሃት አንብቦ ለመረዳትም ሆነ ጽሑፉን ለማቀናበር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው (Unrau 2004) ያስረዳል። እንደባለሙያው ማብራሪያ ጥልቅ አስተሳሰብ በተማሪዎች ውጤት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ አለው። እንዲሁም የተማሪዎችን የማንበብም ሆነ የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ አይነተኛ ብልሃት ነው በማለት አስገንዝቧል። ይህንም ብልሃት ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ትልቁ ሥራ ተማሪዎችን ግለ ግምገማና ግለ ቁጥጥር ማድረግ ነው። ለዚህም በዋናነት ይህንን ሀሳብ ተረድቸዋለሁ። ይህንን ሀሳብ ደግሞ አልተረዳሁትም። ስለዚህ ምን ማድረግ አለብኝ? ብለው እራሳቸውን መጠየቅ ይኖርባቸዋል። ይህንን ጥያቄ የሚጠይቁት ወይም ግለ ቁጥጥር የሚያደርጉት በማንበብ ላይ እያሉና ካነበቡ በኋላም ሊሆን ይችላል። የንባባቸው ቁም ነገር ግን ለማንበብ ብቻ ሳይሆን አንብቦ ለመረዳት መሆን ይኖርበታል። በዚህም መሠረት ተማሪዎቹ እያንዳንዱን አንቀጽ በጥሞና በማንበብ ብዥታ የሚፈጥር ሃሳብ ካለ በጥልቀት በመመርመር አእምሮአዊ ብቃታቸውን በመጠቀም አብራርተው በመፃፍ ማሳየት ይኖርባቸዋል።

እነ Smith (1984) ጽሑፍን በማቀናበሩ ረገድ ያቀረቡት ጽንሰ ሃሳብ ተማሪዎች በተመሳሳይ መንገድ ጠንካራ ይዘት ያለው ጽሑፍ ለማቅረብ አእምሮአቸውን ማሰራት ይጠበቅባቸዋል። ይህንን ተግባር በማከናወን ሂደት ተማሪዎቹ ራሳቸውን የሚጠይቋቸው በርካታ መሠረታዊ ጥያቄዎች መኖራቸውን አክለው አስረድተዋል።

ለምሳሌ፡- በፃፍኩት አንቀጽ ውስጥ ካሉት ዓረፍተ ነገሮች የትኞቹ የተሻሉ ናቸው? ያለአገልግሎት የገቡ ቃላት አሉ ወይ? ዓይነት ጥያቄዎችን መሠረት በማድረግ ተማሪዎቹ ሌሎች መሠረታዊ ጥያቄዎችን ሊያነሱ ይችላሉ። በምጽፈው አንቀጽ ውስጥ በቂ መረጃዎችን ያላካተትኩት ለምንድን ነው? አስፈላጊውን መረጃ አካትቻለሁ ወይ? ዓይነት ጥያቄዎችን ሊጠይቁም ይችላሉ። ቀደም ሲል እንደተገለጸው በውህደት አንብቦ

የመረዳትና ጽሑፍ የማቀናበር ችሎታቸውን ለማሳደግ የሚረዱ በርካታ ብልሃቶች መኖራቸው ተጠቁሟል።

- የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ለማስተማር ከንባብ በፊት፣ በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የመፃፍ ክንዋኔዎችን በማዘጋጀት ተማሪዎቹ ሃሳባቸውን እንዲያደራጁ በማድረግ ረገድ የሚገፋፉ ሊሆኑ ይገባቸዋል (Gary 1995)። ክንዋኔው ቀላልና የተወሰነ ማስታወሻ የመያዝ ዓይነት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ተማራዎቹ በሚያነቡበት ጊዜ የቃላትን ትረጉም ከአገባባቸው መረዳት ሊሆን ይችላል። በአጠቃላይ ክንዋኔው በማንበብና በመፃፍ ትስስር ላይ ያለመ በከፍተኛ ጥንቃቄ የተዘጋጀ ሊሆን ይገባል። ተማሪዎቹ በተከታታይ የሚሰሯቸው የመፃፍ ክንዋኔዎች በቅድመ ንባብ ክንዋኔው ቁልፍ የቃላት ዝርዝር ሊቀርብላቸው ይችላል። ካልሆነም የጽሑፉን መግቢያ ካነበቡ በኋላ ለምሳሌ ተማሪዎቹ የቀደመ ዕውቀታቸውን በመጠቀም ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በጋራ በመወያየት ምንባቡን በማንበብ ምላሽ ለመስጠት ያቀዷቸውን ጥያቄዎች እንዲጽፉ ሊጠየቁ ይችላሉ።

Unrau (2004) የክሂሎቹን በውህደት አቀራረብ በሚመለከት ያቀረበው ጽንሰ ሃሳብ ተማሪዎች በመፃፍ ለማንበብ ምላሽ እንዲሰጡና የተለያዩ ሃሳቦችን እንዲያነሱ የሚገፋፉ ሊሆኑ ይገባቸዋል። ስነ ጽሑፋዊ ለሆኑ ስራዎች፣ ተንኳሽ ስለሆኑ ገፀ ባህሪያት ወይም ጭብጦች፣ አወዛጋቢ ለሆኑ ጥያቄዎች (Controvetial Issues) መጠየቅ ይኖርባቸዋል። በሁለቱም ጉዳዮች ላይ ጥያቄው በከፍተኛ ደረጃ ስሜት ቀስቃሽ ከሆነ በመፃፍ ላይ ጠንካራ ምላሽን ያስከትላል። ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ የሚሰሩት ክንዋኔ የክለሳ ጽሑፍን ሊያጠናክር ይችላል። በቀረበው ሃሳብ ላይ እንደገና እንዲያስቡ የሚገፋፉ ሊሆኑ ይገባቸዋል።

ለምሳሌ ተማሪዎቹ ላነበቡት በጽሑፍ ምላሽ ከሰጡ በኋላ በመፃፍ ጊዜ ጓደኞቻቸው ጋር በመረዳዳት የተፃፈውን መረጃ በማንበብ በማስታወሻቸው ላይ የያዙትን ሊከልሱ ይችላሉ። በወረፋም አንደኛው/ዋ የፃፏቸውን መረጃ ድምጹን/ዋን ከፍ አድርጎ/ጋ በማንበብ ለምላሹም ሆነ በምርምር ለተገኙ ጥያቄዎች ማስታወሻ ይይዛሉ። በመጨረሻም የመጀመሪያውን ጽሑፋቸውን እንዲከልሱ ይደረጋል። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለውን ድህረ ክለሳ በማድረግ በደበኛ የምላሽ ወረቀት ይጽ ፉ። በዚህም

ከመጀመሪያው ምላሻቸው ምን ያህል እንደተለወጡ አብራርተው ነጸጽፉ በማድረግ ማለማመድ ይቻላል።

ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ በሚያነቡበት ጊዜ እንዲጽፉ፣ ራሳቸውን እንዲቆጣጠሩና የማንበብ ልምዳቸውን እንዲያስተካክሉ የሚገፉፉ መሆን ይኖርባቸዋል (Ramonda 1997)። ለዚህም ተግባር መምህሩ የማንበብ ሥራ ከመስጠቱ በፊት በምንባቡ ውስጥ ሊመለሱ የሚችሉ የሂደት ጥያቄዎችን ሊያቀርብ ይገባዋል። እነዚህን ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በጽሑፍ ሲመልሱ የማንበብና የመፃፍ ግንዛቤያቸውን ያዳብራሉ። የማያውቋቸው ቃላትና ዕንስ ሃሳቦች ሲያጋጥሟቸው ማስታወሻ ላይ በመፃፍ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግንዛቤ ይፈጥራሉ።

በመጨረሻም መምህራኑ የተማሪዎቹን ሥራ ለመገምገም ዝርዝር መልሶችን የሚሹ ይዘት ተኮር ጥያቄዎችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ከንባብ በፊት፣ በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ የሚቀርቡ ሊሆኑ ይገባል። ሁሉም ክንዋኔዎች ከንባብ ጋር የተቆራኙ የመፃፍ ተግባሮች፣ በመፃፍ ለማንበብ ምላሽ መስጠት የሚያስችሉና ማንበብና መፃፍን በውህደት የሚያለማምዱ ሊሆኑ ይገባቸዋል (Gary 1995)።

በአጠቃላይ በክለሳ ድርሳናቱ የቀረቡት ጥናታዊ ግኝቶች አንብቦ የመረዳትንና የመፃፍን ክሂሎች በውህደት ማስተማር የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ የሚያዳብር እንደሚሆን ገልጸዋል። የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች የማይነጣጠሉ፣ የሚደጋገፉና ትስስር ያላቸው መሆኑንም አመላክተዋል። በመሆኑም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ክሂሎቹን ተከታታይና ተለጣጣቂነት ባለው ምንገድ ማቅረብ ከተቻለ የተማሪዎችን ግንዛቤ እንደሚያሰፋ፣ በራስ መተማመናቸውን እንደሚያጎለብትላቸው፣ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እንደሚያግዛቸውና ስሜታቸውን ለማንጸባረቅ እንደሚረዳቸው ገልጸዋል።

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የተከተለው የአጠናን ስልት በተግባር የተደገፈ ምርምር የሚከሄድበትን የመጠናዊ ምርምር ዘዴን (Quantitative method) ነው:: ለተግባራዊነቱም የተመረጠው የአጠናን ስልት እውን ሙከራዊ (True Experiment) በመከተል ነው:: በዚህ መሠረት የሁለት ቡድን የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና የአጠናን ስልት (The before-after two group design) በሥራ ላይ ውሏል:: የዚህ አጠናን ስልት ጽንሰ ሃሳብ ሁለት ተጠኚ ቡድኖች ምንም ሳይማሩ በሚወስዱት ፈተናና በተለየ ሁኔታ ከተማሩ በኋላ በሚወስዱት ፈተና የሚያሳዩት የችሎታ ልዩነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚያሳይ ነው (Koul 1996)::

ጥናቱ የዘርፉ ተመራማሪዎች ያቀረቧቸውን ትውረቶች መሠረት በማድረግ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና እሙኖችን በፈተና፣ በቪዲዮ በተቀናቀበረ የክፍል ውስጥ ክንውን ምልከታና ቃለ መጠይቅ በማድረግ ተሰብስበዋል::

### 3.1 ተጠኚዎች

ከጥናቱ ዓላማ አንፃር የዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴን (Purposeful or Judgmental Sampling) በመጠቀም የተጠኚዎች አካባቢና ትምህርት ቤቱ ተመርጧል:: በመሆኑም በደቡብ ጎንደር ዞን፣ በወረታ ከተማ አጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተመርጠዋል:: ትምህርታቸውን ለመከታተል የተመዘገቡት 2800 የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በ17 የመማሪያ ክፍሎች ተመድበዋል:: በየክፍሉ ተመድበው የሚማሩት በችሎታቸው ወይም በተለየ መንገድ ተመርጠው አይደለም:: በመሆኑም ምንም ዓይነት የታቀደና የታወቀ ልዩነት ሳይደረግ በየክፍሉ መደልደላቸው ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር በተገኘ መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል:: በጥናቱ የተካተቱትን ሁሉንም የ10ኛ 17 ምድብ ክፍሎች አባ ውስጥ በማስገባት፣ በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ (Simple Random Sampling) ስእያንዳንዱ የጥና

አካባይ አባል ንሞና ሆኖ ለመመረጥ እኩል እድል በመስጠት 10ኛ "E" እና "H" ክፍሎች ለተጠኝነት ተመርጠዋል፡፡

ጥናቱ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ በተግባር በማስተማርና በማለማመድ የሚኖረውን ጠቀሜታ በሙከራ ማረጋገጥ ስለሆነ መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን አላካተተም፡፡ በመሆኑም ለሙከራዊ ጥናቱ የተማሪዎች ቁጥር ለሙከራና ለጥብቅ ቡድን እንዲያመች ተደርጎ ተደልድሏል፡፡ ጥናቱ በእነዚህ ተማሪዎች ላይ የተደረገበት ምክንያት የሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን መጨረሻቸው የክፍል ደረጃ መሆኑ ትግበራውን አስተማማኝ ያደርገዋል ተብሎ ይታሰባል፡፡ እንዲሁም የጥናቱን አስተማማኝነት ለመጠበቅ አመቺ የክፍል ደረጃ መሆኑና የሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ተፈታኞች መሆናቸው ልምምዱን በትጋትና በትኩረት ይሰሩታል ተብሎ በመገመቱ ነው፡፡

በእያንዳንዱ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ከ50 እስከ 56 ተማሪዎች ተመድበውበታል፡፡ ስለዚህ የጥናቱን አስተማማኝነትና ተገቢነት ለማረጋገጥ የተጠኝዎችን ቁጥር መወሰን የግድ ይላል፡፡ በዚህ መሰረት በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ያሉት 52 ተማሪዎች ለተጠኝነት ተመርጠዋል፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ናሙና ሆኖ ለመመረጥ ታማኝነቱን 100 ፐርሰንት እኩል እድል የሚሰጥ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በመቀጠል ሁለቱን ክፍሎች እጣ ውስጥ በማስገባት በተራ ዕጣ ናሙና ዘዴ 10ኛ "H" ክፍል በሙከራ ቡድን 10ኛ "E" ክፍል ደግሞ በጥብቅ ቡድንነት ተመድበዋል፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ ከጥናቱ ተሳታፊዎች ጋር በጥናቱ ለመሳተፍ የይሁንታ ስምምነት ማግኘት ስለሚያስፈልግ የስምምነት መፈራረሚያ ፎርም በማዘጋጀት ተተግብሯል፡፡ (አባሪ 15ን፣ ከገጽ 110-111 ይመለከቷል)፡፡

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

የጥናቱን ዓላማ መሠረት በማድረግ መረጃ እንዲያስገኙ የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ፈተና፣ በቪዲዮ የተቀናቀበረ የክፍል ውስጥ ክንውን ምልከታና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹ አዘገጃጀትና አተገባበር በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

## 3.2.1 ፈተና

በጥናቱ ዓላማ መሠረት በፈተናዎች መረጃዎችን ለማሰባሰብ ታልሞ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተናዎች ዓይነት፣ አዘገጃጀትና አተገባበሩ ቀርቧል።

### 3.2.1.1 ቅድመ ትምህርት ፈተና

የሙከራና የጥብቅ ቡድኖቹ ተማሪዎች የሙከራ ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት የማንበብና የመፃፍ ችሎታቸውን ዳራና የግንዛቤ ደረጃቸው በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ማወቅ ለጥናቱ ጠቃሚ ነው። ስለዚህ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታቸውን የሚለካ ሦስት ክፍሎች ያሉት ቅድመ ትምህርት ፈተና በአጥኚው ተዘጋጅቷል። የፈተናውን ጥራትና ተገቢነት ለማረጋገጥ አማካሪው፣ አንድ በዩኒቨርሲቲ የቋንቋ መምህርና የትምህርት ቤቱ የቋንቋ ትምህርት ክፍል አባላት ገምግመውታል። በሰጡት ማሻሻያ ሃሳብ መሠረት እንደገና ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል። (አባሪ 1ን ከገጽ 54-60 ይመለከቷል)።

በመጀመሪያው የፈተና ክፍል ከከበደ ሚካኤል (1999) "ታማኝነት ከሁሉ ይበልጣል" በሚል ርዕስ የቀረበውን ተረት የአንቀጹን ዓረፍተ ነገሮች በማዘበራረቅ የተወሰደ ነው። ለእያንዳንዳቸው ቁጥር ተሰጥቷቸው ትደም ተከተላቸው የተዘበራረቁ አሥር ዓረፍተ ነገሮች ቁልቁል በረድፍ ተጽፈው ቀርበዋል። ተማሪዎቹ እነዚህን ቅደም ተከተላቸው የተፋለሱ ዓረፍተ ነገሮች አንብበው እንደገና እንዲያደራጁ ይፈለጋል። በትክክለኛው የሃሳብ ቅደም ተከተል አስተካክለው እንተጹ'ን እንዲጽፋም ይጠበቃል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ምላሽ ሁለት ነጥብ እንዲይዝ ተደርጎ በድምሩ ሃያ ነጥብ ይዟል።

በሁለተኛው የፈተና ክፍል ከሃዲስ ዓለማየሁ (1960) መፃሐፍ ተደርጎበት የተወሰደን የልበለድ ትንጫቤ መሠረት ተደርጎ ተዘጋጅቷል። ተማሪዎች የምንባቡን መልዕክት መገንዘባቸውን ለመለካት በምንባቡ ውስጥ ሊመለሱ የሚችሉ የሂደት ጥያቄዎችን በማካተት ሦስት ንኡሳን ክፍሎችን እንዲይዝ ተደርጓል። በመጀመሪያው ንኡስ ክፍል ለቀረቡት ጥያቄዎች ምንባቡን ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት ለመልሳቸው ምክንያት በመስጠት አያብራሩ እንዲጽፉ የሚያደርጉ ናቸው። ከተ.. መ ለምያና ለሙቀት በሥነሳት ለሚጽፉት ለአንዱ ጥያቄ አራት ነጥብ በመስጠት በድምሩ ስምንት ነጥብ

ይዟል። በሁለተኛው ንኡስ ክፍል ምንባቡን እያነበቡ ቀጣዩን ታሪክ ከቀደመ ዕውቀትና ከታሪኩ ሂደት ተነስተው በመገመት በጽሑፍ የሚመልሷቸው የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ አንብቦ በዕብረቃ ተገቢ ምላሽ መስጠት አራት ነጥብ በመስጠት በድምሩ አርባ አራት ነጥብ እንዲይዝ ተደርጓል። በሦስተኛው ንኡስ ክፍል ከምንባቡ በኋላ የወጡትን ጥያቄዎች ሲመልሱ ከጽሑፉ በሰፈረ ሃሳብ፣ ከቀደመ ልምድና ዕውቀት በመነሳት የሚመልሷቸው ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ መስጠት አራት ነጥብ በመስጠት በድምሩ ስምንት ነጥብ ይዟል።

በሦስተኛው የፈተና ክፍል ከትምህርት ቤቱ የወላጅ መምህር ህብረት ኮሚቴ የተገኘ የክስ መግለጫ (2003) እንዳለ ተወስዷል። መረጃውን ምን ያህል እንደተጠቀሙበትና በዕብረቃ ሃሳባቸውን አደራጅተው የመፃፍ ብቃታቸውን ለመለካት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ለዚህም ተማሪዎቹ የቀረበውን የክስ መግለጫ ካነበቡ በኋላ ራሳቸውን እንደ ተከሳሱ በመቁጠር፣ ነገር ግን ተፈጸመ የተባለውን ጥፋት ያልፈጸሙት መሆናቸውን በመግለጽ ለወላጅ መምህር ህብረት ኮሚቴው መልስ እንዲጽፉ ይጠበቃል። አንብበው የሚሰጡት ግብረ መልስ ሃያ ነጥብ እንዲይዝ ተደርጓል።

### 3.2.1.2 ድህረ ትምህርት ፈተና

ከድህረ ትምህርት ፈተናው ተገቢውን መረጃ መሰብሰብ እንዲቻልና የፈተናውን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ሲባል ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ ተመሳሳይ ይዘት እንዲኖራቸው ተደርጓል። በመሆኑም ፈተናዎቹ በጥያቄ ቁጥር ብዛት፣ በአቀራረብ፣ በይዘትና በአወቃቀራቸው ተመሳሳይ እንዲሆኑ ተደርጓል። ቡድኖቹ በተለያየ ሁኔታ በየግላቸው የተዘጋጀላቸውን ትምህርት በአጥኚው ለአንድ ወር ተምረዋል። ቡድኖቹ ከትምህርቱ በኋላ በትምህርቱ አቀራረብ ልዩነት ምክንያት የችሎታ ልዩነታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ማወቅ ያስፈልጋል። በመሆኑም ለሙከራና ለጥብቅ ቡድኖቹ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታቸውን የሚለካ ድህረ ትምህርት የጽሑፍ ፈተና በአጥኚው ተዘጋጅቷል። ፈተናውን አማካሪው፣ አንድ በዩኒቨርሲቲ የቋንቋ መምህርና የትምህርት ቤቱ የቋንቋ ትምህርት ክፍል ገምጋሚው በሰጡት አስተያየት መሰረት ተሻሽሎና ተጨምቆ ተዘጋጅቷል። በመሆኑም ፈተናው

ሦስት ክፍሎች እንዲኖሩት ተደርጎ ተዘጋጅቷል። (አባሪ 2ን ከገጽ 61-65 ይመለከቷል)

በመጀመሪያው የፈተና ክፍል ማረው ዓለሙ (1998) ያቀረበውን አጭር ምንባብ ተሻሽሎ ተወስዷል። ዕንሰ ሃሳቡን ተረድተው ትርጉም በመገንባት መፃፋቸውን ለመለካት ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ስለዚህ ምንባቡን አንብበው ለችግሩ መፍትሄ ይሆናል የሚሉትን ሃሳብ ምክንያታቸውን በመግለጽ አብራርተው እንዲጽፉ ይጠበቃል። ሃሳባቸውን አደራጅተው በጽሁፍ የሰጡት ምላሽ አሥራ አንድ ነጥብ ይዟል።

በሁለተኛው ፈተና ክፍል ማረው ዓለሙ (ያልታተመና ዓ.ም የሌለው) ያቀረበውን መሻሻል ተደርጎበት ተወስዷል። ተማሪዎች የሂደት ጥያቄዎችን እንዲሰሩና የዕንሰ ሃሳብ ትርጉም መገንባታቸውን፣ በመገመትና በመተንበይ መፃፋቸውን ለመለካት ታልሞ የተዘጋጀ ነው። በምንባቡ ውስጥ ሊመለሱ የሚችሉ የሂደት ጥያቄዎችን በማካተት ሦስት ንኡሳን የፈተና ክፍሎችን ይዟል። በመጀመሪያው የፈተና ክፍል የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት ለመልሳቸው ማስረጃ በመስጠት አብራርተው እንዲጽፉ ይፈለጋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ መስጠት አምስት ነጥብ በመስጠት በድምሩ አሥር ነጥብ ይዟል። በሁለተኛው ንኡስ ክፍል ምንባቡን እያነበቡ ቀጣዩን ታሪክ ከቀደመ ልምድ፣ ዕውቀትና ከታሪኩ ሂደት ተነስተው በመገመት በጽሑፍ የሚመልሷቸው የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ናቸው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ መስጠት አራት ነጥብ በመስጠት በድምሩ አርባ አራት ነጥብ ይዟል። ሦስተኛው ንኡስ ክፍል ድህረ ንባብ ጥያቄዎች ናቸው። ጥያቄዎችን ሲመልሱ ከጽሑፉ በቀጥታ የሰፈረን ሃሳብ መሠረት በማድረግ፣ ከቀደመ ልምድና ዕውቀት በመነሳት ምላሽ እንዲሰጡ ይጠበቃል። ከተገነዘቡትና የቀደመ ዕውቀታቸውን በመገልገል ሊከሰት የሚችልን ሁኔታ በማንጸባረቅ ለፃፉ ተማሪዎች ለ14ኛው ጥያቄ አምስት ነጥብ ለ15ኛው ጥያቄ አሥር ነጥብ እንዲይዝ ተደርጎ፣ በድምሩ አሥራ አምስት ነጥብ ይዟል።

ሦስተኛው ፈተና ክፍል ደግሞ ከደበበ ኃይለጊዮርጊስ (1998) ተሻሽሎ የተወሰደ ነው። የተጀመረን ሃሳብ ለመጨረስ በርካታ መንገዶችን ተጠቅመው የቀረቡትን አሥር ጅምር ዓረፍተ ነገሮች አስፈላጊዎችን ቃላትና ሀረጋት በመገልገል በራሳቸው አባባል እንዲጨርሱ ይፈለጋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ምላሽ ሁለት ነጥብ በመ(ስ)ጠት ከመቶው ሃያ ነጥብ ይዟል።

ድህረ ትምህርት ፈተናው ለሙከራና ለጥብቅ ቡድኖቹ በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜ በአጥኚውና በሁለት የትምህርት ቤቱ ረዳት ፈታኝ መምህራን ህዳር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቷል። የፈተናውን ውጤት አስተማማኝነት ለመጠበቅ ሲባል በአንድ ጠረጴዛ ሁለት ተማሪዎች እንዲቀመጡ ተደርጓል። በዚህ መንገድ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታቸውን፣ የቋንቋ አጠቃቀማቸውን፣ የቃላትን ትርጉም ከአውዳቸው መረዳት መቻላቸውን፣ የዓረፍተ ነገር አወቃቀራቸውን፣ የአንድን ፅንሰ ሀሳብ ትርጉም መገንዘባቸውን፣ የጥያቄውን ምላሽ በተገቢው መንገድ መግለፃቸውንና በጥያቄው ውስጥ ያለውን መረጃ በውል መረዳታቸውን በሰጧቸው ምላሾችና ስብረቃዎች እየታዩ ታርመዋል።

የሁለቱም ክፍሎች የቅድምና ድህረ ትምህርት ፈተና ወረቀቶች በወቅቱ በፈታኞች ተሰብስበዋል። የውጤት አሰጣጡን አስተማማኝነትና ትክክለኛነት ለመጠበቅ ሲባል በትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል አባላት በተመረጡ ሁለት መምህራንና በአጥኚው እንዲታረም ተደርጓል። የአስተራረም ሂደቱም ከፈተና ወረቀቱ ላይ የተማሪዎች ስም ሳይፃፍ መለያ ኮድ ተሰጥቶታል። በዚህም መሠረት የአንድ ተማሪ የመልስ ወረቀት በሶስት ኮፒ ተራብቶ ለሶስቱም አራሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል። ሶስቱ አራሚዎች ለአንድ ተማሪ የሰጡት ውጤት ተደምሮና ለሶስት ተካፍሎ የተገኘው አማካይ ነጥብ የተማሪው ውጤት ተደርጎ ተመዝግቧል።

## 3.2.2 ቃለ መጠይቅ

ለሙከራዊ ጥናቱ መረጃ ማስገኘት የተመረጠው ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ቃለ መጠይቅ ነው። ከቃለ መጠይቁ የሚገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ለመጠበቅ ሲባል ከሙከራ ቡድኑ 52 ተማሪዎች መካከል ስድስት ተማሪዎች በቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት መሠረት ተመርጠዋል። በመሆኑም ከፍተኛ ውጤት ካስመዘገቡት ሁለት፣ መካከለኛ ውጤት ካስመዘገቡት ሁለትና ዝቅተኛ ውጤት ካስመዘገቡት ሁለት፣ በድምሩ ስድስት ተማሪዎች ተመርጠዋል። በአጥኚው አማካኝነት ቅድመ ትምህርት ቃለ መጠይቁ ጥቅምት 8 ቀን 2003 ዓ.ም፤ ድህረ ትምህርት ቃለ መጠይቁ ደግሞ ህዳር 4 ቀን 2003 ዓ.ም ተደርጓል። (አባሪ፤ 3፣ 4፣ 5 እና 6ን፣ ከገጽ 66 -73 ይመለከቷል)።

ቅድመ ትምህርት ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ምክንያት ከሙከራ ትምህርቱ በፊት
አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በሚመለከት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ታስቦ
ነው። በአጠቃላይ የቅድመና የድህረ ትምህርቱ ቃለ መጠይቆች ጥያቄዎች በመስኩ
የተካሄዱ የምርምር ጥያቄዎችን መነሻ በማድረግ በአጥኚው ተዘጋጅቷል። የተጠ
ያቂዎችን ምላሽ ይዞ ለመተንተን እንዲቻል በቪዲዮ እየተቀረጸ የሁለቱም ጊዜ ቃለ
መጠይቅ ተከናውኗል። መረጃውን ከሲዲው በማየትና በማዳመጥ የተገኘው መረጃ
ተተንትኗል።

### 3.2.3 የትምህርት ዕቅድ

ጥናቱን በተገቢው መንገድና ጊዜ ለመከወን እንዲቻል፣ የትግበራውን ሂደት በጥራትና
ሚዛኑን በጠበቀ አኳኋን እንዲጓዝ ለማድረግ ለሙከራና ለጥብቅ ቡድኖቹ ዕለታዊ
የትምህርት ዕቅድ በአጥኚው ተዘጋጅቷል። ዕቅዱን አማካሪው ገምግሞ በሰጠው
አስተያየት መሠረት ለደረጃውና ለጥናቱ እንዲመጥን ተደርጎ ልዩ ልዩ ተግባራት
ተካተውበት ለሙከራ ቡድኑ ተዘጋጅቶ ተተግብሯል። እንዲሁም ለጥብቅ ቡድኑ የትምህ
ርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሚያዘጋጁበት ፎርም መሠረት ዕለታዊ የትምህ
ርት ዕቅድ እየተዘጋጀ ተተግብሯል። (አባሪ፤ 7 እና 8ን ገጽ 74-84 ይመለከቷል)።

ለሙከራ ቡድኑ የትምህርቱ አሰጣጥና ትግበራው አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን
ለማዳበር የሚያገለግሉ ብልሃቶችን፤ በጥልቀት ማሰብ፣ ማብራራትና መተርጎም፤
ማንበባረቅና ጻራዊ ዕውቀትን መጠቀም፣ ማጠቃለል፣ ማሳጠር፣ መገመትና ምስላን
ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅተዋል። በዕለታዊ ትምህርት ዕቅዱ
መሠረት ተግሪዎች የተዘጋጁትን መልመጃዎችና ክንዋኔዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን
በየክፍለ ጊዜው እንዲያከናውኑ ተደርጓል።

### 3.2.4 የመማሪያ/ማስተማሪያ አዘገጃጀት፣ የትምህርቱ አሰጣጥና የትግበራው ሂደት

የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ለማስተማር አጥኚው ለጥናቱ ይመጥናሉ ያላቸውን የተለያዩ ልቦለዶችን፣ ግጥሞችን፣ ተረቶችንና ስነቃሎችን በመምረጥ አደራጅቶ አዘጋጅቷል:: የመማሪያውን ተገቢነትና ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር መገናዘቡን ለማረጋገጥ አማካሪው፣ አንድ በዩኒቨርሲቲ የቋንቋ መምህርና የትምህርት ቤቱ የቋንቋ ትምህርት ክፍል በጋራ ገምግመውታል:: በሰጡት አስተያየትና ማሻሻያ ሃሳብ መሠረት የክፍል ደረጃቸውን፣ የቀደመ ዕውቀታቸውን፣ ቁጥራቸውን፣ ዝንባሌያቸውን፣ ባህላዊ ዳራቸውንና የመሳሰሉትን ግምት ውስጥ በማስገባት እንደገና ተሻሽሏል:: በመሆኑም በስምንት የትምህርት ክፍልና ርዕሶች ተደራጅቶና ተስተካክሎ ልዩ ልዩ ተግባራት ተካተውበት ተዘጋጅቷል:: (አባሪ 9ን ከገጽ 86-103 ይመለከቷል)::

ለሙከራ ትምህርቱ የተዘጋጀው መማሪያ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በማዋሃድ የሚያለማምዱ መልመጃዎችና ከንዋኔዎች እንዲካተቱበት ተደርጓል:: የተመረጡት የመማሪያ ርዕሶችም ያልተንዛዙ፣ ተግባቦትን የሚያጠናክሩ፣ ወቅታዊ የሆኑ፣ ጥንታዊ ቢሆኑም በወቅቱ ተደማጭነት ያላቸው፣ የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያነሳሱና ከዳራዊ ዕውቀታቸው ጋር የተገናዘቡ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል::

ትምህርት አንድ፦ ከአበራ ለማ (1980) "የአፍ ነገር" በሚል ርዕስ የቀረበውን ተውኔት ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ ነው:: የተውኔት ቅንጫቢውን ከማንበባቸው በፊት ቀደም ሲል ከተማሩት የተውኔት ቅንጫቢ ውስጥ የሚገኙ ገፀ-ባህሪያት የሥራ ክንዋኔ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ከሚያደርጉት ጭውውት ጋር አንድነትና ልዩነቱን ጥንድ በመሆን ከተወያዩበት በኋላ በተናጠል አብራርተው እንዲጽፉ ይጠበቃል:: በርካታ ሰዎች መልዕክታቸው ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ፈሊጦችንና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በጽሑፋቸውና በንግግራቸው መካከል ጣልቃ እያስገቡ የሚጠቀሙት ለምን እንደሆነ ከቀደመ ልምዳቸውና ዕውቀታቸው በመነሳት ጥንድ በመሆን ከተወያዩበት በኋላ በተናጠል በጽሑፍ እንዲያንጸባርቁ ይፈለጋል:: ተውኔቱን ካነበቡ በኋላ ለቀረቡት አምስት ፈሊጦች የያዟቸውን መልዕክቶች የሚወክሉ ዓረፍተ ነገሮችን በመመስረት ፍቺዎቻቸውን በተናጠል ይሰጣሉ:: በመቀጠል አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ከተወያዩበት በኋላ ከውይይቱ ያገኙት ማሻሻያ

ሃሳብ መሠረት መልሱን እንደገና በግላቸው አስተካክለው ይጽፋሉ። በፈሲጦችና ምሳሌያዊ አነጋገሮች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት መረጃ በማፈላለግ አብራርተው ጽፈው እንዲመጡ የቤት ሥራ መስጠትና ሌሎችም ተግባራት ተካተውበታል።

*ትምህርት ሁለት፦* ከበድሉ ዋቅጅራ (1996) "እውነትና ንጋት እያደር ይገለጣል" በሚል ርዕስ የቀረበውን ተረት ማሻሻያ ተደርጎበት ተወስዷል። ከቀደመ ልምድ፣ ዕውቀትና ካነበቡት ከታሪኩ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለተካተቱት ጥያቄዎች መልሳቸውን በተናጠል ይጽፋሉ። የገፉትን መልስ በመቀያየር እየገመገሙ አስተያየታ ቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ። ተረት በተናጠል ባለቤት የማይነቀስለት በምን ምክንያት እንደሆነ ጥንድ በመሆን ከተወያዩበት በኋላ ምላሹን በግል በማንጸባረቅ እንዲጽፉ ይጠ በቃል። በመጨረሻም የቀረበውን ተረት አብይ ጭብጥ በራሳቸው አገላለጽ በአጭሩ እንዲጽፉ የሚያደርጉና በቡድን እየተወያዩ መፃፍ የሚያስችሉ ተግባራትም ተካተው ቀርበዋል።

*ትምህርት ሦስት፦* ከሃዲስ ዓለማየሁ (1960) ልቦለድ ተቀንጭቦና ተሻሽሎ ተወስዷል። ቅንጫቢውን ከማንበባቸው በፊት ቀደም ሲል ያነበቡትን የልቦለድ ስራ ለማስተዋወቅ የሚረዳ የማስታወቂያ ጽሑፍ በግል እንዲያዘጋጁ ይጠበቃል። (የሚያዘጋጁት ጽሑፍ ስራውን ላላነበበ ሰው የሚያስተዋውቅ፣ የስራውን ዋና ዋና ጭብጦች መጥና የሚያሳይ ሊሆን ይገባል)። ቅንጫቢ ጽሑፉን ካነበቡ በኋላ ደግሞ በአካባቢያቸው ያለው ሊጋብቻ የመተጫጨት ስርዓት ከእድሜ፣ ከሀብትና ከዘር ሐረግ ጋር ተያይዞ ምን እንደሚመስል ጥንድ በመሆን ከተወያዩበት በኋላ ምላሹን ይጽፋሉ። በመቀጠል ሦስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ከተወየወዩበት በኋላ ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ ሃሳብ መሠረት መልሱን እንደገና በግላቸው አስተካክለው ይጽፋሉ። ወላጆች ልጆቻቸውን በስርዓት አሳድገው ለቁምነገር ለማብቃት ሊከተሏቸው ይገባል የሚሉትን መመሪያ በግል ዘርዝረው እንዲጽፉ ይጠበቃል። በመቀጠል ከጎናቸው ካሉት ጋር በመሆን አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ከተወየወዩበት በኋላ ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ ሃሳብ መሠረት መልሱን እንደገና በግላቸው አስተካክለው ይጽፋሉ።

*ትምህርት አራት፡-* ከደበበ ኃይለጊዮርጊስ (1998) "ለሁሉም ጊዜ አለው" በሚል ርዕስ የቀረበው ግጥም ማሻሻያ ተደርጎበት ቀርቧል:: ግጥሙን ከማንበባቸው በፊት ሀሳብንና ስሜትን አጉልቶ ለማስተላለፍ ከግጥምና ከስድ ጽሑፍ የትኛው ተመራጭ እንደሆነ በግል አብራርተው ይጽፋሉ:: በመቀጠል ከጎናቸው ካለ/ች ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ:: ግጥሙን ካነበቡ በኋላ የተሰማቸውን ስሜት መግለጽ የሚችል አንድ ከአስር ስንኝ ያልበለጠ አጭር ግጥም በግላቸው ከፃፉ በኋላ ጽሑፉን በፊታቸው ከተቀመጠ/ች ተማሪ ጋር ተቀያይረው በማንበብ አስተያየታቸውን ጽፈው ለክፍሉ ተማሪዎች እያነበቡ ያሰማሉ:: በመቀጠል ግጥሙን ሲያነቡ የተረዱትን ቁም ነገር በአጭሩ ጥንድ በመሆን ከተወያዩበት በኋላ ምላሹን በተናጠል በጽሑፍ ይሰጣሉ:: በመጨረሻ የቀረበውን አጭር ግጥም አንብበው መልዕክቱ ሳይዛባ ወደ ስድ (ዝርው) ጽሑፍ ለውጠው በግላቸው እንዲጽፉ የሚያደርጉና ሌሎችም ተግባራት አካተውበት ተዘጋጅቷል::

*ትምህርት አምስት፡-* ከሺበሽ ለማ (1958) "ተጠየቅ" በሚል ርዕስ የቀረበውን የተውኔት ጽሑፍ ተሻሽሎ ተወስዷል:: እስጥ አገባ ጥንታዊ የክርክር ተውኔት ጽሑፉን ከማንበባቸው በፊት በአካባቢያቸው የሚከናወነውን የሽምግልና ስርዓት አስፈላጊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጥንድ በመሆን እየተወያዩበት በኋላ ምላሹን በግል እንዲጽፉ ይጠበቃል:: በመቀጠል ሦስት አባላት ያሉት በቡድን በመመስረት የፃፉትን እያነበቡ ከተወያዩበት በኋላ ዳራዊ እውቀታቸውን በመጠቀም በተናጠል ይጽፋሉ:: የቀድሞው የዳኝነት ስርዓት ከዘመናዊው ጋር ጎን ለጎን ቢሰራበት በፍትህ አሰጣጥ ስርዓቱ ላይ ሊከተል ይችላል ብለው የገመቱትንና ፍትሃዊ ውሳኔ የሚሰጠው የትኛው እንደሆነ ጥንድ በመሆን ከተወያዩበት በኋላ መልሳቸውን በተናጠል በጽሑፍ ይሰጣሉ:: ከጎናቸው ካሉት ጋር አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ከተወየወዩበት በኋላ ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ ሃሳብ መሠረት መልሱን እንደገና በግላቸው ይጽፋሉ:: በአጠቃላይ ለቅድመ ምንባብ፣ ለምንባብ ጊዜና ለድህረ ንባብ ተግባራት በጽሑፍ ምላሽ እንዲጡ ይጠበቃል::

*ትምህርት ስድስት፡-* ከዓለም እሸቱ (1998) "የዘገባ አዘገጃጀት መመሪያ" ተቀንጭቦ የተወሰደ ነው:: የዘገባ ዝግጅትና አዘገጃጀት መመሪያውን ያነባሉ:: በመመሪያው መሠረት እራሳቸውን የትምህርት ቤቱ ርዕስ መምህር እንደሆኑ በመቁጠር፣ የትምህርት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ በዘገባ መልክ በማጠቃለል በአጭሩ

በግል ይጽፋሉ። በመቀጠል ከጎናቸው ካሉ ጥንዶች ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በጽሑፍ የሚሰጡበትና ሌሎችም ተግባራት ተካተውበት ተዘጋጅቷል።

*ትምህርት ሰባት፦* ከደበበ ኃይለጊዮርጊስ (1998) "በሌላ አባባል መግለጽ" በሚል የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ማሻሻያ ተደርጎባቸው ተወስደዋል። በዓረፍተ ነገር የቀረበን ሃሳብ በሌላ አባባል የመግለጽ መመሪያውን በግላቸው ያነባሉ። የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች የያዟቸው ሃሳቦች ሳይዛቡ በልዩ ለዩ አባባሎች ተክተው ይጽፋሉ። እንዲሁም የተወጠነውን ሃሳብ መንፈሱን በመረዳት ፍፃሜው በዚህ መንገድ ሳይሆን አይቀርም ብሎ በመገመት ውጥን ጨራሽ ሃሳብን በተገለጸበት መንገድ በመጨመር ዓረፍተ ነገሮቹን አስተካክለው በግላቸው ይጽፋሉ። በመቀጠል ከጎናቸው ካሉት ጋር በመሆን አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ከተወያወዩበት በኋላ ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ ሃሳብ መሠረት መልሱን እንደገና አስተካክለው በተናጠል እንዲጽፉ የሚያደርጉና ሌሎችም ተግባራት ተካተውበታል።

*ትምህርት ስምንት፦* ከአላምረው ገብረማሪያም (2002) "አጽህሮተ ጽሑፍ" በሚል ከቀረበው መመሪያ ጽሑፍ ተወስዷል። የአህጽሮተ ጽሑፍ ወይም ጽሑፍን የማሳጠር መመሪያውን በግላቸው በማንበብ የቀረበላቸውን ቅንጫቢ ጽሑፍ ጥንድ በመሆን ከተወያዩበት በኋላ በሦስት እጅ አሳጥረው በግላቸው ይጽፋሉ። እንዲሁም የቀረበውን ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ ካነበቡ በኋላ ራሳቸውን በሂሳብ ሥራ ዲፕሎማ እንዳላቸው በመቁጠር በመስፈርቱ መሠረት ማስታወቂያውን ላወጣው መስሪያ ቤት መቀጠር የሚፈልጉ መሆናቸውን በመግለጽ በግላቸው ማመልከቻ ይጽፋሉ። ከኋላቸው ካለ/ች ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በጽሑፍ እንዲሰጣጡ የሚያደርጉና ሌሎችንም ተግባራት አካቶ ይዟል።

በአጠቃላይ ከምንባቦቹ በመጀመሪያ፣በመካከልና በመጨረሻ ላይ የተካተቱት ጥያቄዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ለማስተማር የሚረዱና ተማሪዎችን እንዲተነብዩ፣ እንዲያብራሩ፣ ምስል ከሳች ቃላትን ለይተው እንዲያወጡ፣ እንዲጠይቁና ማጠቃለል እንዲችሉ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጁ ናቸው። በዚህ መንገድ የተዘጋጀው መማሪያ ለሁሉም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች እንዲዳረስ ሆኖ ተራብቶ በየክፍለ ጊዜው እየታደለ ትምህርቱ ተሰጥቷል።

ጥብቅ ቡድኑ ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው መጽሐፍ፣ በተለመደው የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ፣ በመደበኛው ክፍለ ጊዜና ከደረሱበት ርዕስ በመቀጠል ክሂሎቹን በተናጠል በአጥኚው እንዲማሩ ተደርጓል። የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎችም የትምህርቱን ጊዜ ከመደበኛ ፈረቃቸው ውጭ እንዲሆን በተስማሙት መሠረት በሳምንት ሁለት ቀን (በቀን 1:30) ለአንድ ወር በአጥኚው በተዘጋጀው መማሪያ እንዲማሩ ተደርጓል።

## 3.2.5 በክፍል ውስጥ ክንውን የተደረገ የቪዲዮ ምልከታ

በጥናቱ ዓላማ መሠረት ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ምልከታ ነው። የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የዕለት ከዕለት የመማር ማስተማር እንቅስቃሴ፣ የእርስ በእርስ ተራክቦና ከመምህሩ ጋር የነበራቸው ግንኙነት በየእለቱ በቪዲዮ እየተቀረጸ በሲዲ መረጃው ተመዝግቦና ተደራጅቶ ተይዟል። የተደገኘውም መረጃ በአግባቡ ተተንትኗል። ተማሪዎች በልምምዱ ወቅት ምን እንዳጋጠማቸው፣ ክንውኑን እንዴት ይተገብሩት እንደነበርና የተገኘውም ለውጥ ምን ያህል እንደሆነ ተቃኝቷል። (አባሪ 10ን ከገጽ 104-105፤ እንዲሁም የፎቶ ግራፍ መረጃዎችን (አባሪ 16 ከገጽ 112 ይመለከቷል)።

## 3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በፈተናው ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ የመልሱ ዝርዝር ነጥቦች ለአራሚዎች ቀድመው ተሰጥተዋል። የቅድመ ትምህርቱም ሆነ የድህረ ትምህርቱ የጽሑፍ ፈተናዎች በቋንቋ ትምህርት ክፍል በተመረጡ ሁለት መምህራንና በአጥኚው ታርመዋል። በአስተራረሙ መሠረት ለቅድመና ለድህረ ፈተናዎች ለእያንዳንዱ ንኡስ ጥያቄ ተገቢው ነጥብ ተሰጥቷል። በተማሪዎች መለያ ቁጥር መሠረት ዝርዝር ውጤቱን በመደመር ከ100 ያገኙት ተመዝግቧል። (አባሪ፤ 11፣ 12፣ 13 እና 14ን ከገጽ 106-109 ይመለከቷል)።

በሦስቱ አራሚዎች መካከል ያለው የአራሚ ዘለል አስተማማኝነት (Inter-Rater Reliability) ወይም የጳኝነት ስምምነት ደረጃ በክሮንባኽ አልፋ ወይም ክረቬንት አልፋ

(Cronbach's Alpha or Coefficient alpha) ቀመር መሠረት ተሰልቷል:: የተጠኝዎችን ፈተና ከሁለት በላይ በሆኑ አራሚዎች በመካፈል የአንድን ነፃ ተለዋዋጭ የተለያዩ እርከኖች በቡድኖቹ ባህሪያት ላይ የፈጠሩት ልዩነት እንዳለና እንደሌለ ለማረጋገጥ ነፃ ናሙና ልይይት ትንተና ዘዴ (One Way ANOVA) በመጠቀም ተሰልቷል:: በስሌቱ መሠረት የሙከራ ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት በጠቃላይ የሦስቱ አራሚዎች የውጤት አስተማማኝነት 0.889 በመሆኑ የጸኝነት ግምገማው የመጣጣም ደረጃ ተገኝቷል:: በድህረ ፈተናው ደግሞ በጠቃላይ የሦስቱ አራሚዎች የውጤት አስተማማኝነት 0.805 በመሆኑ የጸኝነት ግምገማው የስምምነት ደረጃ ተገኝቷል::

በአጠቃላይ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ ውጤት አሰጣጥ በሦስቱ አራሚዎች መካከል 0.924 የውጤት አስተማማኝነት ተገኝቷል:: ስለዚህ የአስተማማኝነት ውጤቱ ወደ አንድ ሲጠጋ የአራሚዎች ስምምነት መኖሩን ያመላክታል (ያለው 1998):: በዚህ መሠረት በአራሚዎች መካከል በጣም ከፍተኛ የሆነ ስምምነት መኖሩን ስለሚያመለክት መረጃው እንዳለ ተወስዷል:: የፈተናው መረጃዎች በዚህ መልክ ከተሰበሰቡና እንደየተዛምዷቸው ከተደራጁ በኋላ በ"ዲስክሪፕቲቭ" የስታትስቲክስ ስሌት ተተንትነዋል::

በመጀመሪያ የጥብቅ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናው ውጤቶች ልዩነቱን ለማወቅ በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በ"ቲ" ቴስት ተሰልቷል:: በተመሳሳይ ሁኔታ ለሙከራ ቡድኑ የተሰጠውን የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቶች የተገኘውን ለውጥ ለማወቅ በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በ"ቲ" ቴስት ተሰልቷል:: የሙከራና የጥብቅ ቡድኖቹ ከሙከራው ትምህርት በፊት ክሂሎቹን በመገልገል ረገድ የግንዛቤ ደረጃቸው ምን ያህል ልዩነት እንዳለው ማወቅ ያስፈልጋል:: ስለዚህ የሁለቱን ቡድኖች የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤቶች በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በ"ቲ" ቴስት ተሰልቶና ተነፃፅሮ ተተንትኗል:: በመጨረሻ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የታየው የችሎታ ልዩነት በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝና በቡድኖቹ መካከል ያለውን ልዩነት መለካት ያስፈልጋል:: ስለዚህ የድህረ ትምህርት ፈተናውን ውጤቶች በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በ"ቲ" ቴስት ተሰልቶና ተነፃፅሮ ተተንትኗል:: ይህን የስታትስቲክስ በመንተኛ ዘዴ መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት በሙከራና በጥብቅ ቡድን የተካተቱት ተማሪዎች ከ30 በላይ በመሆናቸው ነው::

የሙከራ ቡድኑ አባላት የቃለ መጠይቁ ምላሾች፣ በትምህርቱ አሰጣጥ ሂደቱ ወቅት ከመምህሩ ጋር በነበራቸው ተራክቦና በክፍል ውስጥ ምልከታው የሚገኙት እሙን መረጃዎች እንዳይዛቡ በየጊዜው በቪዲዮ እየተቀረጹ ተሰብስበዋል:: ከመጠናዊ መረጃው ጋር እየተገናዘቡ ተብራርተው ቀርበዋል:: በአጠቃላይ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንዲቻል የመረጃዎችን ሦስት ማዕዘናዊነት (data-triangulation) በተከተለ መንገድ በተለያዩ መሣሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ተጠናቅረውና ተተንትነው ተገልጸዋል::

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች ትንተናና የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የጥናቱን ዓላማዎች ለማሳካት በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከጥናቱ ባህሪይ ጋር በሚሄዱ የመተንተኛ ስልቶችም ተተንትነዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ የመረጃዎች ትንተናና የጥናቱ ውጤት፣ የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 4.1 የመረጃዎች ትንተናና የጥናቱ ውጤት

የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና በሙከራዊ ጥናት ማረጋገጥ የጥናቱ አቢይ ዓላማ ነበር፡፡ በመሆኑም ዓላማውን በተግባር ለመፈተሽ በፈተና፣ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበው የተገኙት የመረጃዎች ውጤቶች ተተንትነዋል፡፡

የሙከራና የጥብቅ ቡድኖቹ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት ምንም ሳይማሩ በወስጹት ፈተናና በተለያየ የአቀራረብ ዘዴ ለአንድ ወር ከተማሩ በኋላ በወሰዱት ፈተና መካከል ያሳዩትን የችሎታ መለያየት ወይም መመሳሰል በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መለየት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ በመደበኛው ክፍለ ጊዜ፣ ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍና በተለመደው የማስተማር ዘዴ ሲማር የቆየው የጥብቅ ቡድኑ ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት ይልቅ በድህረ ትምህርት ፈተናው የተሻለ ውጤት ያስመዘገበ ወይም ያላስመዘገበ መሆኑ በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ አንድ ቀርቧል፡፡ የዚህን ዝርዝር መረጃ (አባሪ 11 እና 12ን ከገጽ 106-107 ይመለከቷል)፡፡

| የጥብቅ ቡድኑ ፈተና | $\bar{X}$ | sd | df | $t_{ob}$ | $t_{cr}$ | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት | 34.75 | 19.79 | | | | |
| ድህረ ትምህርት | 36.23 | 20.11 | 51 | -1.306* | 0.197 | የለውም |

የጉልህነት ደረጃ (የስህተት ይሆንታ መጠን) (Level of significance) $^*P<0.05$

ሰንጠረዥ 1፡- የጥብቅ ቡድኑ የቅድመና የድህረ ትምህርት የፈተና ውጤቶች ንጽጽር በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶ ሲታይ፡-

የጥብቅ ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (36.23) ከቅድመ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት (34.75) ጋር ሲነጻጸር ብልጫ ያለው ይመስላል፡፡ የሁለቱ ፈተናዎች የአማካይ መደበኛ ልይይት (Standard deviation) ማለትም የእያንዳንዱ ተማሪ ከአማካይ ውጤት ወደላይ ወይም ወደታች በአማካይ መራቁ ሲታይ በቅድመ ትምህርቱ ፈተናው (19.79) በድህረ ትምህርቱ ፈተናው ደግሞ (20.11) ነው፡፡ ስለዚህ የአማካይ መደበኛ ልይይቱ ከፍተኛ በመሆኑ፣ የበርካታ ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከአጠቃላዩ አማካይ ውጤት የራቀ ውጤት ተመዝግቧል፡፡

የአማካይ ውጤቶችን ልዩነት አስተማማኝነት ለማወቅ በልዩነት ማረጋገጫ ቀመር (ቲ-ቴስት) ተሰልቷል፡፡ በስታትስቲካዊ ስሌቱ መሠረት ለምናልባት ስህተት 5% ($p<0.05$) በመተው ወይም 95% እርግጠኛ በመሆን በተሰላው ስሌት የቲ-ቴስት ዋጋ ($t_{obtained}$) |-1.306| ነው፡፡ የነፃነት ደረጃው 51፣ የጉልህነት ደረጃው ደግሞ (0.05) ሆኖ፡ መላምቶቹን በመቀበል ወይም ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ወይም መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የተነበበው የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ($t_{critical}$) (0.197) ነው፡፡ ስለዚህ የቲ-ቴስት ዋጋው |-1.306| ኔጋቲቭ ቢሆንም የማንኛውም ቁጥር ፍጹም ዋጋ (Absolute value) ፖዘቲቭ በመሆኑ ፍጹም ዋጋውን በመውሰድ (1.306) ሆኗል፡፡ ስለዚህ የቲ-ቴስት ዋጋ (1.306) ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ (0.197) ጋር ሲወዳደር በልጦ ተገኝቷል፡፡

ትርጉም ባለው መንገድ የተገኘው የውጤት ለውጥ ስታትስቲካዊ ጉልህነት (Statisticsl Significance) (0.197) ከ(0.05) ስለሚበልጥ ጥብቅ ቡድኑ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገበው ውጤት ልዩነት የለውም ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ መልኩ ሲታይ

በቅድመ ትምህርት ፈተናው ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በድህረ ትምህርቱ ፈተና ውጤታቸውም ዝቅተኛ ውጤት አስመዝግበዋል ማለት የሚያስችል ይመስላል:: በመሆኑም የጥብቅ ቡድኑ ተማሪዎች ባድህረ ትምህርት ፈተናው ውጤት ጉልህ የሆነ ብልጫ አላስመዘገቡም:: ለዚህም በልምምዱ ወቅት ገቢራዊ በሆነው የማስተማሪያ ዘዴና አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት አለመማራቸው በምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል::

በተመሳሳይ ሁኔታ የሙከራ ቡድኑ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት ለማስተማር በተዘጋጀው መማሪያ ለአንድ ወር ሲማር ቆይቷል:: ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት ይልቅ በድህረ ፈተናው የተሻለ ውጤት ማስመዝገቡን ወይም አለማስመዝገቡን በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ሁለት ቀርቧል:: የዚህን ዝርዝር መረጃ (አባሪ 13 እና 14ን ከገጽ 108-109 ይመለከቷል)::

| የሙከራ ቡድኑ ፈተና | $\overline{x}$ | sd | df | $t_{obt}$ | $t_{crt}$ | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት | 36.31 | 17.43 | 51 | -17.923* | 0.000 | አለው |
| ድህረ ትምህርት | 62.11 | 25.70 | | | | |

የጉልህነት ደረጃ (የስህተት ይሆንታ መጠን) (Level of significance) $*P<0.05$

ሰንጠረዥ 2:- የሙከራ ቡድኑ የቅድመና ድህረ ትምህርት የፈተና ውጤቶች ንጽጽር በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶ ሲታይ:-

የሙከራ ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (62.11) ከቅድመ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት (36.31) ጋር ሲነጻጸር በከፍተኛ ደረጃ የሚበልጥ ይመስላል:: ውጤቱም በኩረጃ ወይም በሌላ የተላውጠ ተጽዕኖ የተገኘ ሳይሆን በችሎታ እንደሆነም ያመላከተ ይመስላል:: የቅድመ ትምህርቱ (17.43) እና የድህረ ትምህርቱ (25.70) የአማካይ መደበኛ ልይይት (Standard deviation) ከፍተኛ በመሆኑ የብዙዎቹ ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከጠቅላላው አማካይ ውጤት የራቀ እንደሆነ ስሌቱ አመላክቷል::

የቅድመና የድህረ ትምህርቱን አማካይ ውጤት በመጠቀም የአማካይ ልዩነት ማረጋገጫ ቀመር (ቲ-ቴስት) ተሰርቷል:: ለምናልባት ስህተት 5% ($p<0.05$) በመተው ወይም 95% እርግጠኛ በመሆን፣ 51 የነፃነት ደረጃ፣ (0.05) የጉልህነት ደረጃ የተነበበው የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ (0.000) ነው:: የቲ-ቴስት ዋጋው |-17.923| ኔጋቲቭ ቢሆንም ፍጹም ዋጋውን በመውሰድ (17.923) ይሆናል:: የቲ-ቴስት ዋጋው ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋው ጋር ተወዳድሮ ብልጫ አሳይቷል::

በመሆኑም ትርጉም ባለው መንገድ የተገኘው የውጤት ለውጥ ስታትስቲካዊ ጉልህነት (Statisticsl Significance) (0.000) ከ(0.05) ስለሚያንስ ጉልህ ልዩነት ያለው መሆኑን ስሌቱ አመላክቷል:: ስለዚህ የሙከራ ቡድኑ ከትግበራው በኋላ ያሳዩት የችሎታ ልዩነት በስታትስቲካዊ ቀመሩ መሠረት የጎላ ብልጫ አለው ማለት ይቻላል:: በሌላ መልኩ ሲታይ በቅድመ ትምህርት ፈተናው ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በድህረ ትምህርቱ ፈተና የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል ማለት የሚያስችል ይመስላል:: ስለዚህ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በድህረ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡት ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አሳይቷል:: ይህም በልምምዱ ወቅት ገቢራዊ በሆነው ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴና አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት መማራቸው ነው ቢባል ምክንያታዊ ሊሆን ይችላል:: በመሆኑም ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ መሻሻል እንደታየ ስሌቱ አመላክቷል::

የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በድህረ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡት ከፍተኛ ውጤት በቪዲዮ እየተቀረጹ ከተሰበሰቡት የምልከታና የቃለ መጠይቅ እሙን መረጃዎች ጋር የሚስማማ ሆኖ ተገንቷል:: በመሆኑም ተማሪዎቹ በየክፍለ ትምህርቱ በቅድመ ንባብ፣ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ የቀረቡትን የጽህፈት ክንዋኔዎችና ተግባራት በንቃትና በፍላጎት ሲሰሩ ተስተውሏል::

የሙከራና የጥብቅ ቡድኖቹ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቶች ለየብቻ ተነፃጽረው ተተንትነዋል:: በመቀጠል የቡድኖቹን የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት በማነጻጸር ልዩነታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደነበር ማሳየት አስፈላጊ ይሆናል:: ምክንያቱም ከሙከራ ትምህርቱ በፊት ምንም ሳይማሩ በወሰዱት ፈተና ክሂሎቹን በውህደት በመገልገል ረገድ የነበራቸው የግንዛቤ ደረጃ ምን ያህል እንደነበር ማወቅ ያስፈልጋል::

በዚህ መሠረት የሁለቱ ቡድኖች የቅድመ ትምህርት የፈተናው ውጤቶች በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ሦስት ቀርቧል። የዚህን ዝርዝር መረጃ (አባሪ 11 እና 13ን ከገጽ 106-109 ይመለከቷል)።

| ቡድኖቹ | $\overline{X}$ | sd | df | $t_{obt}$ | $t_{crt}$ | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሙከራ | 36.31 | 17.43 | 51 | -0.414* | 0.680 | የለውም |
| ጥብቅ | 34.75 | 19.79 | | | | |

የጉልህነት ደረጃ (የስህተት ይሆንታ መጠን) (Level of significance) *P<0.05

ሰንጠረዥ 3፡- የሙከራና የጥብቅ ቡድኖቹ የቅድመ ትምህርት የፈተና ውጤቶች በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶ ሲታይ፡-

የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት (36.31) ከጥብቅ ቡድኑ አማካይ ውጤት (34.75) የሚበልጥ ይመስላል። የሁለቱ ቡድኖች የአማካይ መደበኛ ልይይት ደግሞ የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ትምህርት ፈተናው (17.43) እና የጥብቅ ቡድኑ በቅድመ ትምህርት ፈተናው (19.79) ሆኗል። በዚህም መሠረት የአማካይ መደበኛ ልይይቱ ከፍተኛ በመሆኑ፣ የበርካታ ተማሪዎች አማካይ ውጤት ከአጠቃላዩ አማካይ ውጤት የራቀና የሚዋዥቅ መሆኑን ስሌቱ አመላክቷል።

የዚህን ልዩነት አስተማማኝነት በስታትስቲክስ ስሌት ቀመር መረጋገጥ ስላለበት በ(ቲ-ቴስት) ተሰልቷል። ለምናልባት ስህተት 5% (p<0.05) በመተው የተሰራው የቲ-ቴስት ዋጋ |-0.414| ኔጋቲቭ ቢሆንም ፍጹም ዋጋውን በመውሰድ (0.414) ሆኗል። በ(0.05) የጉልህነት ደረጃና በ51 የነፃነት ደረጃ በባለሁለት ጫፍ ፍተሻ የተነበበው የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ (0.680) ሆኗል። ስለዚህ የቲ-ቴስት ዋጋ ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ ማነሱ ተረጋግጧል። ትርጉም ባለው መንገድ የተገኘው የውጤት ለውጥ ስታትስቲካዊ ጉልህነት (Statisticsl Significance) (0.680) ከ(0.05) ስለሚበልጥ በጥብቅና በሙከራ ቡድኖቹ መካከል ጉልህ ልዩነት የለም ማለት ይቻላል። በዚህም ምክንያት የሙከራ

ትምህርቱ በተለያየ ሁኔታ ከመሰጠቱ በፊት ሁለቱም ቡድኖች ክሂሎቹን በውህደት በመገልገል ረገድ የነበራቸው እውቅናና ችሎታ ተመሳሳይ ነው ቢባል ምክንያታዊ ነው።

የሙከራና የጥብቅ ቡድኖቹ የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ከተነፃፃረ በኋላ ቡድኖቹ በድህረ ትምህርት ፈተናው መሠረት ምን ያህል የችሎታ ልዩነት እንዳሳዩ (እንዳላሳዩ) ለመገምገም ተሞክሯል። በመሆኑም ትምህርቱን የተማሩበት ሥነ ዘዴና የትምህርቱ ይዘት የተለያየ በመሆኑ የሙከራና የጥብቅ የቡድኖቹ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቶች በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት ቀመር በማነጻጸር ተሰልቶ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ አራት ልዩነታቸው ተፈትሿል። የዚህን ዝርዝር መረጃ (አባሪ 12 እና 14ን ከገጽ 106-109 ይመለከቷል)።

| ቡድኖቹ | $\overline{X}$ | Sd | df | $t_{obt}$ | $t_{crt}$ | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሙከራ | 62.11 | 25.70 | 51 | -5.379* | 0.000 | አለው |
| ጥብቅ | 36.23 | 20.11 | | | | |

የጉልህነት ደረጃ (የስህተት ይሆንታ መጠን) (Level of significance) $*P<0.05$

ሰንጠረዥ 4፡- የሙከራና የጥብቅ ቡድኖቹ የድህረ ትምህርት የፈተና ውጤቶች በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶ ሲታይ፡-

የሙከራ ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (62.11) ከጥብቅ ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (36.23) ብልጫ ያለው መሆኑን ከስሌቱ መረዳት ይቻላል። የሁለቱ ቡድኖች የአማካይ መደበኛ ልይይት (Standard deviation) ሲታይ የጥብቅ ቡድኑ በድህረ ትምህርት ፈተናው (20.11) ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ደግሞ በድህረ ትምህርት ፈተናው (25.70) ሆኗል። ስለዚህ የአማካይ መደበኛ ልይይቱ ከፍተኛ በመሆኑ፣ የበርካታ ተማሪዎች የተናጠል አማካይ ውጤት ከአጠቃላዩ አማካይ ውጤት የራቀ ውጤት አስመዝግበዋል።

የአማካይ ውጤቶችን ልዩነት አስተማማኝነት በስታቲስቲክስ ለማረጋገጥ የቲ-ቴስት ስሌት ተሰርቷል:: ለምናልባት ስህተት 5% ($p<0.05$) በመተው የተገኘው የቲ-ቴስት ዋጋ |-5.379| ቢሆንም ፍጹም ዋጋውን በመውሰድ (5.379) ሆኗል:: በ(0.05) የጉልህነት ደረጃና በ51 የነፃነት ደረጃ በባለሁለት ጫፍ ፍተሻ የተነበበው የቲ-ሰንጠረዥ ዋጋ (0.000) ሆኗል:: ስለዚህ የቲ-ቴስት ዋጋው ከቲ-ሰንጠረዥ ዋጋው ጋር ሲወዳደር በልጦ ተገኝቷል:: በመሆኑም ትርጉም ባለው መንገድ የተገኘው የውጤት ለውጥ ስታትስቲካዊ ጉልህነት (Statisticsl Significance) (0.000) ከ(0.05) ያንሳል:: ስለዚህ የሙከራ ቡድኑ በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ከጥብቅ ቡድኑ ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ከፍተኛ ብልጫ አለው ማለት ይቻላል:: ከዚህ በፊት ሁለቱም ቡድኖች በቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት ተመሳሳይ ደረጃ ነበራቸው:: ነገር ግን ለሙከራ ቡድኑ በልምምድ ወቅት ገቢራዊ በሆነው የማስተማሪያ ዘዴና የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት በመማሩ ምክንያት ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ መሻሻል እንዳሳየ ስታትስቲክሱ አመላክቷል::

ክሂሎቹን በተለመደው መንገድ በተናጠል ሲማር የቆየው የጥብቅ ቡድኑ የጎላ ልዩነት እንዳላሳየ ስሌቱ አሳይቷል:: ከሙከራ ቡድኑ አባላት መካከል ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው የሰጡት ምላሽ ከስታትስቲክስ ውጤቱ ጋር ተደጋጋፊነት አለው:: እንዲሁም በክፍል ውስጥ የክንውን ምልከታው ወቅት በየክፍለ ትምህርቱ በተማሪዎች መካከል የነበረው ተሳትፎና ተራክቦ በንቁ ተሳታፊነት የተከናወነ ነበር:: በሌላ በኩል ቅድመ ትምህርት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው የሙከራ ቡድኑ ስድስት ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት የተማሩበት ጊዜ እንዳልነበር ገልጸዋል:: እንዲሁም ለ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያነት በተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ፣ በማጣቀሻነት በተዘጋጁት መጻሕፍትና ተዛማጅ ጽሑፎች ውስጥ ክሂሎቹን በውህደት እንዲለማመዱ የሚያደርጉ መልመጃዎችና ተግባራት እንዳልተካተቱበት ገልጸዋል:: (አባሪ 5፣ ገጽ 68 -70 ይመለከቷል)::

ለቃለ መጠይቅ የተመረጡት ስድስቱም ተማሪዎች አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ትምህርት በውህደት በመማራቸው ያገኙት አዲስ ነገር ወይም ያጋጠማቸው ችግር ምን እንደሆነ እንዲገልጹ ተጠይቀዋል:: ተማሪዎቹ ከሰጡት ምላሽ ውስጥ "መደበኛው የመማሪያ መጽሐፍ አዘገጃጀቱና አቀራረቡ ችግር አለበት:: በመሆኑም ከምን ተነስተን ምን እንደምንጽፍና እንደምናነብ የሚያስጨንቀን ጓይ ነበር::" በማለት

ተጠያቂዎቹ ገልጸዋል፡፡ በአሁኑ ትምህርት አቀራረብ ግን "እያነበብን መፃፍ ወይም እየፃፍን ማንበብ መሆኑ ትልቅ መነቃቃትን ፈጥሮልናል፡፡" በማለት ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ትምህርት በውህደት መማራቸው ለውጥ እንዳስገኘላቸው ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት መማራቸው እንደጠቀማቸው፣ በራስ መተማመናቸውን የበለጠ እንዳዳበረላቸው፣ አርቀው እንዲያስቡ፣ ትምህርቱን በፍላጎት እንዲከታተሉት ማስቻሉን፣ ወደፊት በዚሁ መንገድ መማር እንደሚፈልጉና ሌሎች ተማሪዎችም በዚሁ መንገድ ቢማሩ እንደሚመረጥ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ይሰጡ የነበሩት የጥንድና የቡድን ሥራዎች ሃሳብ ለመጋራት፣ በጽብረቃ ለመፃፍ መነሻ ሃሳብ ለማግኘት ትልቅ እገዛ እንዳደረገላቸው ገልጸዋል፡፡ (አባሪ 6፣ ገጽ 71 -73 ይመለከቷል) በስታትስቲካዊ ስሌቱ የተገኘውን ጉልህ የውጤት ልዩነት ይህን የሚደግፍ ይመስላል፡፡

ከሙከራ ቡድኑ በቪዲዮ እየተቀረጹ ከተሰበሰቡት የየዕለት ክንውን ምልከታ መረጃዎች እንደተረጋገጠው፣ ማንበብና መፃፍን በውህደት ሲማሩ ሁሉም ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባር በንቃትና በፍላጎት ሲያከናውኑ ተስተውሏል፡፡ የድህረ ትምህርት ፈተናው ውጤትም ይህን ሃሳብ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በልዩ ልዩ ምክንያት በመጀመሪያው ቀን ከቀሩት ስምንት ተማሪዎች ጋር በመወያየት ለችግሮቻቸው የጋራ መፍትሔ በማስቀመጥ፣ ለወደፊቱ ሁሉም እንደማይቀሩ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ በመሆኑም ቀሪዎቹን ቀናት ሁሉም ተማሪዎች በተነሳሽነት ትምህርቱን ተከታትለዋል፡፡ ለቀሪ ተማሪዎች ከመደበኛው የመማማሪያ ጊዜ ውጭ ያልተማሩትን የትምህርት ክፍል የማካካሻ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ በመረጃ ትንተናው እንደታየው የሙከራ ቡድኑ አንብቦ መረዳትና መፃፍን በውህደት በመማራቸው መሻሻል እንዳሳዩ በፈተና፣ በክፍል ውስጥ ክንውን ምልከታና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎችና እሙኖች አመላክተዋል፡፡

## 4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የጥናቱን ዓላማዎች ለማሳካት በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተሰበሰቡ ሲሆን ከጥናቱ ባህሪይ ጋር በሚሄዱ የመተንተኛ ስልቶችም ተተንትነዋል፡፡ በመረጃዎች ትንታኔ መሠረት የጥናቱ ውጤት ተብራርቶ በሚከተለው መንገድ ቀርቧል፡፡

የተጠኚዎችን ፈተና ከሁለት በላይ በሆኑ አራሚዎች በመካፈል የአንድን ነፃ ተለዋዋጭ የተለያዩ እርከኖች በቡድኖቹ ባህሪያት ላይ የፈጠሩት ልዩነት እንዳለና እንደሌለ ለማረጋገጥ ነፃ ናሙና ልይይት ትንተና ዘዴ (One Way ANOVA) በመጠቀም ተሰልቷል። ምክንያቱም የአንድን ተማሪ ውጤት ሦስት የተለያዩ መምህራን በማረማቸውና የተለያየ ውጤት በመስጠታቸው ነው። በዚህ መሠረት የሙከራ ቡድኑን ቅድመ ትምህርት ፈተና በሦስቱ አራሚዎች መካከል ያለው የውጤት አሰጣጥ ሁኔታ እንደሚከተለው ነው። በስሌቱ መሠረት የመጀመሪያው አራሚ መምህር ለሙከራ ቡድኑ በቅድመ ፈተናው ከመቶው የሰጠው ዝቅተኛ ውጤት 2 ሲሆን ከፍተኛው 69 ነው። አማካይ ውጤቱም 36.83 ሆኗል። ሁለተኛው አራሚ መምህር ከመቶው የሰጠው ዝቅተኛ ውጤት 5 ሲሆን ከፍተኛው 70 ነው። አማካይ ውጤቱም 35.33 ሆኗል። ሦስተኛው አራሚ መምህር ደግሞ ከመቶው የሰጠው ዝቅተኛ ውጤት 3 ሲሆን ከፍተኛው 79 ነው። አማካይ ውጤቱም 36.79 ሆኗል። በዚህ መሠረት በጠቃላይ የሦስቱ አራሚዎች የውጤት አስተማማኝነት ስታትስቲካዊ ጉልህነት (Statisticsl Significance) (0.889) በመሆኑ የጳኝነት ግምገማው የመጣጣም ደረጃ ተገኝቷል።

የሙከራ ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት አሰጣጥ ደግሞ፣ የመጀመሪያው አራሚ መምህር ከመቶው የሰጠው ዝቅተኛ ውጤት 8 ሲሆን ከፍተኛው 95 ነው። አማካይ ውጤቱም 60.73 ሆኗል። ሁለተኛው አራሚ መምህር ከመቶው የሰጠው ዝቅተኛ ውጤት 10 ሲሆን ከፍተኛው 98 ነው። አማካይ ውጤቱም 63.97 ሆኗል። ሦስተኛው አራሚ መምህር ደግሞ ከመቶው የሰጠው ዝቅተኛ ውጤት 6 ሲሆን ከፍተኛው 98 ነው። አማካይ ውጤቱም 61.63 ሆኗል።

በዚህ መሠረት በጠቃላይ የሦስቱ አራሚዎች የውጤት አስተማማኝነት ስታትስቲካዊ ጉልህነት (Statisticsl Significance) (0.805) በመሆኑ የጳኝነት ግምገማው የመጣጣም ደረጃ ተገኝቷል። ስለዚህ የአራሚዎች የጳኝነት ስምምነት ከፍተኛ በመሆኑ ውጤቱ እንዳለ ተመዝግቧል። በስሌቱ መሠረት የሙከራ ቡድኑ በቅድመ ፈተናው ከመቶው ዝቅተኛው ውጤት 2 ሲሆን ከፍተኛው 79 ነው። ስለዚህ በከፍተኛውና በዝቅተኛው ውጤት መካከል የመጣው ሰፊ ልዩነት ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት የተማሩበት ጊዜ እንደሌለ ከገለጹት ጋር የሚስማማ ይመስላል።

በአጠቃላይ በስታትስቲክስ ስሌቱ መሠረት የጥብቅ ቡድኑ የተወሰኑ ተማሪዎች ከቅድመ ትምህርት ፈተናው የተወሰነ ግንዛቤ በማግኘታቸው ምክንያት በድህረ ትምህርት ፈተናው መጠነኛ መሻሻል ማሳየት እንደቻሉ ከውጤት መግለጫው መረዳት ይቻላል:: ነገር ግን የጥብቅ ቡድኑ በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል በተደረገው ስታቲስቲካዊ ንጽጽር ጉልህ ልዩነት አለመኖሩ ተመዝግቧል::
(ሰንጠረዥ 1 ይመለከቷል)::

የሙከራ ቡድኑ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተናዎች ውጤትም ተነጻጽሯል:: ከቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት (36.31) ይልቅ በድህረ ትምህርት ፈተናው (62.11) ከፍተኛ ውጤት ተመዝግቧል:: ልዩነቱ በአስተማማኝ የአማካይ ውጤት ልዩነት ማሳያ ቀመር (ቲ-ቴስት) ተሰልቶ የጎላ ልዩነት መመዝገቡ ተረጋግጧል:: ይህም የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት በማስተማር ክሂሎቹን ማጎልበት ይቻላል ወደሚል መደምደሚያ ላይ ሊደረስ ይቻላል:: ለውጡ የመጣው ክሂሎቹን በውህደት ሲማሩ የቀረበላቸውን መማሪያ እያነበቡና እየፃፉ፣ ከንባብ በፊት፣ በንባብ ጊዜና ከንባብ በኋላ በተዘጋጁት ተግባራት ላይ ተወያይተው ያዳበሩትን ሀሳብ አሻሽለው በመፃፋቸው የመጣ ይመስላል:: (ሰንጠረዥ 2 ይመለከቷል)::

ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት ሲለማመዱ ስለጽሑፉ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲተነብዩ፣ ትርጉም እንዲሰጡ፣ ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችን እንዲመረምሩም አግዟቸዋል:: ሌላው ደግሞ ተማሪዎች ሳነበቡት ወይም ለፃፉት ነገር ማጠቃለያ መስጠት እንደቻሉና፣ ሳነበቡት ወይም ለፃፉት ይዘት በቂ መረጃ ያላቸው መሆኑንም የሚጠቁም ሆኖ ተገኝቷል:: ይህም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ እንደ መሠረታዊ አንብቦ መረዳትና የጽሑፍ ማቀናበር ችሎታን ማጎልበቻ ብልሀት ተደርጎ እንደሚወሰድ ጽንሰ ሃሳባቸውን ካረመዱት Gary (1995)፣ Beerdgew (2003) እና Block (1997) ሃሳብ ጋር የጥናቱ ውጤት የሚስማማ ይመስላል::

የሙከራ ቡድኑ መማሪያ የተለያዩ ይዘትና ተግባራትን አካቶ በስምንት የትምህርት ክፍል ተደራጅቶና ተዘጋጅቶ ማንበብና መፃፍን በቅንጅት ተምሯል:: ጥብቅ ቡድኑ ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው መጽሐፍ ክሂሎቹን በተናጠል በተለመደው መንገድ ከተማረ በኋላ ሁለቱም ቡድኖች የችሎታ ልዩነታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማየት ድህረ ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል:: ከፈተናው ውጤት መረዳት

እንደሚቻለው በሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች መካከል (25.8) መሆኑ የጎላ ልዩነት መታየቱን የስታትስቲክስ ስሌቱ አሳይቷል። በመሆኑም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከጥብቅ ቡድኑ ተማሪዎች የላቀ ውጤት አስመዝግበዋል። ይህንንም ልዩነት የፈጠረው የትምህርት አቀራረቡና ማንበብና መፃፍን በውህደት በመማራቸው ነው ቢባል ምክንያታዊ ይሆናል። ስለዚህ ክሂሎቹ በውህደት መቅረባቸው የተማሪዎችን አንብቦ መረዳትና የመፃፍ ችሎታ አጎልብቶታል ለማለት ይቻላል።

ውጤቱም Block (1997) የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች በውህደት ከቀረቡ ተማሪዎች ቋንቋውን የመማር ችሎታቸው ይጎለብታል። እንዲሁም ተማሪ ተኮር ዘዴን በመገልገልና ማንበብና መፃፍን በውህደት በተግባር የሚማሩ ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ ትኩረት እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ በወቅቱ የተሻለው የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ እንደሆነም ካቀረበው ንድፈ ሀሳብ ጋር የጥናቱ ውጤት የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል።

የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች በውህደት ከቀረቡ የተማሪዎችን የጽሑፍ ቋንቋ ሊያሳድጉ ይችላሉ። እንዲሁም ትርጉም እንዲገነቡ ያግዛሉ። ለቀረበ መረጃ አድናቆታዊ ምላሽ በጽሑፍ ለማቅረብ ያስችላሉ። ስለዚህ ማንበብና መፃፍን በውህደት የሚማሩ ተማሪዎች በትምህርቱ ላይ ትኩረት እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ ትምህርቱን በተመስጦ እንዲከታተሉ ያስችላቸዋል። እንዲሁም በተማሪዎች ላይ የኃላፊነት ስሜት በመፍጠር በትኩረት፣ በተረጋጋ መንፈስና በጥሩ ግንዛቤ መልዕክቱንም እንዲረዱት ያስችላቸዋል ከሚለው የእነ Langer (2000) ጽንሰ ሃሳብ ጋር የጥናቱ ውጤት ይደጋገፋል።

በቪዲዮ እየተቀረጹ ከተሰበሰቡት የክፍል ውስጥ ክንውን ምልከታ የመረጃ ውጤቶች መረዳት እንደተቻለው ተማሪዎች ክሂሎቹን በውህደት ሲማሩ በከፍተኛ ስሜት የተከታተሉት፣ የወደዱትና የተቀበሉት መሆኑን አሳይቷል። ከነባሩ የማስተማር ዘዴ በተሻለ ሁኔታ እንደሚመርጡትና በተለይም የአንብቦ መረዳትና እያስታወሱ የመፃፍ ችሎታቸውን እንዳዳበረላቸው ገልጸዋል። ተማሪዎቹ በጥንድና በቡድን ተወያይተው፣ የሰሯቸውን ተግባራት እየተለዋወጡ በመገምገም አስተያየታቸውን በጽሑፍ ሲሰጡ፣ ሁሉም ተማሪዎች በመማሪያው ውስጥ ያሉትን ክንዋኔዎችና መልመጃዎች በትጋት ሲሰሩ ተስተውሏል። (አባሪ 10 ገጽ 104-105 እና አባሪ 16 ገጽ 112-114 ይመለከቷል)

የየቡድኖቹ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ራሱን ችሎ ታይቷል። የሙከራ ቡድኑ በድህረ ትምህርት የፈተና ውጤትና በቅድመ ትምህርቱ ፈተና ውጤት መካከል (25.8) መሆኑ ጉልህ ልዩነት አሳይቷል። ስለዚህ የሙከራ ቡድኑ የተማረበት ሥነ ዘዴና የትምህርት ዝግጅቱ የተለየ መሆኑ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ እረድቷቸዋል ቢባል ምክንያታዊ ሊሆን ይችላል። የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በድህረ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት (62.11 ከመቶ) በራሱ ሲታይ በአንፃራዊነት የተሻለ ውጤት ይመስላል። ነገር ግን ከፍተኛ ውጤት አለመሆኑን መረዳት ይቻላል። በመሆኑም የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅት የማለማመዱ ተግባር በተደጋጋሚ፣ ሰፊ ጥረትንና ጊዜን የሚጠይቅ እንደሆነ ያመላከተ ይመስላል። (ሰንጠረዥ 4 እና 5 ይመለከቷል)።

የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በግል ያስመዘገቡት ውጤት ሲታይ ከሁለት ተማሪዎች በቀር በድህረ ትምህርት ፈተናው የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል። ይህ አንፃራዊ የውጤት መሻሻል የተገኘው ተማሪ ተኮር የማስተማር ሥነ ዘዴን በመጠቀምና ክሂሎቹን በውህደት እንዲማሩ በመደረጉ ይመስላል። ነገር ግን የቆየው አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ አቀራረብ በተናጠል መሆኑና የተማሪዎች ችሎታ ደካማነት ተዳምሮ ለማሻሻል ሰፊ ጥረትና ረጅም ጊዜ እንደሚያስፈልግ የሚጠቁም ነው።

በእያንዳንዱ ተማሪ አማካይ ውጤትና በአጠቃላይ አማካይ ውጤቱ መካከል ያለው ከፍተኛ ልዩነት ማንበብና መፃፍን በውህደት ቢማሩም የሁሉንም ተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ችሎታቸውን በአጭር ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል እንዳልተቻለ የሚያመላክት ሆኗል። የሙከራና የጥብቅ ቡድኖቹ የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት በስሌቱ መሠረት የቲ ሠንጠረዥ ዋጋው (0.68) ከጉልህነት ደረጃው (0.05) በመብለጡ ምክንያት ልዩነት አልተመዘገበም። ይህ ደግሞ ቡድኖቹ ከሙከራ ትምህርቱ በፊት ክሂሎቹን በውህደት በመለማመድ ረገድ ተመሳሳይ የሆነ ችሎታ እንደነበራቸው ያመላከተ ይመስላል። ከሙከራ ትምህርቱ በኋላ ግን በቡድኖቹ መካከል የጎላ ልዩነት ተመዝግቧል። (ሰንጠረዥ 4 ይመለከቷል)።

በድህረ ትምህርት ፈተናው የሙከራ ቡድኑ የተሻለ ውጤት በማስመዝገቡ ምክንያት ማንበብና መፃፍን በውህደት በማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ያመላከተ ይመስላል። በመሆኑም ክሂሎቹንም ለማዳበር ያስችላል

የሚል መደምደሚያ ለመስጠት ያስደፍራል። ክሂሎቹን በውህደት ማስተማር ተማሪዎችን ለትምህርት የሚያነሳሳ፣ የጽሑፍ ቋንቋቸውን እንዲያሳድጉ የሚረዳና በጥሩ ግንዛቤ መልዕክቱንም እንዲረዱት የሚያስችል ቢሆንም፤ ሰፊ ጥረት፣ የልምምድና ጊዜን የሚጠይቅ እንደሆነ መገንዘብ ተችሏል።

በመጨረሻም በመረጃ ትንተናው መሠረት እንደታየው የሙከራ ቡድኑ ድምር ውጤት (3229.72) ከጥብቅ ቡድኑ ድምር ውጤት (1883.96) በመሆኑ ከፍተኛ ብልጫ አሳይቷል። አስተማማኝና ጉልህ እንደሆነም የስታትስቲክስ ስሌቱ አረጋግጧል። የሙከራ ቡድኑ ውጤት ጉልህ ብልጫ የማስመዝገቡ ምክንያት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ውህደታዊ አቀራረብ፣ የትምህርቱ ይዘትና ተማሪዎች ትምህርቱን በትኩረት በመከታተላቸው ነው ቢባል ተጠየቃዊ ይሆናል። (ሰንጠረዥ 4 ይመለከቷል)።

በጥናቱ የተሳተፉት የሁለት ክፍል 104 ተማሪዎች አፋቸውን የፈቱት በአማርኛ ቋንቋ እንደሆነ አጥኝው በክፍል ውስጥ ጠይቆ ለማወቅ ችሏል። የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተመሳሳይ መሆኑ ለጥናቱ ውጤት አስተዋጽኦ ያደረገም ይመስላል። በአጠቃላይ የሙከራ ቡድኑ ከጥብቅ ቡድኑ የተሻለ ውጤት ማስመዝገቡ ለጥናቱ ጥያቄ አወንታዊ ምላሽ አስገኝቷል ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የፍትነታዊ ምርምሩ ውጤት አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን ችሎታ ለማሻሻል የሚረዳ መሆኑን አመላክቷል።

ይህ ውጤት ከሞገስ (1999) እና ከአበበች (2002) የጥናት ውጤት ማንበብንና መፃፍን ለየብቻ በዝምድና ማሳያ በማነፃጸራቸው ረገድ፣ የቲ-ቴስት ስሌቱ በኩደር ሪቻርድስ ቀመር መሠራቱ፣ በናሙና አመራረጥ፣ በጥናቱ ቦታና ጊዜ፣ በአተገባበሩና በተወሰነም ደረጃ ቢሆን በትንታኔው የተለየ ነው። ነገር ግን የማንበብና የመፃፍን ክሂሎች በውህደት በመቅረባቸው ምክንያት የተገኘው የውጤት መሻሻል ተመሳሳይነት አሳይቷል።

# ምዕራፍ አምስት

## የጥናቱ ግኝት ማጠቃለያና አስተያየት

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ግኝት ማጠቃለያ፣ በጥናቱ የተደረሰበት መደምደሚያና ከጥናቱ ውጤት በመነሳት በአጥኝው የተሰነዘሩ አስተያየቶች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

## 5.1 የጥናቱ ግኝት ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራዊ ጥናት እንደነበር ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ በክሂሎቹ ትስስርና ዝምድና ተመስርቶ በውህደት መቅረባቸውን ተግባራዊነትና ውጤታማነት በመፈተሽ በጥናቱ ለመመለስ የተሞከሩ መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

- የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ትስስርና መደጋገፍ ምን ያህል ነው?
- አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን በማጣመርና በማቀናጀት ማስተማር ይቻላልን?
- የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት የማስተማር ልምምዱ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን ለማሻሻል ይረዳ ይሆን?

እነዚህን ጥያቄዎች በአግባቡ መመለስ እንዲቻል በመጀመሪያ ተጠኝዎችና የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተመርጠዋል፡፡ አስፈላጊዎች ናቸው የተባሉ መረጃዎችም ተሰብስበዋል፡፡ የተገኙትን እሙኖችና መረጃዎች በአግባቡ ለመተንተን እንዲቻል የተለያዩ መተንተኛ ስልቶች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ለተጠኝዎቹ አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን የሚለካ ቅድመ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷቸዋል፡፡ የሙከራ ቡድኑ ክሂሎቹን አዋህዶ ለማስተማር የሚያስችል መማሪያ በአጥኝው ተዘጋጅቷል፡፡ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከመደበኛ ፈረቃቸው ውጭ የሚማሩበት መንገድ ተመቻችቷል፡፡ ለአራት ሳምንታት (በሳምንት ሁለት ቀን) ለአንድ ጠር እንዲማሩም ተደርጓል፡፡

የጥብቅ ቡድኑ ደግሞ በተለመደው መደበኛ ክፍለ ጊዜ፣ ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው የመማሪያ መጽሐፍና በነባሩ የማስተማር ዘዴ ትምህርቱን ተከታትሏል። በመጨረሻም ሁለቱም ቡድኖች አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን የሚለካ የጽሑፍ ድህረ ትምህርት ፈተና ለሁለቱም ቡድኖች ተሰጥቷል። ውጤቱም በቃለ መጠይቅና በክፍል ውስጥ ክንውን ምልከታ ከተሰበሰበው መረጃ ጋር እየተገናዘበ ተመዝግቧል።

በአጠቃላይ ለጥናቱ የሚያስፈልጉት መረጃዎች በፈተና፣ በቪዲዮ ቀረፃ በታገዘ የክፍል ውስጥ ክንውን ምልከታና ቃለ መጠይቅ ተሰብስበዋል። የፈተናው ውጤት በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶ ተተንትኗል። የሙከራ ቡድኑ የየዕለት የመማር ሂደት፣ ትግበራውና ከመምህሩ ጋር የነበራቸው ተራክቦ በቪዲዮ ተቀርጾና ተጠናቅሮ በመረጃነት ተይዟል። በመሆኑም የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል።

የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ ተሞክሯል። የሙከራና የጥብቅ ቡድኖቹ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተናዎች በሦስት ባለሙያዎች ታርመዋል። ውጤታቸው ከታወቀ በኋላ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተናዎቹ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቶዋል። ልዩነቱንም በአስተማማኝ የአማካይ ውጤት ልዩነት ማሳያ ቀመር (ቲ-ቴስት) ተሰልቷል። በሙከራና በጥብቅ ቡድኑ አማካይ ውጤት መካከል (25.88) በመሆኑ የጎላ ልዩነት መኖሩን አረጋግጧል። የጥብቅና የሙከራ ቡድኖቹ መካከል በቅድመ ትምህርት ፈተናው ውጤት ልዩነት እንዳልተመዘገበ በስታትስቲክሱ ተረጋግጧል። የሁለቱ ቡድኖች ውጤት በተናጠልም ታይቷል። የሙከራ ቡድኑ በድህረ ትምህርት ፈተናው ያስመዘገበው (62.11) ውጤት ከቅድመ ትምህርት ፈተናው (36.31) ውጤት ጋር ሲነጻጸር የጎላ ልዩነት ያለው መሆኑ ተረጋግጧል። የጥብቅ ቡድኑ ግን የውጤት ልዩነት እንዳልነበረው ተመዝግቧል።

ከክፍል ውስጥ ክንውን ምልከታውና ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ እንዳሳየው በትግበራው ወቅት የመወያየት፣ ከቀደመ ልምድ በመነሳት ሃሳብ የማመንጨትና ካነበቡት ተነስተው የተሰማቸውን በጽሑፍ የመግለጽ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። በተጨማሪም ለትምህርቱ እንደተነሳሱ፣ ሃሳብ የማመንጨትና አስታውሶ የመፃፍ ችሎታቸውን እንዳዳበረላቸው ለመረዳት ተችሏል። ክሂሎቹን በውህደት መማራቸው በተማሪዎች ዘንድ ተመራጭ መሆኑንም የተሰበሰቡት መረጃዎች አረጋግጠዋል። ክሂሎቹ በውህደት የቀረቡበት መንገድ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታ

በማሻሻሉ ምክንያት ክሂሎቹን በውህደት ማስተማር ወደፊትም እንዲቀጥል የተማሪዎችን ይሁንታ አግኝቷል። ይሁን እንጅ አንፃራዊ ለውጥ ቢኖርም የቆየውንና የተለመደውን የተማሪዎችን የማንበብና የመፃፍ ልምድ ችግር ሙሉ በሙሉ መፍታት እንዳልተቻለ ለመረዳት ተችሏል። የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታ ለማሳደግ በተደረገው ልምምድ፤ የጊዜ እጥረት፣ የመማሪያ ክፍል እጥረት፣ የማባዣ ማሽን እጥረትና በሌሎችም ምክንያቶች የተነሳ ጥናቱ እክል አጋጥሞት ነበር።

ከጥናቱ ውጤት በመነሳት አጥኚው ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ደርሷል።

- የስታትስቲክስ ስሌቱ እንደሚያመለክተው ጥብቅ ቡድኑ በቅድመ ትምህርት ፈተናው (34.75) ድህረ ትምህርት ፈተናው (36.23) ቢሆንም በውጤቶቹ መካከል በቲ-ቴስት ስሌቱ መሠረት ጉልህ የሆነ ልዩነት አልተመዘገበም። ነገር ግን አንዳንድ ተማሪዎች የቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናው ይዘት ተመሳሳይ በመሆኑና ከቅድመ ትምህርቱ ፈተና ያገኙት ተሞክሮ ስላገዛቸው፤ በድህረ ትምህርት ፈተናው ውጤት መጠነኛ መሻሻል ታይቷል። ይህም ማንበብና መፃፍን ከትስስራቸው አንፃር በውህደት ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ ጠቀሜታ እንዳለው ፍንጭ ሰጥቷል።
- የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በተዘጋጀው መማሪያ የተማረው የሙከራ ቡድኑ ባስመዘገበው (62.11) ውጤትና ክሂሎቹን በተናጠል ሲማር ከቆየው የጥብቅ ቡድኑ ባስመዘገበው (36.23) መሠረት ከፍተኛ የሆነ ውጤት አስመዝግቧል። በመሆኑም ክሂሎቹን በውህደት ማስተማር ውጤታማ እንደሆነና የዘርፉ ተመራማሪዎች ያቀረቡት ጽንሰ ሃሳብም ትክክል እንደሆነ መረዳት ተችሏል። ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ክሂሎቹን በውህደት የተማሩት ተማሪዎች አንብቦ በመረዳትና በመፃፍ ችሎታቸው በከፍተኛ ደረጃ መሻሻል አሳይቷል። ልዩነቱም ጉልህና አስተማማኝ መሆኑ በልዩነት ማሳያ ስሌቱ መሠረት የረጋገጧል። ስለዚህ ክሂሎቹን በውህደት ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነና ጠቀሜታም የጎላ ነው በሚል መደምደም ይቻላል።
- በአጠቃላይ የሙከራ ቡድኑ ከጥብቅ ቡድኑ የተሻለ ውጤት ማስመዝገቡ ለጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄ አወንታዊ መልስ አስገኝቷል ማለት ይቻላል። ምክንያቱም መሠረታዊ ጥያቄ አወንታዊ መልስ አስገኝቷል ማለት ይቻላል። ምክንያቱም

## 5.3 አስተያየት

ጥናቱ ያስገኛቸውን ውጤቶች መሠረት በማድረግ አጥኝው የሚከተሉት የመፍትሔ አስተያየቶች አቅርቧል።

- የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ከትስስራቸው አንፃር በውህደት ከቀረቡ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ ይህ ጥናት አሳይቷል። ስለሆነም ማንበብና መፃፍን በውህደት ማስተማር ትኩረት ተሰጥቶት ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ ልምምዱን እንዲያደርጉ ቢበረታቱ።
- የተማሪዎች አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታ በወኑ ይዳብር ዘንድ በአንድ የክፍል ደረጃ የሚደረገው ልምምድ /ትግበራ/ በቂ አይደለም። ተማሪዎቹ ከ1ኛ ደረጃ ትምህርት ጀምሮ ክሂሎቹን በውህደት የሚማሩበት ሁኔታ መፈጠር ያለበት ስለሆነ፤ ባለድርሻ አካላት ትኩረት ሰጥተው መፍትሄ ቢሰጡት መልካም ነው።
- የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች በውህደት ከቀረቡ ሁሉንም ተማሪዎች ጥሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ፣ በተመሳሳይ ጊዜ ከአንድ ክሂል በላይ እንዲለማመዱ ያደርጋል። በመሆኑም ተማሪዎች በልምምድ ትምህርቱ የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን ጥናቱ አረጋግጧል። ስለዚህ ክሂሎቹ በውህ ደት ቢቀርቡ።
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች በውህደት ሲያስተምሩ ተማሪዎቻቸውን በግል፣ በጥንድና በቡድን በመከፋፈል የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይኸውም ተማሪዎችን እንዲያንጸባርቁ እንዲያከናውኑ ማድረግ፣ ተገቢውን ዝግጅትና ክትትል በማድረግ፣ የተማሪዎችን ተሳታፊነት በማሳደግ፣ ክሂሎቹን የሚያጎለብቱበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል። በማሳደግ፣ ክሂሎቹን የሚያጎለብቱበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ አንፃር እየተሰራበት ያለው የመማር ማስተማር መንገድ ቢፈተሽና እንዲታረም ቢደረግ።
- ተመራማሪዎች በዚህ ርዕስ ላይ በስፋት ቢያጠኑ ለአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች፣ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ብሎም ለቋንቋው ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ አጥኝው ያምናል።

# ዋቢዎች

ሀዲስ ዓለማየሁ (1960)። *ፍቅር እስከ መቃብር*። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ለማ ንጋቱ (1994)። "የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ትስስር አላቸውን?" *መጽሔተ ትምህርት*። ቅፅ 6 ቁጥር 13፡ አዲስ አበባ። በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት።

መንግስቱ ለማ (1953)። *ጠልፎ በኪሴ*። አዲስ አበባ፣ ብረሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ማረው ዓለሙ (1998)። *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ*። ባህር ዳር፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ሞገስ አመራ (1999)። የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በመጎልበት ረገድ ያለው ሚና። (ያልታተመ) ለሁለተኛ ድግሪ መመረቂያ የቀረበ ጥናት። ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ።

ሺበሽ ለማ (1958)። *ተጠየቅ*። አዲስ አበባ፣ ብረሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

በድሉ ዋቅጅራ (1996)። *በስነ-ጽሑፍ ቋንቋ ማስተማር*። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ተስፋዬ ሸዋዬ (1986)። *አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር*። አዲስ አበባ፣ በትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት።

ትምህርት ሚኒስቴር (1997)። *አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ 9ኛ ክፍል*። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

________ (1997)። *አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ 10ኛ ክፍል*። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ከበደ ሚካኤል (1999)። *ታሪክና ምሳሌ፣ አንደኛ መጽሐፍ*። (ሁለተኛ እትም)። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

አለም እሸቱ (1998)። *የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ*። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

አሳምረው ገብረማሪያም (2002)። *መሠረታዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ አጋዥ መጽሐፍ*። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

አበራ ለማ (1980)። *የማለዳ ስንቅ*። አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

አበበች ተስፋዬ (2002)። አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ መማር ማስተማር ክሂሎቹን በማዳበር ረገድ ያለው ፋይዳ። (ያልታተመ) የድህረ ምረቃ ቴሲስ። ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።

እንክሲቲ መኮንን (1998)። የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ዘዴ አተገባበር ፍተሻ በአዲስ አበባ አስተዳደር በሚገኙ ሦስት ትምህርት ቤቶች። (ያልታተመ) ለሁለተኛ ድግሪ መመረቂያ የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ያለው እንዳወቀ (1998)። *የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር።* አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች።

ደበበ ኃይለጊዮርጊስ (1998)። *ዘመናዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ።* አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት።

ዘውዱ ናሁሰናይ (2001)። በአማርኛ ቋንቋ የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በተረቶች አማካይነት ማስተማር ክሂሎችን ለማዳበር ያለው ሚና። (ያልታተመ) የድህረ ምረቃ ቴሲስ። ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።

Airasian, W. Peter (1997). *Class room Assessment.* Newyork: The Mc Graw- Hill companyies.

Aulls, M.W. (1985). Understanding the Relationship Between Reading and Writing. *Educational Horizons, 64* (10), 39-44.

Barrs, Myra (2000). The Reader in the Writer. *Reading* (United Kingdom Reading Association), July, 54-60.

Beerdgew (2003). *"Reading-writing connection in the class-room"* (http://www. edu/ library/CAGS-project/LTHOMSON/ web % 20 page/r-w % 20 class-room htm.)

Block, Cathy Colling (1997). *Teaching the language arts: Expanding thinking student centered instruction.* Bastone: Allyn and Bacon.

Block C. and Mangieri, J. (1995). *Reason to Read; Thinking strategies for life through literature,* volumes 1-3. Menlo park, CA: Addion.

Boutwell, M. (1983) Reading and Writing Process: A Reciprocal Agreement. Language *Arts, 60* (6), 723-730.

Cole, G.Peter and Chan, K.S. (1997). *Teaching principles and practices.* New york: Prentice Hall.

Conley, Mark W. (1997). *Reading and writing: teaching for the connection* (2nd ed.). Less har court Brache and company.

Gary, Cobine (1995). *"writing as a response to reading."* (http://www. Vtaide.com./ pnp/ERIC/Write-read.htm.)

Harp, Bill and Brewry, Johnn (1996). *Reading and Writing Teaching for the connection.* (2nd ed.). S.A: Har court brace and company.

Heaton, J.B. (1990). *Class Room Testing.* London; Longman.

Kennedey, Barbara C. (1994). *"The role of topic and the reading writing connection."* (http//www. Writing. Edu. /TESC Ej/ej01/a.3.him.)

Koul, L. (1996). *Methodotogy of Educational Research.* (2nd ed.). Uiks Publishing House Pvt. Ltd.

Langer, Judith and Flihan, Sheial. (2000). "New York; international Reading Asociation."

May, Frank B. (1990). *Reading as Communication.* New York: Macmillan pudlishing company.

Mayo, L. (2000). Making the Connection: Reading and Writing Together. English Journal, 89 (4), 74-77.

Ramonda, R. (1997). *Read, write, react:* An integrated approach to reading and writing. New York: McGraw-Hill. (http://www.nade.net/documents/ SCP98/SCP98 .8.pdf)

Ruddel, Martha Rapp (1997). *Teaching Content Reading and Writing.* (2nd ed.). U.S.A: Allyn and Bacon.

Shanahan, T. & Lomax, R.G. (1988). A Developmental Comparison of Three Theoretical Models of the Reading-Writing Relationship. *Research in the Teaching of English, 22* (2), 196-212.

Smith, F. (1983). *Reading Like a Writer.* Language Arts, 60 (5), 558-567.

Smith, C. B., & Dahl, K. L (1984). *Teaching Reading and Writing Together: The Classroom Connection.* NY: Teachers College Press.

Smith, L. (1997). Creating an integrated language development program. *Journal of College Reading and Learning,* 27, 167-173. (http://www.nade.net/ docum ents/ SCP98/SCP98.8.pdf)

Squire, J. (1984). *"Composing and Comprehending: two sides of the same dasic process"* in composing and comprehending J.J. Jensen (ed) ERIC clearing house on Reading and Communication Skills.

Unrau, Norman (2004). *Content Area Reading and Writing Fostering Literacy. Middle and High School Culture.*USA: Merill prentice Hall.

Williams, (1984). *Reading in the Language classroom.* London: Macmillan Publishers.

# አባሪ አንድ

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር የቋንቋዎች ጥናት ፋኩሊቲ ለተግባራዊ ስነ ልሳን የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ትምህርት ክፍል ማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት ለቀረበ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ**

በሙከራና በጥብቅ ቡድን ለተካተቱ የ10ኛ "E" እና የ10ኛ "H" ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ ቅድመ ትምህርት ፈተና።

*መለያ ኮድ ------------------ ክፍልና ሴክሽን ----------------------*

***አጠቃላይ መመሪያ፡-*** የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ ሲባል ለተደረገ ሙከራዊ ጥናት መረጃ ማስገኘት ነው። ቡድኖቹ ክሂሎቹን በውህደት ምንም ሳይማሩ የማንዛቤ ደረጃቸውና ችሎታቸው ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ቅድመ ትምህርት ፈተናው ተዘጋጅቷል። ከዚህ አንፃር ይህ ፈተና ሦስት ክፍሎች አሉት። የእያንዳንዱን ክፍል መመሪያ በጥንቃቄ ካነበቡ በኋላ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በጽሑፍ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ጥያቄዎችን ለመስራት የተፈቀደው ጊዜ 1:30 ሰዓት ሲሆን፣ አጠቃላይ 100 ነጥብ ይይዛል።

*ክፍል አንድ፡- ቀጥሎ ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቀው የተቀመጡትን ዓረፍተ ነገሮች እንደያዙት ሃሳብ በቅደም ተከተል በማስተካከል "ታማኝነት ከሁሉ ይበልጣል" የሚል ርዕስ አንድ የተሟላ ተረት አድርጋችሁ ፃፉ። ለእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር በትክክለኛው ቦታ ተስተካክሎ መፃፍ ሁለት ነጥብ በመስጠት፣ ከመቶው ሃያ ድርሻ ይኖረዋል።*

1. ንጉሱም ግምጃ ቤቱን አስቀርቦ እንዲህ አለው::
2. አንድ ቀን አንድ እባብ ባልተከደነ ጠርሙስ ውስጥ ገብቶ ወተቱን ጨልጦ ጠጣው::
3. ተቆጣጣሪውም መዝገቡን አምጥቶ የሰረቀውን ገንዘብ ለንጉሱ አስረዳው::
4. ወተቱን ከጠጣ በኋላ ከጠርሙሱ ለመውጣት ቢሞክር ሰውነቱ ወፍሮ አላስወጣው አለ::
5. ሰውየው እንደወጣ ንጉሱ ተቆጣጣሪ ሆኖ የሚሰራውን ሰው ይህ ግምጃ ቤት ሥራውን ይልቀቅ ወይ ብሎ ጠየቀው::
6. እንዳንተ አስተያየት እባቡ ከጠርሙሱ ለመውጣት ምን ማድረግ አለበት? ብሎ ጠየቀው::
7. ከንጉሱ ዘንድ ቀርቦ ከእንግዲህ ወዲህ እየነገድሁ ለመኖር ስላሰብኩ ግርማዊነትዎ ቢፈቅዱልኝና ቢያሰናብቱኝ ብሎ ጠየቀ::
8. የጠጣውን ወተት መልሶ ከተፋው በኋላ ሰውነቱ ስለሚቀጥን በቀላሉ ያስወጣዋል ብሎ ግምጃ ቤቱ መለሰ::
9. የንጉስ ግምጃ ቤት ሆኖ ያገለግል የነበረ አንድ ሰው የንጉሱን ገንዘብ እየሰረቀ ብዙ ሃብት አጠራቅሞ ከበረ::
10. ንጉሱም ያንተም ነገር እንዲሁ ያለ ነው አለው:: (ከበደ ሚካኤል፣ 1999 2ኛ መጽሐፍ የተሻሻለ?

ታማኝነት ከሁሉ ይበልጣል

--------------------------------------------------------------------------------

*ክፍል ሁለት፡- 2.1 ቀጥሎ የቀረቡትን ሁለት ጥያቄዎች ምንባቡን ማንበብ ከመጀመራችሁ በፊት ለመልሳችሁ ምክንያት በመስጠት አብራርታችሁ ፃፉ (ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች)፤ ከመቶው አሥር ድርሻ ይኖረዋል።*

1. አንድ ሰው በሌሊት በብቸኝነት በጫካ ውስጥ ዛፍ ስር በማደሩ/ሯ ምክንያት ምን ሊያጋጥመው እንደሚችል ዘርዝራችሁ ፃፉ?--------------------

2. ሰዎች ያልጠበቋቸው ችግሮች በሚያጋጥሟቸው ጊዜ ምን ዓይነት ስሜት ይፈጠርባቸዋል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ለምን? ---------------------------------------

*2.2 በምንባቡ መካከል የሚቀርቡትን የሂደት ጥያቄዎች የምንባቡን ቀጣይ ታሪክ ከቀደመ ልምድና ከታሪኩ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት የምትመልሱት ነው:: ከጥያቄው ቀጥሎ ያለውን ምንባብ ጥያቄዎችን ሳትሰሩ የምንባቡን ቀጣይ ክፍል ማንበብ ክልክል ነው:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ መስጠት አራት ነጥብ በመስጠት በአጠቃላይ ከመቶው አርባ አራት ድርሻ ይኖረዋል::*

ምንባብ

(1) "አምላኬ እባክህ ጠብቀኝ የምህረት መላክተኛህን ላክልኝ!" አሉና መልካ እየሱስ ለመድገም "ለዝክረ ስምከ" ሲሉ በፊታቸው ሃያ ሜትር ያክል ራቅ ብላ የነበረች ትንሽ ቁጥቋጦ ከብዳ ታዩቻቸው:: ወዲያው መልካ እየሱሳቸውን አቋርጠው ዓይኖቻቸውን አሻሹና እንደገና ቢገልጡ ያ እቁጥቋጦው ውስጥ ከብዶ የታያቸው ነገር የሚንቀሳቀስ መሰላቸው:: እንደገና አስተውለው ሲመለከቱ አንድ ወይም ሁለት ርምጃ ወደፊት እየተራመደ ቀረብ ሲል ካናት እስከ ጅራቱ ጥርት ብሎ ታያቸው::

ጥያቄ 3. እቁጥቋጦው ውስጥ ከብዶ የታያቸው ነገር ቀረብ ሲል ከአናት እስከ ጅራቱ ጥርት ብሎ ያዩት ነገር ምን ሊሆን ይችላል? ለግምታችሁ ምክንያታችሁ ምንድን ነው? ---------------------------------------

(2) እግዚአብሔር መላከ ምህረቱን እንዲልክላቸው ቢለምኑት ያለመኑትን መላክ መቅሰፍቱን ላከላቸው:: "ነብር!..." አሉ አባ ዓለም ለምኔ ቀስ ብለው:: ከዚያ በሁዋላ እንደበታቸው ታሰረ:: ልባቸው እንደተቃጠለ ሻማ ቀልጦ በውስጣቸው የፈሰሰ መሰላቸው:: ሙሉ አካላቸው ቆርጦ ለፀሀይ እንደ ሰጡት ለጋ ተክል ዛለ:: አእምሮዋቸው ድንዝዝ አለ:: ዓይኖቻቸው እንቅልፍ እንደ ከበዳቸው ሲስለመለሙ አንዱ ነብር ሁለት እዩሆነ ይታያቸው ጀመር:: ለመጮህ እዩሞከሩ የሚበቃ ትንፋሽ አጡ::

ጥያቄ 4. በአባ ዓለም ለምኔ ላይ የደረሰው ዓይነት ችግር ቢያጋጥማችሁ ምን ዓይነት የመፍትሄ እርምጃ ትወስዱ ነበር? ---------------------------------------

(3) ነብሩ እንዲህ ቀስ እያለ ተጉዞ አባ ዓለም ለምኔ አሉበት ለመድረስ ትንሽ ሲቀረው ቆም ብሎ እያጉረመረመ እሳቸውን ትንሽ ተመለከተና ከዚያ ዓይኖቹን ወደ ወንዝዋ አተኩሮ ይመለከት ጀመር። መነኩሴውም የመጀመሪያው የፍርሃት ስመመን እንደ ማለፍ ብሎላቸው አእምሮዋቸውን መግዛት ሲጀምሩ ዓይኖቻቸውን ሲፈሩ ሲችሩ ገለጥ አደረጉ። ነብሩ ሽንጡን ለሳቸው ሰጥቶ ፊቱን ወደ ወንዝዋ አዙሮ እየተመለከተ ጅራቱን በቀስታ ከወዲያ ወዲህ ሲያወዛውዝ አዩ። ቀስ ብለው ነብሩ ወደሚመለ ከትበት ዓይኖቻቸውን ቢልኩ ከወንዝዋ ወዲህ ማዶ የሳር ክምር በራሱ ላይ የተሸከመ የሚመስል ነገር ቆሞ አዩ።

ጥያቄ 5. ነብሩ እያጉረመረመ አባ ዓለም ለምኔን የሚጠጋቸው ምን ፈልጎ ይመስላ ችኋል? እንዴ አወቃችሁ? ------------------------------------------------

ጥያቄ 6. ከወንዝዋ ወዲህ ማዶ የሳር ክምር በራሱ ላይ የተሸከመ የሚመስል ነገር ቆሞ ያዩት ምን ይምስላችኋል? ለግመታችሁ ምክንያታችሁ ምንድ? --------

(4) ምንም እንኳ ያንበሳን ስም እንጂ መልኩን አይተው ባያውቁም እንዲሁ በግምት አዲስ መጪው እሱ መሆኑን አወቁ። ሁለቱ ነበዞች ሃያ ሜትር ያክል በሚሆን ርቀት ቆመው ትንሽ ከተፋጠጡ በኋላ አንበሳ ቀስ እያለ አንድ ወይም ሁለት እርምጃ ወደፊት ሲራመድ ነብር ያኑ ያክል ወደ ኋላ ማፈግፈግ ጀመረ። እንዲህ እያሉ አባ ዓለም ለምኔ ካሉበት ዛፍ ሥር ተጠጉ።

ጥያቄ 7. እንደ አባ ዓለም ለምኔ በሁለት ኃይለኛ አራዊቶች ብትከበቡ ምን ዓይነት እርምጃ ትወስዳላችሁ? ለምን? ------------------------------------------------

ጥያቄ 8. ከአንበሳና ከነብር ማን ያሸንፋል? ምክንያታችሁ ምንድን ነው? ---------------

(5) አባ ዓለም ለምኔ ያ እንደ ተቃጠለ ሻማ ቀልጦ የፈሰሰ ልባቸው ሀይሉን እንዴት እንዳጠራቀመ እኒያ ከተዘረጉበት ለማጠፍ አስቸግሯቸው የነበሩ እግሮቻቸው እንዴት ተነስተው እንደቆሙ ሳይታወቃቸው እንደ ብርቱ እንደ ጤናማ ሮጠው እዛፉ ላይ ለመውጣት ቢሞክሩ ግንዱ ወፍሮ መታቀፍ ስላልቻሉና ያበጡ እግሮቻቸው መቆንጠጥ ስላቃታቸው ተንሸራተው ወደቁ። እንደገና ለመውጣት ሲሞክሩ ተመልሰው ሲወድቁ ዛፉ ከላጠውና ጋሬጣ ከወጋው እግራቸው እዚያ ወርካ ስር የፈሰሰው ደም ሲታይ በደም ስራቸው አንድ ጠብታ ደም የቀረ አይመስልም ነበር። በመጨረሻ ተስፋ ቆርጠው ማልቀስ ጀመሩ።

ጥያቄ 9. የአንበሳውና ነብሩ ፍጥጫ ለአባ ዓለም ለምኔ መፍትሄ ያመጣል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ምክንያታችሁን በመግለጽ ፃፉ? ------------------------------

ጥያቄ 10. አባ ዓልም ለምኔ ተስፋ ቆርጠው ማልቀስ ጀምረዋል። እናንተ ብትሆኑ ከአደጋው ለማምለጥ ምን ትሰሩ ነበር? ------------------------------

(6) አንዷት ከትልቁ ዋርካ አጠገብ ለብቻዋ በቅላ እላይ ከትልቁ ዋርካ ቅርንጫፎች ጋር የተገናኘች ቀጭን ዛፍ አዩ። ወዲያው እየሮጡ ሄዱና እስዋን አቅፈው በልባቸው እየተሳቡ ወጥተው ከዋርካው ቅርንጫፎች መካከል ተጣብቀው ተቀመጡ።

ጥያቄ 11. አባ ዓለም ለምኔ ከዋርካው ላይ በመውጣታቸው ከአንበሳው መበላት ማምለጥ ቢችሉ ከነብሩ መበላት ማምለጥ ይችላሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ? ለምን? ------------------------------

ጥያቄ 12. በታሪኩ መሠረት ስለ አባ ዓለም ለምኔ የኑሮ ሁኔታ ምን ተገነዘባችሁ?------

(7) አንበሳው ዋርካው ስር የፈሰሰው ደምና ጠረናቸው ሲሸተው እዚያ ግድም መሆናቸውን እያወቀ ፈልጎ ስላጣቸው በብርቱ ጉምጅትና ቁጣ እያገሳ መሬቱን ሲልጥ፣ ደንጊያውን ሲፈነቅል፣ ቁጥቋጦውን ሲጥስ፣ ልባቸው ራደ። እንዳላመለጡት ሲረዱ ተስፋ በመቁረጥ ስቅስቅ ብለው ማልቀስ ጀመሩ። (ሀዲስ ዓለማየሁ 1960)

ጥያቄ 13. ከመጨረሻው አንቀፅ የድርጊት ሁኔታ በመነሳት የአባ ዓለም ለምኔ ፍፃሜ ምን ሊሆን ይችላል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ------------------------------

*2.3 ቀጥሎ የሚቀርቡት ጥያቄዎች ቀደም ሲል ካነበባችሁት ምንባብ ተመስርተው የወጡ ናቸው፣ ስለዚህ ጥያቄዎቹን ስትመልሱ፡-*

*ሀ/ ከጽሑፉ በቀጥታ የሰፈረን ሃሳብ መሠረት በማድረግ፣*

*ለ/ ከቀደመ ልምድና ዕውቀት በመነሳት የሚመለሱ ናቸው፣ (ድህረ-ንባብ ጥያቄዎች)፣ ከመቶው አሥር ድርሻ ይኖረዋል።*

14. የጽሑፉን አብይ ጭብጥ በራሳችሁ አገላለጽ በአጭሩ ፃፉ? ------------------------------

15. እጅግ በጣም የምትወዱትን ወይም የምታፈቅሩትን ሰው አስቡና እንዲኖረው የምትፈልጉትን ተፈላጊ ወይም ጥሩ ባህሪያት በቃላት ብቻ በመዘርዘር በተፈላጊነት ቅደም ተከተላቸው መሠረት ዘርዝራችሁ ፃፉ? ------------------------------------

*ክፍል ሦስት፡- ቀጥሎ የቀረበውን የክስ መግለጫ ካነበባችሁ በኋላ ራሳችሁን እንደ ተከሳሳችሁ መበቁጠር፤ ነገር ግን ተፈጸመ የተባለውን ጥፋት ያልፈጸማችሁት መሆናችሁን በመግለጽ ለወላጅ መምህር ህብረት ኮሚቴው መልሳችሁን በማመልከቻ ፃፉ፣ ከመቶው አሥራ ስድስት ድርሻ ይኖረዋል።*

ቁጥር ወመህ/2/11/2003

ቀን 18/01/2003

ለተማሪ.....................................................................

የ10ኛ ክፍል ተማሪ

ወረታ

ጉዳዩ፡- <u>በከባድ የዲሲኘሊን ጥፋት የተከሰሱ መሆኑን ስለማሳወቅ</u>

የወረታ አጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተዳደር እርስዎን ግዴታዎን ባለመወጣትና ሥነ ሥርዓት ባለማክበር ሲከስ፡-

- በቅድሚያ ጥፋቱን ተረድቶ እንዲፀፀት ዕድሉ ተሰጥቶታል።
- ጥፋቱን ለወላጅ በማሳወቅ በማረም እንዲተባበሩ ተደርጓል።
- በትምህርት ቤቱ አስተዳደር በኩል ተግሳጽና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታል።

በትምህርት ቤቱ አስተዳደር በኩል ተግሳጽና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶታል። ከዚህ አልፎ መምህር ለመደብደብ ሙከራ በማድረጉ ምክንያት የወላጅ መምህር ህብረት ኮሚቴው ጉዳዩን መርምሮ በትምህርት ቤቱ ህግና ደንብ መሠረት አስፈላጊውን ውሳኔ እንዲሰጥ ትምህርት ቤቱ ጠይቋል።

ስለዚህ የፈጸምከው የዲሲኘሊን ጉድለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የትምህርት አመራር፣ አደረጃጀት፣ የሕብረተሰብ ተሳትፎና የፋይናንስ መመሪያ ላይ ግዴታቸውን በማይወጡና ሥነ-ሥርዓት በማያከብሩ ተማሪዎች ላይ የሚወሰደውን የዲስኘሊን እርምጃ መሠረት በማድረግ፣ አንተ የተከሰስህበት ጥፋት ጠባዩን አስተካክሎ

የትምህርት ቤቱ ጤናማ አባል ሊሆን እስኪችል ድረስ ከትምህርት ቤቱ ለአንድ ዓመት ይገለላል ይላል፡፡

በዚህ መመሪያ መሠረት የተፈጸመው ጥፋት በከባድ የዲሲኘሊን ቅጣት የሚያስከስስ በመሆኑን ተረድተህ፤ የትምህርት ቤቱ የወላጅ መምህር ህብረት ኮሚቴ ጉዳዩን አጣርቶ ውሳኔ ለመስጠት ይችል ዘንድ መልስህን ጽፈህ በ28/01/2003 ዓ.ም ለኮሚቴው በሀፊ እንድታቀርብ የትምህርት ቤቱ የወላጅ መምህር ህብረት አዟል፡፡
(ከትምህርት ቤቱ የወላጅ መምህር ህብረት ኮሚቴ የተገኘ 2003)

60

---

---

# አባሪ ሁለት

## በሙከራና በጥብቅ ቡድን ለተካተቱ የ10ኛ "H" እና የ10ኛ "E" ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የድህረ ትምህርት ፈተና።

*መለያ ኮድ* ------------------ *ክፍልና ሴክሽን* ---------------------

***አጠቃላይ መመሪያ፦*** የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ ታስቦ ለተደረገው ሙከራዊ ጥናት መረጃ ማስገኘት ነው። ሁለቱም ክፍሎች በተለያየ መንገድ ለአንድ ወር የተማሩት ትምህርት ምን ያህል የባህሪይ ለውጥ እንዳስገኘና ልዩነታቸው በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለመገምገም እንዲቻል የድህረ ትምህርት ፈተናው ተዘጋጅቷል። ከዚህ አንፃር ይህ ፈተና ሦስት ክፍሎች አሉት። የእያንዳንዱን ክፍል መመሪያ በጥንቃቄ ካነበቡ በኋላ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በጽሑፍ ይስጣሉ። ጥያቄዎችን ለመስራት የተፈቀደው ጊዜ 1:30 ሰዓት ሲሆን፣ አጠቃላይ 100 ነጥብ ይይዛል።

***ክፍል አንድ፦*** *ቀጥሎ የቀረበውን አጭር ታሪክ አንብቡና ለችግሩ መፍትሄ ነው የምትሉትን ሃሳብ ምክንያታችሁን በመግለጽ አብራርታችሁ ፃፉ። ከመቶው አሥራ አንድ ድርሻ ይኖረዋል።*

አንዲት በግ አንድ ትልቅ ወንዝ በመሻገር ላይ እያለች ከወንዙ የወጣ አዞ ይይዛታል። በዚህ ጊዜ ከወንዙ ዳር ከነበሩት ሦስት ሰዎች መካከል አንደኛው ዋሽንት መንፋት ሲጀምር አዞው በዋሽንቱ ፈዞና ተመስጦ በጓን ለቀቃት። ወዲያው ሁለተኛው ሰው አነጣጥሮ በመተኮስ አዞውን ገደለው። ሦስተኛው ሰው ደግሞ ዋናተኛ ኖሮ በጓን ዋኝቶ ከወንዙ አወጣት። ከዚህ በኋላ ሦስቱ ሰዎች የይገባኛል ጥያቄ በማንሳት ተከራከሩ። ሁሉም በጓን ለማዳን የእኔ አስተዋጽኦ ይበልጣል በሚል ለመስማማት አልቻሉም። ስለዚህ በጓ የማን ትሁን? (ማረው ዓለሙ 1998) ------------------------------------------

*ክፍል ሁለት፡- 2.1 ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን ማንበብ ከመጀመራችሁ በፊት ለመልሳችሁ ምክንያት በመስጠት ፃፉ (ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች)። ከመቶው አሥር ድርሻ ይኖረዋል።*

1. በደል የደረሰባቸው ግለሰቦች ለሚያቀርቡት አቤቱታ ወይም ክስ በወቅቱ ምላሽ ላለማግኘታቸው በምክንያትነት የሚጠቀሱ ጉዳዮች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ? ዘርዝራችሁ ፃፉ? ------------------------------------------------------------
2. እነዚህ ግለሰቦች ተገቢ ምላሽ ባለማግኘታቸው ምን ስሜት ሊያድርባቸው ይችላል? -
------------------------------------------------------------------------

*2.2 በምንባቡ መካከል ተካተው የቀረቡትን የሂደት ጥያቄዎች የድርጊቱን ቀጣይ ክስተት ከቀደመ ልምድና ከታሪኩ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት የሚመለሱ ናቸው። ከጥያቄው ቀጥሎ ያለውን ምንባብ ጥያቄዎችን ሳትሰሩ ቀጣዩን ምንባብ ማንበብ ክልክል ነው። እያንዳንዱ ጥያቄ አራት ነጥብ የሚይዝ ሲሆን፤ ከመቶው አርባ አራት ድርሻ ይኖረዋል።*

## ምንባብ

(1) ጥልቅ ሀሳብ የገባቸው አባ አንቀርሻው ያለአግባብ የማመልከቻ ጸሐፊው የወሰደባቸው ተጨማሪ አንድ ብር ቁጭት እያብከነከናቸው ከጸሐፊው ቢሮ ወጡ። ቀጥለው ምን ማድረግ እዳለባቸው እያንሰላሰሉ የየጁ አውራጃ ፖሊስ አዛዥ ቢሮ ወደሚገኝበት ግቢ አዘገሙ።

ጥያቄ 3. አባ አንቀርሻው ወደ ፖሊስ አዛዡ ቢሮ የሄዱት ማንን ሊከሱ ይመስላችኋል? በምን አወቃችሁ? ------------------------------------------------

(2) "ይህን ሁሉ ወረቀት ይዤ ወደ አዛዡ ቀርቤ በቃል ጭምር ባስረዳ አይቀበሉኝ ይሆን? መከራ በልቼ ያሳደኳት አንዷ ምርኩዜ ክብሯ ተደፍሮ፣ ስትሞትና ወድቃ ስትቀር እኔም ያለሟሪ ስዋትት ዳኛ የለም ባገሩ?" እያሉ ራሳቸውን አጥብቀው ይጠይቃሉ።

ጥያቄ 4. አባ አንቀርሻው ክሳቸውን የፖሊስ አዛዡ ላይቀበላቸው እንደሚችል የተጠራጠሩት ለምን ይመስላችኋል? ------------------------------------------------

ጥያቄ 5. አባ አንቀርሻው ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ ምንድን ነው? ----------------------------

(3) ወደ ፖሊስ አዛዡ ቢሮ ሲያመሩ ሽንጡ ላይ ሽጉጥ ያገነደረ ረዥም ደረተ ሰፊ ፖሊስ ገላመጣቸው:: ችግራቸውን ሊያስረዱት ቢሞክሩም ሊያዳምጣቸው ፈቃደኛ አልሆነም:: ከልክሎ ደግሞ አልከለከላቸውም:: እጅ እጃቸውን ያያል። ምንም የማይወጣቸው መናጢ ድሃ መሆናቸውን ሲያውቅ ግን ተጠይፏቸው ከአጠገባቸው ዞር አለ::

ጥያቄ 6. ፖሊሱ ከአባ አንቀርሻው ምን ፈልጓል? እንዴ አወቃችሁ? -----------------

ጥያቄ 7. አባ አንቀርሻው ፖሊስ አዛዡ ቢሮ ሲገቡ ጥሩ የባለጉዳይ አቀባበል የሚጠብቃቸው ይመስላችኋል? ለምን? ------------------------------------------------

(4) አባ አንቀርሻው ጣደፍ ጣደፍ እያሉ ወደ ፖሊስ አዛዡ ቢሮ ተጠጉ:: ዘንጋቸውን አስተካክለው አስቀመጡ:: የተበተነ ጋቢያቸውን በባለጉዳይ ደንብ አጣፍተው በልቦናቸው ፈጣሪያቸውን ተማጸኑ:: የቢሮውን በር ገፋ አድርገው ገቡና ለጥ ብለው ወለሉን ሳሙት:: በፍርሃት የሚብረከረከው ጉልበታቸው ሊከዳቸው ተቃረበ::

ጥያቄ 8. "ለጥ ብለው ወለሉን ሳሙት" የሚለው አገላለጽ ይህ ጽሑፍ የተፃፈበት ዘመን የፍትህ ሥርዓቱ ምንን ይጠቁማል? ------------------------------------------------

(5) ከፊት ለፊታቸው ፊቱን የሐምሌ ደመና አስመስሎ የሚመለከታቸው የፖሊስ አዛዥ ሻለቃ ደግሞ በአግራሞት አስተዋላቸው:: እንደአባ አንቀርሻው ዓይነት ጎስቋላ ሰው ጋር በቢሮው ሲያስተናግድ የመጀመሪያው የሆነበት ይመስላል። ከላይ እስከ ታች መዘናቸው:: በላብ የራሰ ማጅራቱን በመሀረሙ እየጠረገ ሲቃኛቸው አባ አንቀርሻው እጃቸውን የኋሊት አጣምረው አቀረቀሩ:: ምን ነበር! ብሎ አንባረቀባቸው:: ሻለቃው ግራ እጁን አገጩ ላይ አስደግፎ ያስተውላቸው ጀመር:: ግራ እጁ ጣቶች ላይ የተደረደሩት የወርቅ ቀለበቶች ዓይን ይስባሉ::

ጥያቄ 9. ጎስቋላ ሰው በቢሮው ማስተናገድ የማይፈልግ የቢሮ ኃላፊ ትክክል ነው ወይስ አይደለም? ለምን?------------------------------------------------

ጥያቄ 10. አባ አንቀርሻው አቤቱታቸው ፍትሃዊ ምላሽ ያገኛል ብላችሁ ትገምታላ ችሁ? እንዴት አወቃችሁ? ------------------------------------------------

(6) በአክብሮትና በፍርሃት መላ ሰውነታቸው የታመሰባቸው ባለጉዳይ አሮጌ ጋቢያቸውን ገለጥለጥ አድርገው ከብብታቸው ስር ዶሴያቸውን መዘው አቀበሉት:: ክላሰሩ አዲስ ነው:: ወረቀቶቹ ግን በላበት ጠቁረዋል:: ከመላሽቃቸው የተነሳም ሦስት አራቱ እንደ ነባበሮ የተጣበቁ በመሆናቸው ማላቀቁ ፈተና ሆነበት ለሻለቃው::

ጥያቄ 11. በታሪኩ መሠረት ስለ አባ አንቀርሻው ምን ተገነዘባችሁ? ------------------

(7) ፖሊስ አዛገፉ የተቀበለውን ዶሴ ገለጥ ሲያደርግ የሆነ ጠረን አፍንጫውን ሳይተነፍገው አልቀረም ከፉኛ አስነጠሰው:: መሀረሙን አውጥቶ ፊቱ ላይ እያራገበና እየተጠየፈ በሁለት ጣቶቹ ገልበጥበጥ አደረገው:: የሚያነብ ለመምሰል ያህል:: ከዚያ ቀና ብሎ አያቸውና ምን ነበር ጉዳዮት አላቸው እንደገና:: አይ ጌታየ ምኑ ተነግሮ ያልቃል ... ነገሬ ብርቱ ነው፤ አሉትና ዝም አሉ:: ክላሰሩን አጥፎ ከፊት ለፊቱ ገፋ በማድረግ ጊዜ የለኝም ጉዳዮትን በአጭሩ ይገለጹልኝ አላቸው ፊቱን ወደ ጎን እያዞረ::

ጥያቄ 12. በዚህ ምንባብ ውስጥ የጸሐፊው መሠረታዊ መልዕክት ወይም ጭብጥ ምንድን ነው? ------------------------------------------------

(8) ክስ ነው ጌታየ ...
ምነን ነው የከሰሱት?
አይ! ጌታየ ዶሴየ ይናገራል:: እኔ ሳወራው ውየ ሳወራው ባድር የሚያልቅ አይደለም አሉት አባ አንቀርሻው በደፈናው:: ይህን ዶሴ ገና አንብቤ! አላቸው ሻለቃው ዶሴያቸውን በጥላቻ ዓይን እየተመለከተ:: ጉዳዮትን እንድረዳልዎ ካሰቡ በቃል አሳጥረው ይነገሩኝ፣ ካልሆነ የማይሆን ነው:: ጊዜ የለኝም ብየዎታለሁ እኮ!
... እረ ጋ ብለው ያንብቡት እኔ እታዛ ሁኘ እጠብቃለሁ::
እንዲያማ አይሆንም ሌላ ቀን ይዘውት ብቅ ይበሉ ብሎ ክላሰሩን ገፋላቸው:: አባ አንቀርሻው ለጥ ብለው እጅ ነሱና መቼ ልምጣ አሉት::
ነገ ... ከነገ ወዲያ ... ሳምንት ... ወር ... መንፈቅ ... ዓመት ... ማለቂያ የሌለው ቀጠሮ:: (ፀሀየ፣1885 ዋቢ በመጥቀስ ማረው ዓለሙ 1998)

ጥያቄ 13. ከመጨረሻው ዓረፍተ ነገር አገላለጽ በመነሳት ስለ አባ አንቀርሻው የአቤቱታ ፍፃሜ ምን ማለት ይቻላል? ------------------------------------------------

2.3 ቀጥሎ የሚቀርቡት ጥያቄዎች ቀደም ሲል ካነበባችሁት ምንባብ ተመስርተው የወጡ ናቸው:: ጥያቄዎቹን ስትመልሱ:-

ሀ/ ከጽሑፉ በቀጥታ የሰፈረን ሃሳብ መሠረት በማድረግ፣

ለ/ ከቀደመ ልምድና ዕውቀት በመነሳት የሚመለሱ ናቸው::

(ድህረ-ንባብ ጥያቄዎች)፣ ለ14ኛው ጥያቄ አምስት ነጥብ፣ ለ15ኛው ጥያቄ አሥር ነጥብ በመስጠት፤ ከመቶው አሥራ አምስት ድርሻ ይኖረዋል::

14. በፖሊስ አዛዡ ቦታ ብትሆኑ አባ አንቀርሻውን እንዴት ታስተናግዷቸው ነበር? ----

15. ጆግ በጣም የምትወዷቸውን/የምታፈቅሯቸውን ሰዎች አስቡና እንዳይኖሯቸው የምትፈልጓቸውን መጥፎ/ብልሹ ባህሪያት በቃላት ብቻ በመዘርዘር ፃፏቸው? -------

*ክፍል ሦስት:-* የተጀመረን ሃሳብ ለመጨረስ በርካታ መንገዶችን ተጠቅማችሁ፣ የሚከተሉትን ጅምር ዓረፍተ ነገሮች አስፈላጊ ቃላትና ሀረጋትን በመገልገል በራሳችሁ አባባል ጨርሱ:: ከመቶው ሃያ ድርሻ ይኖረዋል::

1. የአካባቢያችን ንጽህና መጠበቅ ------------------------------------------------::
2. ትምህርት ቤት ሲዘጋ ------------------------------------------------------::
3. ኃላፊነትን በአግባቡ አለመወጣት ------------------------------------------------::
4. ሁለት ትልልቅ ልጆች ትላንት ------------------------------------------------::
5. በቃሉ መኪና እንደገዛ --------------------------------------------------------::
6. ------------------------------------------------------------ ኅበዝ ቴክኒሻን ነው::
7. ------------------------------------------------------- ብንችል እንዴት ጥሩ ነበር::
8. ------------------------------------------------- ሲከፈት የጀሮየን ታንቡር ሊበጥሰው ነበር::
9. ------------------------------------------------------ ለመከታተል በመቻላቸው ነበር::
10. ------------------------------------------------ በማቀፍ ወደፊት መራመድ ይኖርበታል::

# አባሪ ሦስት

## በሙከራ ቡድን ለተካተቱ የ10ኛ "ዘ" ክፍል ተማሪዎች የቀረበ ቅድመ ትምህርት ቃለ መጠይቅ፡፡

ቀን፡- ጥቅምት 8/02/2003 ዓ.ም

ቦታ፡- ከኮምፒዩተር ቤተ ሙከራ ክፍል

***ለተጠያቂ ተማሪዎች፡-*** የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ ለተደረገው ሙከራዊ ጥናት መረጃ ማስገኘት ነው፡፡ ከቃለ መጠይቁ የተገኘውን መረጃ ከታቀደው ዓላማ ውጭ ለሌላ ተግባር አይውልም፡፡ ስለዚህ ቀጥሎ ለማቀርባቸው ጥያቄዎች እውነተኛና ትክክለኛ መልስ እንድትሰጠኝ/ጭኝ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

1. ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ እስካሁ ድረስ የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት የተማርህበትን መንገድ እንዴት ትገልጸዋለህ? (ምን ስሜት አሳደረብህ)
2. 9ኛና 10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን ስትማር በውህደት እንድታነብና እንድት ጽፍ የሚያደርግ መልመጃ ያጋጠመህ ጊዜ አለ?
3. 9ኛና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቋንቋውን ተጠቅመህ በውህደት እንድታነብና እንድትጽፍ ለማድረግ ምን ዓይነት ዘዴ ይጠቀማሉ?
4. የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት አቀናጅቶ ትምህርቱ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ ቢሰጥ ምን ሊፈጠር ይችላል ትላለህ?
5. ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማጣቀሻነት ከተዘጋጁት መጻሕፍትና ተዛማጅ ጽሑፎች መካከል ማንበብና መፃፍን በውህደት እንድትለማመዱ የሚያደርጉ አሉ?
6. የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት እንድትማር ቢደረግ፣ ጥቅሙ ወይስ ጉዳቱ የሚያመዝን ይመስልሃል?

# አባሪ አራት

## በሙከራ ቡድን ለተካተቱ የ10ኛ "H" ክፍል ተማሪዎች የቀረበ ድህረ ትምህርት ቃለ መጠይቅ።

ቀን፡- ህዳር 4ቀን 2003 ዓ.ም

ቦታ፡- ኮምፒዩተር ቤተ ሙከራ ክፍል

*ለተጠያቂ ተማሪዎች፡-* የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ ታስቦ ለተደረገው ሙከራዊ ጥናት መረጃ ማስገኘት ነው። ትምህርቱ ከመስጠቱ በፊት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ስድስት ተማሪዎች ተፈላጊውን መረጃ ሰጥተዋል። በተጨማሪ ትምህርቱ ከተሰጠ በኋላ የመጣውን ለውጥ ለማወቅ ይህ ድህረ ቃለ መጠይቅ ተከናውኗል። ስለዚህ ቀጥሎ ለማቀርባቸው ጥያቄዎች እውነተኛና ትክክለኛ መልስ እንድትሰጠኝ በትህትና እጠይቃለሁ።

1. ለአንድ ወር የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት የተማርክበትን መንገድ እንዴት ትገልጸዋለህ? (ምን ስሜት አሳደረብህ)?
2. የዚህ ወር ትምህርት አቀራረብ ከዚህ በፊት ከተማርክበት መንገድ ጋር ሲነፃጸር ልዩነቱ ምንድን ነው? የትኛው ይመረጣል?
3. አሁን በተማርክበት መንገድ ያሻሻልከው ችሎታ አለ? ብትገልጽልኝ?
4. በዚህ ዓይነት የትምህርት አቀራረብ ሁሉም ተማሪዎች ወደፊት እንዲማሩ ቢደረግ ጠቀሜታ አለው ወይስ የለውም? ለምን?
5. የዚህ ዓይነት ትምህርት አቀራረብ ወደፊት የሚቀጥል ቢሆን መሻሻል ያለባቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?
6. አሁን በተማርክበት መንገድ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች እንዲማሩ ቢደረግ ምን ሊፈጠር ይችላል ብለህ ትገምታለህ?

# አባሪ አምስት

## በቪዲዮ ከተቀረጸው የቅድመ ትምህርት ቃለ መጠይቅ የተወሰደ ናሙና

የተሳታፊው ስም፣ ተማሪ አንድ

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት፣ ጥቅምት 8 ቀን 2003

ሰዓት፣ 10:00

1. ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ እስካሁ ድረስ የአማርኛ ቋንቋን ትምህርት የተማርህበትን መንገድ እንዴት ትገልጸዋለህ? (ምን ስሜት አሳደረብህ)

"እስካሁን በተማርኩባቸው የአማርኛ መጽሐፎች አሁንም እየተማርኩበት ያለው የአማርኛ መጽሐፎች፣ በአጠቃላይ እይታ ስመለከተው እ... ያው በምንባብ ላይ የተመሠረተ ሆኖ ምንባቦቹም ምንም እንኳ ድህረ ምንባብና ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች ቢኖሯቸውም እነዚያን ጥያቄዎች ግን እ... ያው ተማሪው እንዲጽፍ ደግሞ ከምንባቡ ተነስቶ የተሰማውን ነገር እንዲያንጸባርቅ የሚያደርጉ ዓይነቶች አይደሉም:: ከዚህ በተጨማሪ መጽሐፉ ያጠናቀራቸው እንደ መጽሐፍ ማንበብ፣ መናገር፣ ማዳመጥና ሥነ ጽሑፍ በሚሉ ርዕሶች የተከፈለ ነው:: እንዲሁም ሰዋስው በሚለው የርዕስ ክፍል እ... በአጠቃላይ የአማርኛን ቋንቋ አጠቃላይ እይታ እንድናውቀው የሚያደርገን እንጅ የበለጠ ከውስጣችን ያለውን ነገር እንድናይ አይገፋፋንም:: ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ በመጽሐፉ ውስጥ ያለው ቅኔ፣ ስነ ቃሎች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ፈሊጦች የመሳሰሉት ነገሮች ከዚህ በፊት የምናውቃቸውና አሰልቺ እየሆኑ ያሉ ነገሮች ናቸው:: እ... ያው እንደ ቋንቋ ተማሪነት እነዚያን ነገሮች ልንማራቸው የሚገቡ ዓይነት ነገሮች አይደሉም:: ከዚህ አንፃር ስመለከተው መጽሐፉ እነዚህ ጉድለቶች አሉበት::"

(ዘ)

2. 9ኛና 10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን ስትማር በውህደት እንድታነብና እንድትጽፍ የሚያደርግ መልመጃ ያጋጠመህ ጊዜ አለ?

"የ9ኛና የ10ኛ ክፍል ትምህርትን እስካሁን እስከማር ባለው ሂደት ውስጥ እንድጽፍና እንዳነብ የሚረዱኝ መልመጃዎችን አላገኘሁም። እ… ቅድም እንዳልሁት ድህረ ምንባብና ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች ቢኖሩም፣ ጥያቄዎቹ ግን አንብቤ እንድጽፍ የሚያደርጉኝ አይደሉም። ምንአልባት በአጫጭር ቃሎች የሚገለጹ ነገሮችን እንድጽፍ የሚገፋፉኝ ዓይነት ናቸው እንጅ፣"

3. 9ኛና 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቋንቋውን ተጠቅመህ በውህደት እንድታነብና እንድትጽፍ ለማድረግ ምን ዓይነት ዘዴ ይጠቀማሉ?

"የ9ኛና የ10ኛ ክፍል መምህሮቹ እ… ያው መጽሐፉ በታተመበት የመጽሐፉ አስታይል ያስተምራሉ። እ… ያው እንደ መጽሐፉ የሚያስተምሩት እንጅ እ… ያው ተጨማሪ ነገር ለማምጣት እስከ ዛሬ የተጠቀሙበት ሁኔታ አላየሁም። ማንበብና መፃፍንም በቅንጅት የተማርኩበት አጋጣሚ የለም። እ… ያው እንደዚህ ነው።"

4. የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት አቀናጅቶ ትምህርቱ ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ ቢሰጥ ምን ሊፈጠር ይችላል ትላለህ?

"የማንበብና የመፃፍ ክሂል አንድ ላይ ተጠናቅረው ከቀረቡ ምንአልባት የተማሪው የመፍጠር ችሎታው ከፍ ይላል። የሚያስባቸውን ነገሮች ወረቀት ላይ የማስፈር፣ እ… እንዲሁም ደግሞ ሌሎች ሰዎች እንዲሰሙለት ይሆናል። ስለዚህ ተማሪው የመፃፍ ችሎታውና ፍላጎቱ ይነቃቃል። በዚህም ምክንያት ምርጥ ምርጥ ደራሲዎች ትምህርት ቤቷም ሆነች አገሪቱ እንድታፈራ ይረዳታል።"

5. ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በማጣቀሻነት ከተዘጋጁት መጻሕፍትና ተዛማጅ ጽሑፎች መካከል ማንበብና መፃፍን በውህደት እንድትለማመዱ የሚያደርጉ አሉ?

"ማንበብን ለየብቻቸው የተፃፉ መጽሐፎች አሉ፣ በእርግጥ ማንበብን እንዳትኩር፣ እንዳውቅ የሚያደርጉ እንዲሁም ደግሞ ሰዋስውን፣ ቅኔዎችን፣ አባባሎችን እንዳውቅ

የሚያደርጉ እንዲሁም ደግሞ በአጫጭር ቃላት እንድጽፍ የሚያደርጉ፣ እ... የግጥም አፃፃፍ ዘዴን የሚያሳዩ መጽሐፎች፣ ልቦለድን ለመፃፍ የሚረዱ መጽሐፎች አሉ። ነገር ግን አንብቤ ያነበብኩትን ነገር ደግሞ እዚያው ላይ እንድገልጽ የሚያደርጉ መጽሐፎች፣ እ... በአጠቃላይ ደግሞ ማንበብና መፃፍን አንድ ላይ አድርጌ እንዳስጉዝ የሚያደርጉኝ መጽሐፎች እስካሁን አላጋጠሙኝም።"

6. የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት እንድትማሩ ቢደረግ፣ ጥቅሙ ወይስ ጉዳቱ ያመዝናል?

"የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ከቅድሙ ጥያቄ ላይ ለመመለስ እንደሞከርሁት የመፃፍና የማንበብ ክሂል አንድ ላይ ተሰጠ ማለት ተማሪው የመፍጠር ችሎታውን ከፍ የማድረግ እድል አገኘ እንደማለት ነው። እ... እና በትክክል ተማሪው ይጠ ቀማል እንጅ ይጎዳል ብዬ አላስብም። ስለዚህ ጥቅሙ ያመዝናል፣ እ... ያው በጣም ይበልጣል ብዬ አስባለሁ።"

70

# አባሪ ስድስት

## በቪዲዮ ከተቀረጸው የድህረ ትምህርት ቃለ መጠይቅ የተወሰደ ናሙና

የተሳታፊው ስም፣ ተማሪ ሦስት

ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን፣ ህዳር 4ቀን 2003

ሰዓት 10:00

1. ለአንድ ወር የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት የተማርክበትን መንገድ እንዴት ትገልጸዋለህ? (ምን ስሜት አሳደረብህ)?

"ለአንድ ወር የተማርኩበት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን እንድናዳብር በአንድ ላይ ተደርገው የተሰጡበት የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎች ቢሆንም፤ እ… ትምህርቱ በአጠቃላይ መልካም ነው ብዬ አምናለሁ:: ምክንያቱም በትምህርቱ የተሰጠነው መልመጃዎች ለምሳሌ እ… እንደሞከርነው እ… እንደሰራነው ጭምር፣ ትምህርቱ በአጠቃላይ ያለንን ነገር አውጥተን መፃፍ እንድንችል፣ እ… በራስ መተማመናችን የበለጠ ማዳበር እንድንችል፣ ጽሑፎቻችንን ለሌሎች ማሰማት እንድንችል፣ በቡድን ተወያይተን ለምንጽፈው ሃሳብ እንድናገኝ የሚረዳን፣ የጓደኞቻችን ጽሑፍ አንብበን አስተያየታችን በጽሑፍ እንድንሰጥ የሚያደርገንና እንድናውቅ የሚያደርገን ዓይነት ነው:: ስለዚህ ተመችቶኛል::"

2. የዚህ ወር ትምህርት አቀራረብ ከዚህ በፊት ከተማርክበት መንገድ ጋር ሲነፃጸር ልዩነቱ ምንድን ነው? የትኛው ይመረጣል?

"ልዩነት አለው፤ ሰፊ ልዩነት፤ ባለፈው እንደተጠየቀውና ጥያቄውን ለመመለስ እንደሞከርኩት ልዩነት አለው፤ እ… ሰፊ ልዩነት፤ ምክንያቱም ባለፈው እነዳልሁት መጽሐፎቻችን ያው… በተለይ የአማርኛ መጽሐፉችን የተሞላው የተለያዩ ምንባቦችን፣ እ… የተለያዩ ህጎችን፣ ስነ ቃሎችን፣ የምናውቃቸውን

ብዙ ጊዜ የተለመዱትን ነገሮች፣ እና በአሁኑ ወቅት ግን ያ ዓይነት ስታይል ቀርቶ፣ እ...ግን የበለጠ የራሳችንን ሃሳብ እንድናወጣና እንድንጽፍ የሚያደርገን ዓይነት ነገር ነው ያየሁት፤ ስለዚህ ሰፊ ልዩነት አለ፣ ይህን ነው ያየሁት።"

3. አሁን በተማርክበት መንገድ ያሻሻልከው ችሎታ አለ? ብትገልጽልኝ?

"አወ ያሻሻልሁት ችሎታ አለ፤ እ... ምንድንነው በተለያዩ ምንባቦች እየተሰጠን ምንባቦቹን ያነበብን እንዴት መፃፍ እንዳለብን የሚያስችሉን ሁኔታዎች ተፈጥረው ነበር። ታሪኮችን ከመጀመሪያቸው አንስተን እንዴት እያስቀጠልን መሄድ እንዳለብን፣ ይህ ደግሞ ጽሑፍን እንዴት መፃፍ እንደምንችል፣ ጽሑፎችም የታሪክ ውጣውረድን ማስወረድ መቻል እንደምንችል አሳይቶኛል። የማንበብና የመፃፍ ችሎታየን በቅንጅት እንዳዳብር ረድቶኛል። እ... ጽሑፎችን በአጠቃላይ በጽሑፎች ዙሪያ ጥሩ ነገር አግኝቻቸበታለሁ ብዬ እገምታለሁ።"

4. በዚህ ዓይነት የትምህርት አቀራረብ ሁሉም ተማሪዎች ወደፊት እንዲማሩ ቢደረግ ጠቀሜታ አለው ወይስ የለውም? ለምን?

"ጠቀሜታ አለው፤ ያው... ከዚህ በፊትም ገልጨዋለሁ ተማሪዎች በዚህ አይነት መልኩ ቢማሩ 1ኛ ያነባሉ፣ ይጽፋሉ፣ የፃፉትን ደግሞ ያነባሉ፣ በዚህ መልኩ በራስ የመተማመናቸውን፣ እ... ችሎታቸውም ይዳብራል። እ... የመፃፍ ችሎታቸውም ይዳብራል። ስለዚህ ጥሩ ጥሩ ፀሐፊዎች ይኖራሉ። እ... ይመጣሉ፣ ብዬ እገምታለሁ። ከክፍል ስንወጣ ስለትምህርቱ አሰጣጥ ከጓደኞቻችን ጋር ስንነጋገር በጣም ጥሩ እንደሆነና ለአማርኛ መምህራችን የሰጠኸነን መማሪያ አሳይተን እንደዚህ እንዲያስተምረን ለመጠየቅ አስበናል።"

5. የዚህ ዓይነት ትምህርት አቀራረብ ወደፊት የሚቀጥል ቢሆን መሻሻል ያለባቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

"አወ ጥረቱ ጥሩ ነው። ... በዋነኛነት እያጠናንበት ያለው ማንበብና መፃፍ በአንድ ላይ አጣምሮ የማየትን ትምህርት ነው። እና በትክክል ሙሉ ለሙሉ

ትምህርቱ ያጠቃለለው ነገር ትክክል ነው ብዬ አምናለሁ። ነገር ግን እንደ ተጨማሪ መጽሐፉ ላይ ያሉት በሙሉም ባይሆኑ የተወሰኑ አስፈላጊ ነገሮች አሉ ተብለው የታመነባቸው ተጨምረውበት፤ ለምሳሌ የሰዋስው ፓርቱ በደንብ ሙሉ ለሙሉ መጽሐፉ እንዳለው አሰልቺ በሆነ መልኩ ሳይሆን አጠር ብሎ ለማስታወስ ያክል እ... ምዕላዶች፣ እንዲሁም ሌሎቹ አጠር አጠር ተደርገው፣ በአጠቃላይ ግን ሰፋ ብሎ ማንበብና መፃፍን አንድ ላይ አድርጎ ያጣመረ ትምህርት ቢሆን የበለጠ የተሻለ ይሆናል ብዬ እላለሁ።"

6. አሁን በተማርክበት መንገድ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች እንዲማሩ ቢደረግ ምን ሊፈጠር ይችላል ብለህ ትገምታለህ?

"አሁን በተማርንበት መንገድ ሁሉም የክፍል ደረጃዎች ቢማሩ ያው... ከታች ጀምረው እ... ከታች ክፍል ጀምረው ተማሪዎች እየፃፉ፣ በደንብ እያነበቡ እየፈጠሩ መምጣት ይጀምራሉ እና ከትንንሽ ክፍሎች ጀምሮ ፈጣሪ ተማሪዎችን የፈጠራ ችሎታ ከልጅነታቸው ጀምሮ እያሳደጉ መምጣት ይቻላል ማለት ነው። በተጨማሪም ማንበብና መፃፍን በአንድ ላይ አቀናጅተው መማራቸው የፈጠራ ችሎታቸውን የበለጠ ያዳብርላቸዋል ብዬ እገምታለሁ።"

73

# አባሪ ሰባት

## ለሙከራ ቡድኑ አባላት ማስተማሪያነት የተዘጋጀ ዕቅድ

የጥናቱ ዓላማ በተፈለገው መጠንና ጊዜ ግቡን እንዲመታ፣ የትግበራው ሂደት በጥራትና ሚዛኑን በጠበቀ አኳኋን እንዲጓዝ ለማድረግ ዕቅድ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ቀጥለው የቀረቡት ዕቅዶች የሙከራና የጥብቅ ቡድኑን የየዕለት ተግባራት በተገቢው መንገድና ጊዜ ለመከወን የሚያስችል ዕለታዊ ዝርዝር ዕቅድ በአጥኚው ተዘጋጅቷል። በመሆኑም የዚህ በስምንት ቀን ለመተግበር ታስቦ የተዘጋጀው ዕቅድ ዋና ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ ታስቦ ለተደረገው ሙከራዊ ጥናት መረጃ ማስገኘት ነው።

የትምህርት ዓይነት አማርኛ

ማክሰኞ ጥቅምት 9 ቀን 2003 ዓ.ም

ክፍል 10ኛ "H"

የቡድን አባላት ብዛት በግልና በቡድን (ከ2-4)

የመጀመሪያ ሳምንት 1ኛ ክፍለ ጊዜ

የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 1:30

የትምህርቱ ርዕስ፦ ማንበብ፣ በጥልቀት ማሰብ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ መፃፍ

የትምህርቱ ዓላማ፦ ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፦

- ለቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ።
- ከምንባቡ ለወጡ ፈሊጦች የያዟቸውን መልዕክቶች የሚወክሉ ዓረፍተ ነገሮች በመመስረት ፍቻቸውን ይጽፋሉ።
- በምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት አብራርተው ይጽፋሉ።

ዝርዝር ተግባራት፡-

1. "የአፍ ነገር" በሚል ተቀረበው የተውኔት ቅንጫቢ ለሁሉም ተማሪዎች ታድሎ ያነቡታል፡፡
2. ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በግላቸው ከሰሩ በኋላ መልሳቸውን በቀኛቸው ከተቀመጠ/ች ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ፡፡
3. የመመሪያ ሁለትን ጥያቄዎች ጥንድ በመሆን ከተወያዩ በኋላ መልሱን በግላቸው ይጽፋሉ፡፡ በመቀጠል ከጎናቸው ካሉት ጥንዶች ጋር አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ይወያዩበታል፡፡ ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ ሃሳብ መሠረት መልሱን አሻሽለው እንደገና በተናጠል ይጽፋሉ፡፡
4. በምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት መረጃ በመፈለግ አብራርተው ይጽፋሉ፣ (የቤት ሥራ)

መርጃ መሣሪያዎች፡-

- አበራ ለማ፣ (1980)
- የተውኔት ቅንጫቢ ጽሑፍ፡፡

ግምገማ፡-

እያነበቡ ዓረፍተ ነገሮችን ሲመሠርቱ፣ ተመሳስሎና ልዩነትን አብራርተው እየፃፉ እንዲሳሩ ሲደረግ፤ የግል፣ የጥንድና የቡድን ተግባራት መልሶችንና ተዛማጅ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም ተማሪዎች በውህደት የማንበብና የመፃፍ ክሂልን በማጎልበት ረገድ ለውጥ ማሳየታቸውን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ (መነሻ ሃሳብ፡- Block, (1997)፣ Beerdgew, (2003) እና Gary, (1995) )

የትምህርት ዓይነት አማርኛ

ሐሙስ ጥቅምት 11 ቀን 2003 ዓ.ም

ክፍል 10ኛ "ሀ"

የቡድን አባላት ብዛት በግልና በቡድን (ከ2-4)

የመጀመሪያ ሳምንት 2ኛ ክፍለ ጊዜ

የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 1:30

የትምህርቱ ርዕስ:- ማንበብ፣ መተንበይና መገመት፣ ዳራዊ ዕውቀትን መጠቀም ማንፀባረቅ በጥለቀት ማሰብ፣ ማጠቃለልና መፃፍ

የትምህርቱ ዓላማ:- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:-

- ቅንጫቢውን በማንበብ ከቀደመ ልምድና ከታሪኩ ሂደት ተነስተው በመገመት ይጽፋሉ፡፡
- ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ፡፡

ዝርዝር ተግባራት:-

1. "እውነትና ንጋት እያደር ይገለጣል" በሚል ርዕስ የተፃፈ ተረት ለሁሉም ተማሪዎች በግል ታድሎ ያነቡታል፡፡
2. ያነበቡትን ከቀደመ ልምድና ከታሪኩ ሂደት ተነስተው በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለተካተቱት ጥያቄዎች በግል መልሳቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ፡፡
3. ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች ጥንድ በመሆን ከተወያዩ በኋላ መልሳቸውን በተናጠል በጽሑፍ ይሰጣሉ፡፡ ከጎናቸው ካሉት ጋር በመሆን ሦስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ከተወየወዩበት በኋላ ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ ሃሳብ መሠረት መልሱን እንደገና በግላቸው አስተካክለው ይጽፋሉ፡፡

መርጃ መሣሪያዎች:-

- በድሉ ዋቅጅራ (1996)
- የተረት ቅንጫቢ ጽሑፍ፡፡

ግምገማ:-

እያነበቡ በመገመት ሲጽፉና ለድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሑፍ እየሰጡ እንዲማሩ ሲደረግ፣ በጥንድና በቡድን የማንበብና የመፃፍ ተግባራት መልሶችን በመገምገም ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ ያለውን ለውጥ በመከታተል ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ (መነሻ ሃሳብ:- Beerdgew, (2003) እና Block, (1997))

የትምህርት ዓይነት አማርኛ

ማክሰኞ ጥቅምት 16 ቀን 2003 ዓ.ም

ክፍል 10ኛ "ዘ"

የቡድን አባላት ብዛት በግልና በቡድን (ከ2-4)

ሁለተኛ ሳምንት 3ኛ ክፍለ ጊዜ

የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 1:30

የትምህርቱ ርዕስ፡- ማንበብ፣ በጥልቀት ማሰብ፣ መተንበይና መገመት፣ መፃፍ

የትምህርቱ ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የስነ-ጽሑፍ ስራውን ላላነበበ ሰው ለማስተዋወቅ የሚረዳ የማስታወቂያ ጽሑፍ ያዘጋጃሉ፡፡
- ካነበቡት ተነስተው በአካባቢያቸው ያለው ለጋብቻ የመተጫጨት ስርዓት ከእድሜ፣ ከሀብትና ከዘር ሐረግ ጋር ተያይዞ ምን እንደ ሚመስል በመዘርዘር ይጽፋሉ፡፡
- ወላጆች ልጆቻቸውን በስርዓት አሳድገው ለቁምነገር ለማብቃት ሊከተሏቸው ይገባል የሚትሉትን መመሪያ በጽሑፍ ያዘጋጃሉ፡፡

ዝርዝር ተግባራት፡-

1. የታደላቸውን ቅንጫቢ ጽሑፉ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ያነባሉ፡፡
2. የፍቅር እስከ መቃብርን ልቦለድ ጽሑፍ ስራውን ለማስተዋወቅ የሚረዳ የማስታወቂያ ጽሑፍ በግላቸው ካዘጋጁ በኋላ ጽሑፉን በግራቸው ከተቀመጠ/ች ተማሪ ጋር ተቀያይረው በማንበብ አስተያየታቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ፡፡
3. ለጋብቻ የመተጫጨት ስርዓት ከዕድሜ፣ ከዘርና ከሀብት ጋር በተያያዘ ምን እንደሚመስል ጥንድ በመሆን ከተወያዩ በኋላ በግል ይጽፋሉ፡፡ በመቀጠል ሦስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ይወያዩበታል፣ ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ ሃሳብ መሠረት መልሱን እንደገና በተናጠል ይጽፋሉ፡፡
4. ወላጆች ልጆቻቸውን በስርዓት አሳድገው ለቁምነገር ለማብቃት ሊከተሏቸው ይገባል የሚሉትን መመሪያ በመዘርዘር ጥንድ በመሆን ከተወያዩበት በኋላ በግል ይጽፋሉ፡፡ በመቀጠል አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት፣ መመሪያ ነው ብለው ፃፉትን መልስ በየተራ እያነበቡ ይወያዩበታል፡፡ የተስማሙበትን መመሪያ በተናጠል እንደገና አሻሽለው ይጽፋሉ፡፡ ቀጥለው ከጥጋቸው ካለ ቡድን ጋር በመቀያየር የተፃፈውን በጋራ እያነበቡ በመገምገም አስተያየታቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ፡፡

መርጃ መሣሪያዎች፡-

- ሀዲስ ዓለማየሁ (1960)
- ቅንጫቢ ጽሑፍ፡፡

ግምገማ:-

ለጋብቻ የመተጫጨት ስርዓትን በመዘርዘር ሲጽፉ፣ የማስታወቂያ ጽሑፍ ሲያዘጋጁና መመሪያ በጽሑፍ እንዲያዘጋጁ ሲደረግ፣ ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት መገልገላቸውን በመከታተል ለውጥ ማሳየታቸውን መገምገም ይቻላል። (መነሻ ሃሳብ:- Block, (1997)፣ Beerdgew, (2003) እና Gary, (1995))

የትምህርት ዓይነት አማርኛ

ሐሙስ ጥቅምት 18 ቀን 2003 ዓ.ም

ክፍል 10ኛ "ዘ"

የቡድን አባላት ብዛት በግልና በቡድን (ከ2-4)

ሁለተኛ ሳምንት 4ኛ ክፍለ ጊዜ

የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 1:30

የትምህርቱ ርዕስ:- ማንበብ፣ ማጠቃለል፣ ማብራራትና መተርጎም፣ ዳራዊ ዕውቀትን በመጠቀም በማስጸባረቅ መፃፍ

የትምህርቱ ዓላማ:- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:-

- ለቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መልሳቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ።
- በአንድ አጋጣሚ የተሰማቸውን ስሜት መግለጽ የሚችል አንድ አጭር ግጥም ይጽፋሉ።
- ግጥሙን ሲያነቡ የተረዱትን ቁም ነገር በአጭሩ ይጽፋሉ።
- በግጥም የቀረበን ሃሳብ ወደ ስድ ንባብ ለውጠው ይጽፋሉ።

ዝርዝር ተግባራት:-

1. የታደላቸውን የግጥም ቅንጫቢ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ያነባሉ።
2. ቅድመ ንባብ ጥያቄውን በተናጠል ከሰሩ በኋላ ከጓላቸው ካለ/ች ተማሪ ጋር

በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ።

በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ።

3. የተሰማቸውን ስሜት መግለጽ የሚችል አንድ ከአስር ስንኝ ያልበለጠ አጭር ግጥም ከፃፉ በኋላ ጽሑፋን በፊታቸው ከተቀመጠ/ች ተማሪ ጋር ተቀያይረው በማንበብ አስተያየታቸውን ጽፈው ለክፍሉ ተማሪዎች እያነበቡ ያሰማሉ።
4. የግጥሙን ሃሳብ በአጭሩ በዝርው በግላቸው ይጽፋሉ፤ ከጎናቸው ሦስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ከተወያዩበት

በኋላ ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ መሠረት መልሱን እንደገና አስተካክለው በተናጠል ይጽፋሉ።

5. ጥንድ በመሆን ተወያይተው በግጥም የቀረበውን ሃሳብ ወደ ስድ ንባብ ለውጠው በግል ከፃፉ በኋላ አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት፣ የፃፉትን ስድ ጽሑፍ በየተራ እያነበቡ ይወያዩበታል። እንደገና አሻሽለው በተናጠል ይጽፋሉ። ከጎናቸው ካለ ቡድን ጋር በመቀያየር የተፃፈውን በጋራ እያነበቡ በመገምገም አስተያየታቸውን በግል ጽፈው ይሰጣሉ።

መርጃ መሣሪያዎች:-

- ደበበ ኃይለ ጊዮርጊስ (1998)
- የግጥም ቅንጫቢ ጽሑፍ።

ግምገማ:-

የግጥምን አፃፃፍ፣ አከዋወንና ማህበራዊ ፋይዳውን ተረድተው ግጥምን ሲጽፉና ወደ ዝርው ጽሑፍ ሲለውጡ ግንዛቤ ማዳበራቸውንም እንዲገለገሉ ሲደረግ፣ ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት መጠቀማቸውንና ማሻሻላቸውን መገምገም ይቻላል። (መነሻ ሃሳብ:- Block, (1997)፣ Beerdgew, (2003) እና Gary, (1995))

የትምህርት ዓይነት አማርኛ
ማክሰኞ ጥቅምት 23 ቀን 2003 ዓ.ም
ክፍል 10ኛ "H"
የቡድን አባላት ብዛት በግልና በቡድን (ከ2-4)
ሦስተኛ ሳምንት 5ኛ ክፍለ ጊዜ
የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 1:30

የትምህርቱ ርዕስ:- ማንበብ፣ መገመት፣ ማብራራትና መተርጎም፣ በጥልቀት ማሰብና መፃፍ

የትምህርቱ ዓላማ:- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:-

- በአካባቢያቸው ስለሚከናወነው የሽምግልና ስርዓት፣ ሂደትና አስፈላጊነት ዘርዝረው ይጽፋሉ።

- ምንባቡን አንብበው የቀድሞውንና ዘመናዊውን የዳኝነት ስርዓት ከዘመናዊው ጋር በማነፃፀር አብራርተው ይጽፋሉ።
- ካነበቡት ተነስተው የቀድሞውን የዳኝነት ስርዓት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ዘርዝረው ይጽፋሉ።

ዝርዝር ተግባራት፡-

1. የታደላቸውን ቅንጫቢ ጽሑፉ ሁሉም ተማሪዎች በግላቸው ያነባሉ።
2. በአካባቢያቸው የሚከናወነውን የሽምግልና ስርዓት አስፈላጊነቱን በሚመለከት የሚያውቁትን ጥንድ በመሆን ተወያይተው በግል ይጽፋሉ። በመቀጠል ሦስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የፃፉትን መልስ በየተራ እያነበቡ ከተወያዩበት በኋላ በግላቸው እንደገና አሻሽለው ይጽፋሉ።
3. የቀድሞው የዳኝነት ስርዓት ከዘመናዊው ጋር ጎን ለጎን ቢሰራበት በፍትህ አሰጣጥ ስርዓቱ ላይ ሊከተል ይችላል ብለው የገመቱትንና ፍትሃዊ ውሳኔ የሚሰጠው የትኛው እንደሆነ ጥንድ በመሆን ተወያይተው በተናጠል ይጽፋሉ። ከጎናቸው አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ከተወየወዩበት በኋላ ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ ሃሳብ መሠረት መልሱን እንደገና በግላቸው ይጽፋሉ።
4. በምንባቡ መሠረት ሙግቱ የተሟጋቹን ንቃት፣ ብልሃትና ብርታት ስለመጠየቁ፣ የቀድሞው ችሎት ከከሳሽና ከተከሳሽ ውጭ ላሉት ሰዎች ስለሚኖረው ጠቀሜታ በግላቸው ዘርዝረው ይጽፋሉ። ሦስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የፃፉትን መልስ በየተራ እያነበቡ ተወያይተው የተስማሙበትን ሃሳብ በግላቸው እንደገና አሻሽለው ይጽፋሉ።

መርጃ መሣሪያዎች፡-

- ሺበሺ ለማ (1958)
- የተውኔት ቅንጫቢ ጽሑፍ።

ግምገማ፡-

የግል፣ የጥንድና የቡድን ተሳትፏቸውን በመከታተል፣ ከአካባቢያቸው የተረዱትን በማስረጽ፣ ድምዳሜና የመፍትሄ ሃሳብ ላይ መድረሳቸውን በማረጋገጥ ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት መጠቀማቸውንና ማሻሻላቸውን መመዘን ይቻላል። (መነሻ ሃሳብ፡- Block, (1997)፣ Beerdgew (2003) እና Gary, (1995)

የትምህርት ዓይነት አማርኛ

ሐሙስ ጥቅምት 25 ቀን 2003 ዓ.ም

ክፍል 10ኛ "ሀ"

የቡድን አባላት ብዛት በግልና በቡድን (ከ2-4)

ሦስተኛ ሳምንት 6ኛ ክፍለ ጊዜ

የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 1:30

የትምህርቱ ርዕስ፡- ማንበብ፣ ምሰላ፣ ማብራራትና ማጠቃለል፣ መፃፍ

የትምህርቱ ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ባነበቡት የዘገባ አፃፃፍ መመሪያ መሠረት የትምህርት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ በዘገባ መልክ በጽሑፍ ያዘጋጃሉ።

ዝርዝር ተግባራት፡-

1. የታደላቸውን የዘገባ አፃፃፍ መመሪያ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ያነቡታል።
2. ባነበቡት መመሪያ መሠረት እራሳቸውን የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር እንደሆኑ በመቁጠር፣ የትምህርት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ በዘገባ መልክ ጥንድ በመሆን ተወያይተው ባጭሩ በግላቸው በጽሑፍ ያዘጋጃሉ። ከጎናቸው ካለ ቡድን ጋር በመቀያየር የተፃፈውን በጋራ እያነበቡ በመገምገም አስተያየታቸ ውን በጽሑፍ ይሰጣሉ።

መርጃ መሣሪያዎች፡-

- አለም እሸቱ 1998)
- አጋዥ ጽሑፍ።

ግምገማ፡-

ዘገባውን ሲጽፉ የጥንድና የቡድን ተሳትፏቸውን በመከታተል፣ ድምጻሚና መፍትሄ ሃሳብ ላይ መድረሳቸውን፣ በመከታተል ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት መጠቀማቸውንና ማሻሻላቸውን በመከታተል ግምገማውን በማካሄድ ማረጋገጥ። (መነሻ ሃሳብ፡- Block, (1997)፣ Beerdgew, (2003) እና Gary, (1995))

የትምህርት ዓይነት አማርኛ

ማክሰኞ ጥቅምት 30 ቀን 2003 ዓ.ም

ክፍል 10ኛ "H"

የቡድን አባላት ብዛት በግልና በቡድን (ከ2-4)

አራተኛ ሳምንት 7ኛ ክፍለ ጊዜ

የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 1:30

የትምህርቱ ርዕስ፡- ማንበብ፣ ማጠቃለል፣ ማብራራትና መተርጎም፣ መፃፍ

የትምህርቱ ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ዓረፍተ ነገሮችን በማንበብ የያዟቸውን ሃሳብ በልዩ ለዩ አባባሎች ተከተው ይጽፋሉ፡፡
- የታሪኩን መነሻ በማንበብ ውጥን ታሪኩን፣ ጨራሽ የሆነ ሃሳብ በማፃፍ ይደመድማሉ፡፡

ዝርዝር ተግባራት፡-

1. የታደላቸውን የጽሑፍ ሁሉም ተማሪዎች በተናጠል ያነቡታል፡፡
2. ዓረፍተ ነገሮች የያዟቸውን ሃሳብ በልዩ ለዩ አባባሎች ተክተው በግላቸው ከፃፉ በኋላ ከጎናቸው ካለ/ች የማሪ ጋር በመቀያየር ገምግመው አስተያየታቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ፡፡
3. የቀረበውን ውጥን ታሪክ በማንበብ የታሪኩን ፍፃሜ ጨራሽ በሆነ ሃሳብ ጥንድ በመሆን ተወያይተው በተናጠል ጽሑፉን ይደመድማሉ፡፡ ከጎናቸው ካሉት ቡድን በመሆን ተወያይተው በተናጠል ጽሑፉን ይደመድማሉ፡፡ ከጎናቸው ካሉት ቡድን ጋር በመሆን አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ከተወየወዩበት በኋላ ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ መሠረት መልሱን እንደገና አስተካክለው በተናጠል ይጽፋሉ፡፡

መርጃ መሣሪያዎች፡-

- አለም እሸቱ (1998)
- የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን የያዘ አጋዥ ጽሑፍ፡፡

ማምገማ፡-

ባነበቡት ጽሑፍ ላይ ተመስርተው በራሳቸው አገላለጽ መፃፋቸውን፣ ውጥን ታሪኩን ጨራሽ በሆነ ሃሳብ መፃፋቸውን በመከታተል፤ ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ማሻሻላቸውን ግምገማ በማካሄድ ማረጋገጥ፡፡ (መነሻ ሃሳብ፡- Beerdgew, (2003)፣ Block. (1997) እና Gary, (1995))

የትምህርት ዓይነት አማርኛ

ሐሙስ ህዳር 2 ቀን 2003 ዓ.ም

ክፍል 10ኛ "H"

የቡድን አባላት ብዛት በግልና በቡድን (ከ2-3)

አራተኛ ሳምንት 8ኛ ክፍለ ጊዜ

የክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 1:30

የትምህርቱ ርዕስ፡- ማንበብ፣ ማሳጠር፣ በጥልቀት ማሰብና መፃፍ

የትምህርቱ ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ባነበቡት የጽሑፍ ማሳጠሪያ መመሪያ መሠረት ቅንጫቢ ጽሑፉን በሦስት እጅ አሳጥረው ይጽፋሉ።
- የቀረበውን ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ ካነበቡ በኋላ ራሳቸውን በሂሳብ ሥራ ዲፕሎማ እንዳላቸው በመቁጠር በመስፈርቱ መሠረት ማስታወቂያውን ላወጣው መስሪያ ቤት መቀጠር የሚፈልጉ መሆናቸውን በመግለጽ ጉዳያቸውን በመዘርዘር ማመልከቻ ይጽፋሉ።

ዝርዝር ተግባራት፡-

1. ቅንጫቢ ጽሑፉን በመመሪያው መሠረት ጥንድ በመሆን ተወያይተው በተናጠል በሦስት እጅ አሳጥረው ይጽፋሉ፤ ከጎናቸው ካሉት ጋር አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ከተወየወዩበት በኋላ ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ጽሑፉን እንደገና አስተካክለው በተናጠል ይጽፉሉ።
2. የቀረበውን ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ ካነበቡ በኋላ ራሳቸውን በሂሳብ ሥራ ዲፕሎማ እንዳላቸው በመቁጠር በመስፈርቱ መሠረት ማስታወቂያውን ላወጣው መስሪያ ቤት መቀጠር የሚፈልጉ መሆናቸውን በመግለጽ ጉዳያቸውን በመዘርዘር በግላቸው ማመልከቻ ይጽፋሉ። ከኋላቸው ካለ/ች ተማሪ ጋር በመቀያየር አንብበው አስተያየታቸውን በጽሑፍ ይሰጣሉ።

መርጃ መሣሪያዎች፡-

- አላምረው ገብረማሪያም (2002)
- ከትምህርት ቤቱ የተገኘ የቅጥር ማስታወቂያ ቅንጫቢ ጽሑፍ፡፡

ግምገማ፡-

ቅንጫቢ ጽሑፉን በሦስት እጅ አሳጥረው ሲጽፉ፣ ባነበቡት ማስታወቂያ ጽሑፍ ላይ ተመስርተው በራሳቸው አገላለጽ የደብዳቤ አፃፃፍ ደንቡን ጠብቀው ሲፅፉ በመከታተል ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ማሻሻላቸውን በመከታተል ግምገማውን በማካሄድ ማረጋገጥ፡፡ (መነሻ ሃሳብ፡- Block, (1997)፣ Beerdgew, (2003) እና Gary, (1995) )

84

# አባሪ ስምንት

## ለጥብቅ ቡድኑ አባላት ማስተማሪያነት የተዘጋጀ ዕቅድ

የመምህሩ ስም _እሸቴ መብራት_ ቀን _10/2/2003_

የትምህርት ዓይነት _አማርኛ_ ክፍልና ሴክሽን _10ኛ "E"_

የክፍል ጊዜ ርዝማኔ _40 ደቂቃ_ የትምህርት ርዕስ _አንብቦ መረዳት_

| | የትምህርቱ ዓላማዎች | የትምህርቱ ይዘቶች | በመማር ማስተማር ክንዋኔው የመምህሩ ተግባር | በመማር ማስተማር ክንዋኔው የተማሪው ተግባር | የግምገማ ሥልት |
|---|---|---|---|---|---|
| | • አንድን ጽሑፍ አንብበው ያገኙትን ቁም ነገር ያስረዳሉ<br>• ቃላትን ያዛምዳሉ::<br>• ለቃላት የሚስማሙ ፍችዎችን በመስጠት ያብራራሉ:: | ➢ አንብበው ያገኙትን ቁም ነገር መግለጽ::<br>➢ ቃላትን ማዛመድ::<br>➢ የቃላትን አውዳዊ ፍች በቃል መግለጽ:: | ❖ ቅድመ ንባብ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ከማንበባቸው በፊት ምን ማድረግ እንዳለባቸው መግለጽ፣<br>❖ በንባብ ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ማሳወቅ::<br>❖ አንብበው ሲጨርሱ በጭብጡ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ::<br>❖ ቃላትን እንዲያዛምዱና ለቃላትና ሀረጎች ፍች እንዲሰጡ ማድረግ::<br>❖ ለሁሉም ተግባራት ማጠቃለያ መስጠት | ✓ የመወያያ ጥያቄዎችን መስራት::<br>✓ በጽሑፉ ውስጥ የተካተቱትን ፈሊጦች መለየት፣ የዘይቤዎችን ምንነትና ፋይዳ ለመገንዘብ መሞከር::<br>✓ በጭብጡ ላይ መወያየት ቃላትን ማዛመድ፣ ለቃላትና ሀረጎች ፍች መስጠት | ተማሪዎች የሰሩትን እንዲገልጹ በማድረግ ማስተካከያ በመስጠት::<br>ተማሪዎች የሰሩትን በማየት ማስተካከያ መስጠት:: |

ዝግጅቱን ያጸደቀው ስም ................

የትምህርት ክፍሉ ተጠሪ ስም ............................

የመምህሩ ፊርማ ...............................

ፊርማ .............. ቀን ..................

ፊርማ ............ ቀን ..............................

ቀን ..............................

# አባሪ ዘጠኝ

## ለሙከራ ቡድኑ አባላት ማስተማሪያነት የተዘጋጀ ማስተማሪያ፡፡

በስምንት ክፍል የተለያዩ ተግባራትን አካቶ የተዘጋጀው ትምህርት ዋና ዓላማ ለሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በቅንጅትና በውህደት ማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና በሙከራ ለማረጋገጥ ታስቦ ለተደረገው ሙከራዊ ጥናት መረጃ ማስገኛት ነው፡፡

## ትምህርት ፩

*መመሪያ ፩፡- የተውኔት ቅንጫቢውን ከማንበባችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሑፍ ስጡ (ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች)፣*

1. በአንድ የተውኔት ቅንጫቢ ውስጥ የሚገኙ ገፀ-ባህሪያት የሥራ ክንዋኔና ከቤተሰቦቻችሁ ጋር የምታደርጉትን ጭውውት አንድነትና ልዩነት አብራርታችሁ ፃፉ? -----------------------------------------------------------------------
2. በርካታ ሰዎች መልዕክታቸው ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ፈሊጦችንና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በጽሑፋቸውና በንግግራቸው መካከል ጣልቃ እያስገቡ የሚጠቀሙት ለምን ይመስላችኋል? መጠቀማቸውን ትደግፋላችሁ? ------------

### የእፍ ነገር

ተማሪ አንድ "ክፍት አፍ አለኝ እኮ!"
ተማሪ ሁለት "ማን!"
ተማሪ አንድ "አፈኛ"
ተማሪ ሁለት "አፉ ቢለጎም ይሆናላ"
ተማሪ አንድ "መቼ ቀንቶት ብለህ! ይህ አንኮላ"
ተማሪ ሁለት "ኳላኮ?"

ተማሪ አንድ "ምህኛቱ ወዲህ ነው"

ተማሪ ሁለት "ወዴት?"

ተማሪ አንድ "ተፈጥሮው ስድቡ ሁሉ የአፍ ነገር ነው"

ተማሪ ሁለት "እንዴት?"

ተማሪ አንድ "እንገር አባቱ? ...አፉ ለምዶበት"

ተማሪ ሁለት "ያፍ አመል እንዲሉ ለማለት?"

ተማሪ አንድ "አፍ ዳገት አይፈራም ሲሉ ሰምቶ"

ተማሪ ሁለት "እንዴት?"

ተማሪ አንድ "አፍ ታልተናገሩበት እዳሪ ነው ይባል የለ"

ተማሪ ሁለት "እሱስ እርግጥ ነው። አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል"

ተማሪ አንድ "አፍን ጠቅሞ ወርቁን ቅሞ፣ ሲባልስ መቼ የዋዛ"

ተማሪ ሁለት "ቢሆንም አፍ ያበዛ፣ ጥበቡ ዋዛ እንዳይሆን"

ተማሪ አንድ "ቢሆንም አፍ ነገር፣ ዓይን አገር አያጣም ይባላል"

ተማሪ ሁለት "ቢሆንም አፍ ያለው ያግባሽ ከብት ያለው ነው ተረቱ"

ተማሪ አንድ "ምን የአፍ ነገር ብዙ ነው"

ተማሪ ሁለት "እርግጥ መዘዙ የዚያኑ ያህል ነው"

ተማሪ አንድ "በርግጥ አፍ ሲያርፍ፣ ወዳጁን ያማል"

ተማሪ ሁለት "በርግጥ አፍ ሲናገር ልብ ይንቃል"

ተማሪ አንድ "ቢሆንም አፈኛ ባፉ፣ ኃይለኛ በመዳፉ መመካቱ አይቀርም"

ተማሪ ሁለት "ቢሆንም አፍና ቅብቅብ ሁልጊዜም አይበላም ይባላል"

ተማሪ አንድ "የለም አፍ ሲያድጥ ከእዳ፣ እግር ሲያድጥ ከአንጋዳ መዶሉ አይቀር ም"

ተማሪ ሁለት "እርግጥ በለፈለፉ፣ ባፍ ይጠፉ"

ተማሪ አንድ "አፍ እላፊ ያስከትላል ጥፊ"

ተማሪ ሁለት "አፈ ምላጭ በደረቁ ይላጭ"

ተማሪ አንድ "የአፍ ዘመድ ከገበያም አይገድ እንዲሉ"

ተማሪ ሁለት "እንዲያ እንዲያ ነው። አፍ የማይታማበት ምን አለ?"

ተማሪ አንድ "ትንግርት እኮ ነው፣ አይዋ አፍ በደግ አለመነሳቱ"

ተማሪ ሁለት "ኧረ ወዲያ! እንኳን በደግ ሊነሳ በክፉ ስሙም በኖረ!"

ተማሪ አንድ "ሹል አፍ! ሲባል"

ተማሪ ሁለት "ኧረ ስንቱ ያፍ ነገር ..." *(አበራ ለማ 1980)*

መመሪያ ፪:- የተውኔት ቅንጫቢውን በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ቀጥሎ ለቀረቡት ፈሊጦች የያዟቸውን መልዕክቶች የሚወክሉ (የሚገልጹ) ዓረፍተ ነገሮችን በመመስረት ፍቻቸውን ፃፉ? (ድህረ ንባብ ጥያቄዎች)

1. ሹል አፍ ----------------------------------------------------------------------------------
2. እሬ ምላጭ ------------------------------------------------------------------------------
3. አፍ እላፊ -------------------------------------------------------------------------------
4. ያፍ አመል ------------------------------------------------------------------------------
5. ክፍት አፍ -------------------------------------------------------------------------------

## ትምህርት ፱

መመሪያ ፩:- ከቀደመ ልምድና ካነበባችሁት ከታሪክ ሂደት ተነስታችሁ በመገመት በምንባቡ ውስጥ ለተካተቱት የሂደት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሑፍ ስጡ?

### እውነትና ንጋት እያደር ይገለጣል

ከብዙ ዓመታት በፊት አቶ ሞልቶት የሚባል አንድ ህብታም ሰው በሸዋ ይኖር ነበር:: ይህም ሰው የበለጸገና ትህትና ያለው ሰው በመሆኑ ብዙ ሰዎች ያከብሩትና ይፈሩት ነበር:: ከደግነቱም ብዛት የተነሳ ለሰዎች ያላራጣ ገንዘቡን ያበድር ነበር:: ድሆች ጎረቤቶቹንም ያግዝ ነበር::

አንድ ተንኮለኛ ሰው ገንዘቡን ተበድሮ እየተሰወረ ሲኖር ከእለታት አንድ ቀን ለጉዳዩ ወደ አደባባይ ወጥቶ ሳለ ሰውዬውን በድንገት አገኘው:: ተበዳሪውም እስካሁን ድረስ ረስቶት ይሆናል ስለዚህ ስለ ገንዘቡ አይጠይቀኝም እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ "የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳምና" ህብታሙ ተበዳሪውን በሰላም ካነጋገረው በኋላ በስውር ማመልከቻ ጽፎ ከሰሰው::

ጥያቄ 1. አበዳሪው የወሰደው እርምጃ ትክክል ነው ትላላችሁ? እናንተ ብትሆኑ ምን እርምጃ ትወስዱ ነበር? ---------------------------------------------------------

"ሰነፍ እረኛ ከፉቅ ይመልሳል" እንደተባለው ሁሉ ይህ ባለፀጋ ባጠገቡ ሳለ ወዲያው ጉዳዩ እንደ ተፈጸመ ሳይጠይቀው ቀርቶ አሁን ግን ተረስቶ በነበረው ገንዘብ ሊዛለል ነው:: ተበዳሪውም "ምን ያምጣ ድሃ ምን ያግሳ ውሃ" የሚባለውን ተረት እያንሰላሰለ "መበደሩንስ ተበድሬ ነበር ነገር ግን አሁን የምከፍለው የለኝም ብዬ ለዳኞች ብነግራቸው አንድ አስተያየት ያደርጉልኛል" በማለት ተስፋ አደረገ:: ተበዳሪውም በዳኛ ፊት ቀረበና ሲጠየቅ አመነ:: ይሁን እንጂ ምንም የሌለው መናጢ ድሃ መሆኑን ለዳኞች አመለከታቸው:: ዳኞቹም "ፍርድ አያውቅ ዳኛ ተገን አያውቅ እረኛ" እንደተባለው ያሉ ነበሩና እስከ ዛሬ ድረስ ከቆየስ አሁን ልትጠይቀው አይገባም ብለው በሃብታሙ ላይ ፈረዱበት::

ጥያቄ 2."ምን ያምጣ ድሃ ምን ያግሳ ውሃ" ሲል ምን ማለቱ ነው? --------------------

በዚህ ነገር አቶ ሞልቶት ተናዶ ወደ ቤቱ ሄደ:: አቶ ቢሰውር ሊጠይቀው ቢመጣ ሲናደድ ሲበሳጭ አገኘው:: እሱም ጥቂት ትዕግስት እንዲያደርግ "ከነገር ከፉ ቁጭት ካውሬ ከፉ ድርጭት" የተባለውን ተረት ከዚህ በፊት አልሰማህምን? ባይሆንስ እንዴት እስከዚህ ድረስ ትበሳጫለህ? አይሆንም! ከቶ እንደዚህ ያለ ሥራ እንዳይደግምህ:: ስለዚህ ለወደፊቱ "አባት ካነሰው ምግባር ያነሰው" የተጎዳና የተበላሸ መሆኑን እያስብክ ገንዘብህን አታበድር ብሎ መከረው::

ጥያቄ 3. እናንተ በአቶ ቢሰውር ቦታ ብትሆኑ ለአበዳሪው ምን ዓይነት ምክር ትመክሯቸው ነበር? ለምን?--------------------------------------------------------

ከዚህ በኋላ አቶ ሞልቶት ለካ "ሰዶ ማሳደድ ሲያምርህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ" ተብሎ የተነገረው ይህን የመሳሰለ ችግር ለሚገጥማቸው ሰዎች ኖሯል፣ ብሎ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ገንዘብ ማበደሩን አቋረጠ ይባላል::

ጥያቄ 4. "ሰዶ ማሳደድ ሲያምርህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ" ሲል ምን ማለቱ ነው? -------

ነገር ግን ምንም ቢሆን ያንድ ሰው ኃጢያት ለዘወትር ወይም ለሁልጊዜ ተደብቆ አይኖርምና ይህ ተበዳሪ እንደ ልማዱ ሌላ ሰው ሲያታልል በፖሊሶች እጅ ተያዘና

ታሰረ። ቅጣቱንም በሚገባ ተቀበለ። ይኸውላችሁ "እውነትና ንጋት እያደረ ይገለጣል" የተባለው ይህ ነው። አስቀድሞ ገና በህፃንነቴ ሳለሁ አባቶቻችን "የአቡነ ዘበሰማያት ጦር ሲወጋ እንጂ ሲወረወር አታይም" እያሉ ሲያወሩ እሰማ ነበር፤ ይሁን እንጂ እውነት መሆኑን እስካሁን አላረጋገጥሁም ነበር። (ሀዲስ ዓለማየሁ፣ ተረት ተረት የመሠረትን ዋቢ ጠቅሶ በድሉ ዋቅጅራ 1996)

ጥያቄ 5. "የአቡነ ዘበሰማያት ጦር ሲወጋ እንጂ ሲወረወር አታይም" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ በአጭሩ ፃፉ? ----------------------------------------

*መመሪያ ፪፡- ምንባቡን በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሑፍ ስጡ(ድህረ ንባብ ጥያቄዎች)፣*

1. ተረት በተናጠል ባለቤት የማይነቀስለት በምን ምክንያት ነው? ---------------------
2. ዕውነትና ንጋት እያደር ይገለጣል በሚል ርዕስ የቀረበውን ተረት አብይ ጭብጥ በራሳችሁ አገላለጽ በአጭሩ ፃፉ?-------------------------------------------------------

## ትምህርት ፫

*መመሪያ ፩፡- ቅንጫቢውን ከማንበባችሁ በፊት ለቀጣዩ ጥያቄ መልሳችሁን በጽሑፍ ስጡ (ቅድመ ንባብ ጥያቄ)፣*

1. የፍቅር እስከ መቃብርን ስራ ለማስተዋወቅ የሚረዳ የማስታወቂያ ጽሑፍ አዘጋጁ። የምታዘጋጁት ጽሑፍ ስራውን ላላነበበ ሰው የሚያስተዋውቅ፣ የስራውን ዋና ዋና ጭብጦች የሚያሳይና የጽሑፉ የቃላት ብዛት የተወሰነ ሊሆን ይገባል። ------------------------------------------------------------

*መመሪያ ፪፡- ከቀደመ ልምድና ካነበባችሁት ከታሪኩ ሂደት ተነስታችሁ በመገመትና በመተንበይ በምንባቡ ውስጥ ለተካተቱት የሂደት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሑፍ ስጡ?*

ቅንጫቢ ጽሑፍ

ሰብለወንጌል ባል ሳታገባ ጊዜዋ በማለፉ የመንደሩ ሰው ሽሙጥና ሀሜት በሄደችበት ሁሉ አንገትዋን ቀና አድርጋ ሰው ለማየት ያሳቅቃት ነበር። አንድ ቀን ከእናትዋ ጋር እቤተክርስቲያን ቆማ ስታስቀድስ፣

"እባክሽ እባክሽ እይለኝ የጌቶችን ልጅ እናትዋን!፣ አከለች።" አለች ደብሪቱ የምትባለው ከመንደሩ አሽሟጣጮች አንድዋ።

"ምን እናትዋን አከለች ትያለሽ? ከእናትዋ በለጠች በይ እንጂ! ዳሌዋንና ደረትዋን አታይም እስቲ የወለደች መስላ።" አለች ጓደኛዋ ስንዱ።

"እነዚህ ምን ሊያደርጓት ነው አስረው የሚያወፍሯት አርደው ይበሏት ይመስል? ወዲያ ላንዱ አይሰጧትም እንዴ?"

"አሁንማ ለማን ይሰጧት ጠያቂ ሲጠፋ? የጠየቋቸውን ሁሉ አታክሉንም አትመስሉንም እያሉ ሲያባርሩ ኖረው አሁን ጠያቂ አጡ።"

ጥያቄ 1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ልጃገረዶች የቤተሰቦቻቸውን ቁጥጥርና አያያዝ በሚመለከት የምታውቁትን አስተያየት ፃፉ? ------------------------------------

"እረ ፍታውራሪ አሰጌ ጠይቀዋል አሉ? አለች ደብሪቱ የሽሙጥ ሳቅ እየሳቀች።"

"የትኛው አሰጌ?"

"እኒህ የብቸናው ፍታውራሪ አሰጌ።"

"ምን ልጅ አላቸው?"

"ለራሳቸው ነው እንጂ ምን ልጅ አላቸው።"

"ለራሳቸው? ኧረ የዲማው አባቴ! የልጅ ልጃቸው አትሆንም?"

"እንዳውም ይግረምሽ! በልጃገረድ ስም አላገባም ብለው ሳይፋረሱ አይቀርም ይባላል!"

"ኧረ በተፋረሱ ምን በወጣት አንዲት ፍሬ ልጅ ሞት የረሳቸው አሮጌ ሰብሳቢ መሆንዋ

አባቷ "ቤት ብትቀመጥ ምን ይጎድላታል።"

"የምትኖርበትስ አያስመኝም ስቃይ ነው አሉ ይሁን እንጂ መቃብር ይመስል የሞተ ሽማግሌ ከመሸከም ያው የምትኖርበቱ ስቃይ ይሻላል።"

"ኧረ እባክሽ የጌታ ልጅ ናት ምን ስቃይ ይኖርባታል?"

ስቃዩስ ይኸ ነው አይባልም አሉ። ያቺ ያመቴ ልጅ የኔ ልጅ የትሁኔ ጓደኛ ናት። አቤታችን በመጣች ቁጥር ስትነግረን ይገርመናል! እኔማ የሷን ታሪክ ስሰማ ድሃ አድርጎ የፈጠረኝን አምላክ አመሰግናለሁ።

"እንዴትኮ?"

ጥያቄ 2. ውሳጆች ልጆቻቸውን በምን መንገድ መቆጣጠር አለባቸው ትላላችሁ? --------

"እንዴትማ... እየውልሽ አሽከሮች እንኳን ከሴቶች በቀር ወንዶች እስዋ በምትኖርበት ቤት አቅራቢያ የታዩ እንደሆነ እነሱም እሷም ወዮላቸው። አሁን እንደምታያት እንዲሁ አቤተክርስቲያንና አዘመዶቻው ቤት ካልሆነ ወደ ሌላ ወጥታ የሰው ፊት ለማየት አይፈቀድላትም። ለዚያውም ቢሆን እንደ እስረኛ ዘወትር በዘበኛ ተከባ ነው። ከቤትዋ ወጥታ ባጥር ውስጥ እንኳ ስትዘዋወር አባትዋ ወይም እናትዋ ያዩዋት እንደሆነ ማን ጠራሽ? ማንን ትጠብቂያለሽ? እያሉ በሰው ፊት ሳይቀር ያዋርዷታል። ታድያ እሷ የእድሜ ጓደኞቿ እንደልባቸው ሲሆኑ እያየች አትበላ አትጠጣ ዘወትር ማልቀስ ብቻ ነው፤ ኧረ ስንቱን ልንገርሽ? ያቺን ያመቴን ልጅ አግተሻት አንድ ቀን ባወራችሽ፣ ኧረ... ኧረ... ኧረ...ድህነት በስንት ጣሙ እቴ!" አለች ደብሪቱ እንደተቆረቆረች ሁሉ ራስዋን እያወዛወዘች የምታወሪው ወሬ በሩቅ እንዳይሰማ ግራ እጅዋን አፍዋ ላይ ገድባ።

ጥያቄ 3. በእድሜ የማይመጣጠኑ ሰዎች ጋብቻ ቢፈጽሙ ምን ሊፈጠር ይችላል? ------

"ለምን ብለው ነው አንዷን ልጃቸውን እንዲህ የሚያስቸግሯት፣" አለች ስንዱ። "ክብራቸውን ለመጠበቅ የነገሌ ልጅ እንዲህ ሆነች እንዳይባል እንግዲያ ለስዋ አዝነው መሰለሽ? ለሷስ ቢያዝኑ የውብት አበባዋ ሳረግፍ ለአንድ ጎበዝ በሰጧት!"

"ለነሱ ክብር እስዋ ዋጋ ከፋይ ሆነች ማለት ነው!"

"ታዲያስ!"

"ግፉም ነው! ለካ ከጌታ መወለድ ከአንድ ወገን ሲመለከቱት የክብር ባርነት ነው! ታውቂያለሽ! እኔ የምፈራው አንድ ነገር ነው፣" አለች ስንዱ። (ሀዲስ ዓለማየሁ 1960)

*መመሪያ ፫፦ ቅንጫቢ ጽሑፉን ካነበባችሁ በኋላ ለቀጣዮቹ ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሑፍ ስጡ (ድህረ ንባብ ጥያቄዎች)፣*

1. በአካባቢያችሁ ያለው ለጋብቻ የመተጫጨት ስርዓት ከእድሜ፣ ከሀብትና ከዘር ሐረግ ጋር ተያይዞ ምን እንደሚመስል በመግለጽ ፃፉ?----------------------------------
2. ሰብለወንጌልን ብትሆኑ ከዚያ ዓይነት ኑሮ ለመውጣት ምን ታደርጉ ነበር? ---------
3. ወላጆች ልጆቻቸውን በስርዓት አሳድገው ለቁምነገር ለማብቃት ሊከተሏቸው ይገባል የምትሉትን መመሪያ ዘርዝራችሁ ፃፉ? ------------------------------------------

## ትምህርት ፱

*መመሪያ ፩፦ ግጥሙን ከማንበባችሁ በፊት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሑፍ ስጡ (ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች)።*

1. ሀሳብንና ስሜትን አጉልቶ ለማስተላለፍ ከግጥምና ከስድ ጽሑፍ የትኛው ይመረጣል? ለምን? ------------------------------------------------------------
2. ግጥም ከሌሎች የስነ-ጽሑፍ ዘርፎች ተለይቶ የሚታወቅበት ባህሪይ አለው? ለምላሻችሁ ምክንያታችሁ ምንድን ነው? ---------------------------------------------

### ለሁሉም ጊዜ አለው

የድሆቹን በደል አንድ ባንድ አይቼ
ስሞታውን ሁሉ በዝርዝር ሰምቼ
ከጨረስኩ በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን
ከጅረት አጠገብ ጥቅጥቅ ወዳለ ደን
ሄድሁና ቁጭ ብዬ ከትልቅ ቋጥኝ ላይ
እገረም ጀመረ ስለ ሰዎች ስቃይ።

ትግል እንደ ያዝሁኝ ከሃሳቤ ጋራ
ትልቅ ሽማግሌ ግርማው የሚያስፈራ
ለሁሉም ጊዜ አለው እያለ ሲያወራ

ድንገት ደረሰብኝ ካለሁበት ስፍራ።
እኔም ሁኔታውን እንደ ተመለከትኩ
ፈላስፋ መሆኑን ወዲያው ተገነዘብኩ።

ጊዜ...ጊዜ...ጊዜ... የምትለው
አሳየኝ በል እስቲ ከወዴት ነው ያለው
ላለው ለሚያመጣ ከሌለው ለሚሰርቅ
ለወሽካታ ጊዜ ምነው ባትጨነቅ
ብዬ ሳጉረመርም ባይኑ እያተኮረ
አዳምጠኝ እያለ መናገር ጀመረ።

ምንም እንኳ ለሰው እንደተፈጠረ የሚቀር ቢመስለው
ጠቢቡ ሰለሞን ተናግሮታልና ለሁሉም ጊዜ አለው
የትዕግስትን ፍሬ ከኑሮ ላይ ወስዶ ሲውጡት ቢመርም
ቀን ይወስዳል እንጂ የታቀደ ዓላማ ሳይሳካ አይቀርም።
ለሁሉም ጊዜ አለው ወዳላዩት ዓለም ቀስ ብሎ ለመግባት
በኑሮ ሸለቆ ዳግመኛ ተወልዶ አብቦ ለማፍራት
አስተውለው እስቲ ባሻገር ያለውን የተራራ ውበት
ነገር ግን የሰው ልጅ መሆን ከሚገባው ከመስመሩ ወጥቶ
በእኩልነት ፋንታ ሀይለኛ ደካማ የሚል ዘዬ አምጥቶ
በብልጠት መኪታ እኖራለሁ ይላል ኑሮን አበላሽቶ።

ኑሮውም ከንቱ ነው የተስፋና ሀዘን አዘቅት የሞላበት
የማይሆነውን ሆኖ የሚሆነውን ሳይሆን መክኖ የቀረበት
ሆኖም በሥራ ኃይል እንዲህ ያለው ኑሮ በርግጥ ይሸነፋል
ጊዜ ያዘዘው ለት ደወሉ ሲደወል እንደጥላ ያልፋል።
ያኔ ነው እንግዲህ ዕውነት ኃይል ስትሆን ማጭበርበር ተረስቶ
ኑሮ ሚለመልመው ከጠወለገበት ከትቢያ ተነስቶ
የዕውቀት አፈርሳታ ታማኝ አቅመኛ የሚመረጥበት
ያኔ ስለሆነ የታሸገ ምላስ የሚላቀቅበት።
ይታየኛል አለ፣ ጊዜ ነው ወሳኙ ለሁሉም ነገር
ይህንን ተናግሮ ሽማግሌው ፈላስፋ ከፊቴ ሲሰወር
ከሀሳብ እንቅልፌ ተመልሼ መጣሁ ከሄድሁበት አገር።
(ደበበ ኃይለ ጊዮርጊስ 1998)

መመሪያ ፪፦ ግጥሙን ካነበባችሁ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሑፍ ስጡ (ድህረ ንባብ ጥያቄዎች)፣

1. በአንድ አጋጣሚ የተሰማችሁን ስሜት መግለጽ የሚችል አንድ አጭር ግጥም ፃፉ? ------------------------------------------------------------

2. ግጥሙን ስታነቡ የተረዳችሁትን ቁም ነገር በአጭሩ ፃፉ? --------------------

ምሳሌ፦ ግጥም፦ ውፍረቱ ክሳቱ ቅጥነቱ ግዝፈቱ
ጥቁረቱ ቅላቱ ንጣቱ ግርጣቱ
ማራኪ ገፅታው ማግኘቱ ማጣቱ
መስፈሪያው አይሆንም ለሰው ሰውነቱ።

ግጥሙ ወደ ስድ ጽሑፍ ሲለወጥ፦

ስድ ንባብ፦ የአንድን ሰው ማንነት ለመለካት ውጫዊ የሆነው ገፅታው፣ የሰውነት ቅርጹ፣ አቋሙና ሀብቱ ወሳኝ ሊሆን አይችልም።

መመሪያ ፫፦ ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሠረት የሚከተለውን ግጥም አንብባች ሁ መልዕክቱ ሳይዛባ ወደ ስድ ጽሑፍ ለውጣችሁ ፃፉ?

1. አንድ ነገር አለ ብንመለከት
እንስሳ ከሰው ልጅ የሚበልጥበት
በሰዎች መካከል ሰካራሞች ሞልተው
እንሰሶች ግን መቼም አይሰክሩም ጠጥተው።

ስድ ጽሑፍ ------------------------------------------------------------

## ትምህርት ፩

መመሪያ ፩፦ ጽሑፉን ከማንበባችሁ በፊት ለቀጣዩ ጥያቄ መልሳችሁን በጽሑፍ ስጡ (ቅድመ ንባብ ጥያቄ)።

1. በአካባቢያችሁ የሚከናወነው የሽምግልና ስርዓት አስፈላጊ ነው ወይስ አይደለም? ለምን? ------------------------------------------------------------

## ተጠየቅ

በአገራችን በኢትዮጵያ የሥነ-ሥርዓት ህጎች እንደዛሬው ተደንግገው ባልወጡበትና ከወጡም በኋላ በስራት ሥራ ላይ ባልዋሉበት ዘመን ሙግቱም ሆነ ዳኝነቱ ይካሄድ የነበረው በዘልማድ እንደነበር አይዘነጋም። የችሎቱም ሥፍራ ባብዛኛው በየዛፉ ጥላ ስር ለህዝብ ግልጽ በሆኑ ቦታዎች ነበር። ይህ ያደባባይ ስርዓት ያገራችን ብቻ ሳይሆን፣ ብዙዎች የውጭ አገር ሰዎችን ትኩረት ጭምር የሚስብና የሚማርክ እንደነበር ይነገርለታል። በመሆኑም በተለይ የጥንቱን ህብረተሰብ አኗኗር፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ለማየት ላልቻሉ በምናብ ያስቃኛል።

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ይህ የችሎት ስርዓት ቀስ በቀስ ቦታውን ለዘመነኛው የአሰራር ስርዓት መልቀቁ የግድ ነበር። ዳግማዊ ምኒልክ አገራቸውን በተሻለ የስልጣኔ ጎዳና ለመምራት በነበራቸው ጽኑ ፍላጎት አቋቁመዋቸው ከነበሩት አዳዲስ መንግስታዊ ተቋሞች አንዱ የዳኝነት ሚኒስቴር ይገኝበታል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የ"ተጠየቅ" ሙግት እየተዳከመ መጣ።

የጥንቱ ችሎት በተነሳ ቁጥር ይበልጥ ትውስ የሚለውና ትዝታውም ከብዙዎች አእምሮ ውስጥ ሳይፋቅ እንደቆየ የሚነገርለት አንድ ነገር አለ። ይኸውም ተውኔታዊ ባህሪይ የነበረው የከሳሽና የተከሳሽ አለባበስ፣ አቋቋም፣ ዘንግ አያያዝ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የነገር አቀራረብና በአጠቃላይም ሞቅና ደመቅ ያለው ጥምር የአሞጋገቱ ስልት ነበር። ተሟጋቾ ለመርታት ረትቶም እርካታ፣ ዝናና ክብርን ለመቀዳጀት በቅድሚያ የተሟጋቹን ንቃት፣ ብልሃትና ብርታት ይጠይቃል። በተለይም የመሟገቻው ቋንቋ በተዋቡ ቃላት፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ በተረት፣ በአፈ ታሪክ፣ በእንቆ ቅልሽና በመሳሰሉት ዘዴዎች የበለጸገና ለዛ ያለው መሆን ይጠበቅበት ነበር። የእነዚህ ሁሉ ውህድ የችሎቱ ነፃ ትርኢት ስለነበር፣ ወጪ ወራጁን አላፊ አግዳሚውን ሁሉ ይማርክና ያማልል ነበር።

የቀድሞው ችሎት በአንድ የመከራከሪያ ጉዳይና ጭብጥ ላይ በመመርኮዝ ከሳሽና ተከሳሽ ብቻ የሚሟገቱበት ወይም በአጠቃላይ ከአንድ የክስ ጉዳይ ጋር አግባብ ያላቸው ሰዎች ብቻ የሚያዘወትሩት መድረክ አልነበረም። ይልቁንም ለሌሎችም ጭምር የአሞጋገትና የአነጋገር ስልትን የመቅሰሚያ፣ ህግና ዳኝነትን የመማሪያ፣ ከሹማምንቶችና ከመሳሰሉት ከፍተኛ ሰዎች ጋር የመተዋወቂያና ለዳኝነትም ሆነ ለሌላ ስልጣን የመመረጫ ቦታም ነበር። ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ቀጣዩን ሙግት እንመልከት።

አንድ በሬ የጠፋበት ደገኛ ገበሬ በሬውን ፍለጋ አገር ላገር ሲንከራተት፣ ከአንድ የቆላ መንደር አካባቢ ሲደርስ ሙዳ ስጋ እነጨ የሚበላ ልጅ ይመለከትና በጥርጣሬ ከልጁ አባት ጋር የይገባኛል እሰጥ አገባ ሙግቱን ይቀጥላል።

በላ ልበልሃ!
ያጤ ስርዓቱን የመሠረቱን
አልናገርም ሃሰቱን
ሁሌ ዕውነት ዕውነቱን
በሬ ጠፍቶብኝ ከደጋ
በሰፈርህ ጎራ ስል ለፍለጋ
ከልጅህ እጅ ስላገኘሁ ሙዳ ስጋ
ልትከፍለኝ ይገባል የበሬየን ዋጋ

ተከሳሹ አፈ ጮሌ ተሟጋች፣ ነገር አዋቂና አራቃቂ ነበርና እሱም በበኩሉ የዳኛውን ስሜት ለመስረቅና በክርክሩ አሸናፊ ለመሆን እንዲህ ብሎ ይጀምራል፣

እገሌ አለችው እናቱ
ወርቅ የፈሰሰበት ይመስላል ደረቱ
መቃ ይመስላል አንገቱ
ከሱ ወዲያ ዳኝነት
ቀጠሮ ማይሰጥ ላመት
እሱ የፈረደው ፍርድ
ብራቅ የመታው ግንድ
ግንዱም ይደርቃል
ፍርዱም ይጸድቃል

በማለት የዳኛውን ይሁንታ ለማግኘት ካሞካሸ በኋላ ከሳሹን እንዲህ በማለት ይመልስለታል፤

በሬ ጠፍቶብህ ከደጋ
ወደቆላ ብትመጣ ፍለጋ
ከልጆ አፍ ብታይ ሙዳ ስጋ
ከቤቴ በላይ መንገድ አለ
በመንገዱም ላይ ዛፍ ያልፍበታል
ከዛፉም ላይ አሞራ ይሰፍርበታል
አሞራና አሞራ ሲጣሉ ሙዳ ስጋ ቢተፉ
አላዋቂ ልጅም ያገኘውን ወዳፉ
ይኸም አያስኝም ክፉ

ከሳሽና ተከሳሽ ግራ ቀኝ ቆመው በሚሟገቱበት ወቅት በጭብጡ ላይም ሆነ ከጭብጡ ውጭ በሆነ ጉዳይ ላይ ተከሳሽ ወይም ከሳሽ የቀረበበትን ክስ ቢክድ ውርርድ ይከፍል ነበር። የኸውም መወራረድ ማለት ሲሆን ተረችው የተለያዩ ነገሮችን ለምሳሌ በቅሎ፣ ፈረስ፣ ማርና ወዘተ "እሰጥ!" ወይም "አገባ!" ብሎ መቀጮውን ለመክፈል ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል።

በአጠቃላይ የቀድሞውን የዳኝነት ስርዓት ቀስ በቀስ ቦታውን ለዘመናዊው እየለቀቀና፣ ልዩ ልዩ የስርዓት ህጎች ተደንግገው በስራ ላይ እንደዋሉ እንረዳለን። (ሺበሽ ለማ 1958)

*መመሪያ ፬፡- ጽሑፉን ካነበባችሁ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልሳችሁን በጽሑፍ ስጡ (ድህረ ንባብ ጥያቄዎች)፣*

1. የቀድሞው የዳኝነት ስርዓት ከዘመናዊው ጋር ጎን ለጎን ቢሰራበት በፍትህ አሰጣጥ ስርዓቱ ላይ ምን ሊያስከትል ይችላል? ------------------------------
2. ከቀድሞውና ከዘመናዊ የፍትህ አሰጣጥ ሥርዓት ሂደት ለባለጉዳዮች ፍትሃዊ ውሳኔ የሚሰጠው የትኛው ይመስላችኋል? ------------------------------
3. ሙግቱ የተሚጋቹን ንቃት፣ ብልሃትና ብርታት ይጠይቃል ሲባል ምን ማለት ነው? ------------------------------

# ትምህርት ፯

## የዘገባ አዘገጃጀትና አቀራረብ

ዘገባ የተሰማን፣ የታየን፣ የተሰራና በሚገባ የተጠናን ጉዳይ ከስሜታዊነት ነፃ በሆነ መንገድ ማቅረቢያ ዘዴ ነው።

### የዘገባ ዝግጅት መመሪያ

1. ዘገባ የሚቀርብበትን ጉዳይ በሚገባ ተገንዘቡ።
2. የዘገባውን ቅንብራዊ ሁኔታ በቅድሚያ አቅዱ።
3. አስፈላጊ መረጃዎችን አሰባስቡ።
   1.1 ስለአርዕስተ ጉዳዩ ከሚያወሱ ልዩ ልዩ ጽሑፎች
   1.2 ከባለሙያዎች
   1.3 ልዩ ልዩ ድርጅቶችን በማነጋገር
   1.4 ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ግለሰቦችና የመሳሰሉት ናቸው።

### የዘገባ አዘገጃጀት መመሪያ

1. ዘገባውን ያዘጋጃችሁበትን ቀን በመጀመሪያው ገጽ ላይ በቀኝ በኩል ፃፉ።
2. የዘገባውን ርዕስ በመጀመሪያው ገጽ መሀል ላይ ፃፉ።
3. የዘጋቢውን ስም በመጀመሪያው ገጽ ከርዕሱ በታች በግራ በኩል ፃፉ።
4. ለዘገባው ተገቢውን መግቢያ ፃፉ።
5. በአስተዋጽኦአችሁ መሠረት የዘገባውን ሀተታ ፃፉ።
6. ዘገባችሁን በሒሳብ ስሌቶች በስታትስቲካዊ መረጃዎች፣ በንድፎች፣ በካርታዎ ችና በስዕላ ስዕል እንዳስፈላጊነቱ በእነዚህ የተደገፈ አድርጉ።
7. ዘገባውን ግልጽና ማራኪ በሆነ ቋንቋ አቅርቡ።
8. በዘገባው ውስጥ የሀሳብ ድግግሞሽና ተቃራኒ ሀሳቦች እንዳይኖሩ ተጠንቀቁ።
9. በዘገባችሁ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችንና መፍትሄዎቻቸውን ጠቁሙ።

ዘገባችሁን በማጠቃለል ለውሳኔ የሚረዱ ሀሳቦችን ፃፉ። (ዓለም እሸቱ 1998)

መመሪያ ፩:- ከላይ በቀረበው መመሪያ መሠረት እራሳችሁን የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር እንደሆናችሁ በመቁጠር፣ የትምህርት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ በዘገባ መልክ በአጭሩ በጽሑፍ አዘጋጁ? ---------------------

## ትምህርት ፯

### በልዩ ወይም በሌላ አባባል መግለጽ

አንድን ሃሳብ በልዩ ለዩ አባባል መግለጽ ይቻላል፣ ለምሳሌ

መስራት የመናገርን ያህል ቀላል አይደለም።

- መናገር ከመስራት የቀለለ ነው።
- መስራት ከመናገር ይልቅ ከባድ ነው።
- የመናገርን ያህል መስራት ቀላል ነገር አይደለም።

መመሪያ ፩:- ከላይ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች የያዟቸው ሃሳቦች ሳይዛቡ በልዩ ልዩ አባባሎች ግለጹ፣

1. የሞተው ላያመሰግን፣ ከሞትም ላይነሳ፣ ፀጉር መንጨቱ፣ ማቅ መልበሱ ምን ይባላል? -----------------------------------------------------------
2. አብዲሳን ሳይ አሉላን እየመሰለኝ፤ አሉላን ሳይ ደግሞ አብዲሳን እየመሰለኝ ተቸግሬያለሁ። -----------------------------------------------------------
3. የነገርከኝ ነገር ልቤን ስለነካው፤ እንዲሁ ሌሊቱን ሙሉ እሱኑ እያንሰላሰልሁ አደርኩ።-----------------------------------------------------------
4. የአስር አለቃ ሃለፎም አቋቋምና መሣሪያ አደጋገኑ የሚያስደንቅ ቢሆንም፣ አልሞ መምታቱ ላይ ግን ውጤታማ አይደለም። --------------------------------
5. የሰው ልጅ አረም የበዛበት የመከራ ተክል ነው። --------------------------------

መመሪያ ፪:- የተጀመረን ወይም የተወጠነን ሃሳብ ለመጨረስ የተለየና ይህ ነው የሚባል ቀምር ያለው አይደለም። የተወጠነውን ሃሳብ መንፈሱን በመረዳት ፍፃሜው በዚህ መንገድ ሳይሆን አይቀርም ብሎ ውጥን

*ጨራሽ ሃሳብን በተገለጸበት መንገድ በመጨመር ሃሳቡን መደምደም ነው:: ስለዚህ ቀጣዩን ውጥን ታሪክ ፍፃሜውን ጨራሽ የሆነ ሃሳብ በመጨመር ታሪኩን ደምድሙ፣*

መርጌታ ስመረ ከወለሉ ላይ የለቃቀሟቸውን ወረቀቶች ጠረጴዛው ላይ ካስቀመጡ በኋላ ብድግ ብለው መስኮቱን ዘጉት:: መለስ ሲሉ አንድ ሁለት ማስታወሻ የተፃፈባቸው ብጣሽ ወረቀቶች ከጠረጴዛው ስር አዩ:: እርጅና ያጎሳቆለውን ጠይም ፊታቸውን ቅጭም አድርገው በአንድ እጃቸው የጠረጴዛውን ጫፍ ለመደገፊያ ይዘው ጎንበስ ሲሉ ጠረጴዛው ላይ የነበረው የቀለም ብልቃጥ ከንበል ብሎ የማስታወሻ ወረቀታቸውን በከለው:: -------

---

## ትምህርት ፳

### አህጽሮተ ጽሑፍ

አህጽሮተ ጽሑፍ ወይም ጽሑፍን ማሳጠር ማለት በሰፊው የተተነተነን ሃሳብ ፍሬ ነገሩን ብቻ በመውሰድ በአጭሩ መጥኖ ማቅረብ ማለት ነው:: አንድን ጽሑፍ በምናሳጥርበት ጊዜ የሚከተለውን መመሪያ መከተል ያስፈልጋል::

1. የጽሑፉን አጠቃላይ ሃሳብ ለማግኘት ምንባቡን ደግማችሁ ደጋግማችሁ አንብቡ::
2. በአጠረው ጽሑፍ ላይ መስፈር ያለበትን ፍሬ ሃሳብ ለይታችሁ አውጡ::
3. ከጽሑፉ ሃሳብና መልዕክት እስካላፈነገጠ ድረስ የሚያጥረውን ጽሑፍ ቅልብጭ ለማድረግ ይረዱናል የምትሏቸውን ቃላት ተጠቀሙ::
4. እንዲያጥር ከተሰጠው ጽሑፍ ሃሳብ ሌላ የራሳችሁን ሃሳብ አትጨምሩ::
5. በአጣሪው ጽሑፍ ውስጥ መገለፅ ያለበት ፍሬ ነገር አለመቅረቱን አረጋግጡ::
6. የራሳችሁን አባባልና ቋንቋ ተጠቀሙ::
7. በአንደኛ መደብ አገላለጽ የቀረቡ ዓረፍተ ነገሮችን በሦስተኛ መደብ አነጋገር ለውጣችሁ ፃፉ::
8. በምን ያህል መጠን ማጠር እንዳለበት ካልተገለጸ በሲሶ አሳጥሩ::
   (አላምረው ገብረማርያም 2002)

*መመሪያ ፩፡- ከላይ በቀረበው መመሪያ መሠረት የሚከተለውን ቅንጫቢ ጽሑፍ በሦስት እጅ አሳጥራችሁ እንደገና ፃፉ።*

ባህል ሲባል በህብረተሰብ ታሪክ ሂደት ውስጥ መላው የሰው ልጅ የፈጠራቸውን ቁሳዊና መንፈሳዊ የባህል ግንኙነቶች፣ የተፈጠሩበትን ግልጋሎት ላይ የሚውሉበትንና የሚተላለፉበትን ዘዴዎች ያጠቃልላል። ቁሳዊ ባህል የሚባለው የሰው ልጅን ቁሳዊ ክንውንና ውጤቶችን የሚሸፍን መስክ ሲሆን፣ የቴክኒክ መገልገያ መሣሪያዎችን፣ የማምረት ልምድንና ሌሎችንም ቁሳዊ ሀብቶች በማጠቃለል ይይዛል። መንፈሳዊ ባህል የሚባለው ደግሞ ሰዎች ቁሳዊ ምርትን በማምረት ሂደት የሚያመ ርቱት የመንፈሳዊ ምርት መስክ ሲሆን ይህም እንደ ሳይንስ ትምህርት ሥነ ጥበብ፣ ፍልስፍና፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ባህላዊ ቁሶች ያጠቃልላል። እነዚህ የቁሳዊና የመንፈሳዊ የባህል መስኮች የተነጣጠሉ ሳይሆን እርስ በራሳቸው የተያያዙ ናቸው። በመካከላቸው ባለው ግንኙነት ውስጥ መንፈሳዊው ባህል ከቁሳዊ ባህል የሚመነጭና በሱም የሚወሰን ይሁን እንጂ መንፈሳዊው በቁሳዊው ላይ ተመልሶ የራሱን ተጽዕኖ ያሳድራል። ይኸው የቁሳዊ ባህል እድገት ደግሞ ተመልሶ በተራው የመንፈሳዊውን ባህል ዕድገት ያዳብራል። (ደበበ ኃይለ ጊዮርጊስ 1998) ---------------------------------------------------------------

*መመሪያ ፪ ፡-ቀጥሎ የቀረበውን ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ ካነበባችሁ በኋላ ራሳችሁን በሂሳብ ሥራ ዲፕሎማ እንዳላችሁ በመቁጠር በመስፈርቱ መሠረት ማስታወቂያውን ላወጣው መስሪያ ቤት መቀጠር የምትፈለጉ መሆናችሁን በመግለጽ ጉዳያችሁን በመዘርዘር ማመልከቻ ፃፉ፣ ከመቶው 20 ድርሻ ይኖረዋል።*

ቁጥር ወ/ከ/ት/08/03/03

ቀን 12/01/2003

## ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ

የወረታ አጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባለው ክፍት የሥራ መደብ ሠራተኞችን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል። ስለዚህ፡-

➢ የሥራ መደቡ መጠሪያ-----------------------------------------------የሂሳብ ክፍል ኃላፊ

➢ የመለያ ቁጥር-----------------------------------------------------ወረ-5/ሂ-7

➢ ደመወዝ -----------------------------------------------------------801

➢ ብዛት----------------------------------------------------------------1 (አንድ)

➢ የሥራ ቦታ--------------------------------------------------ወረታ ከ/ት/መ/ሁ/ደ/ት/ቤት

➢ ደታ-----------------------------------------------------------------አይለይም

➢ ተፈላጊ ችሎታ በሂሳብ አያያዝ፡-

✓ በ10 + 3 በሙያና ቴክኒክ የሰለጠነ/ች እና 4 ዓመት የሥራ ልምድ

✓ ዲፕሎማ 0 ዓመት የሥራ ልምድ

ማሳሰቢያ፡- የመመዝገቢያ ቦታ ወረታ የከ/ትም/መሰ/ሁለ/ደ/ት/ቤት

❖ የመመዝገቢያ ጊዜ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት፣

❖ የትምህርት ማስረጃችሁንና ይጠቅመኛል የምትሉትን ማስረጃ የማይመለስ ሁለት ፎቶ ኮፒ ከዋናው ጋር ማቅረብ ይጠበቅባችኋል፣

❖ ሴቶች ይበረታታሉ።

(ከትምህርት ቤቱ የተገኘ ማስታወቂያ 2003)

---

103

# አባሪ አሥር

## የሙከራ ቡድኑ የክፍል ውስጥ ክንውን የምልከታ ናሙና

ቀን፣ ጥቅምት 9ቀን 2003 ዓ.ም

ሰዓት፣ ከ9:00-10:30

የሙከራ ቡድኑ የጧት ፈረቃ ስለነበር በእረፍት 4:05 ላይ ተገናኝተን ትምህርቱ የሚሰጥበትን አመቺ ጊዜ ለመምረጥ ከተወያየን በኋላ ከመደበኛው ፈረቃ ውጭ ከሰዓት በኋላ እንዲሆን ተስማማን። በ9:00 ለመገናኘት በያዝነው ቀጠሮ መሠረት በ8:54 ላይ 40 ተማሪዎች ስለተገኙ ወደ መማሪያ ክፍሉ ገብተን መቀመጫዎችን አደራጀን። ስለምናከናውነው ተግባር ስንነጋገር ከቀሪዎቹ ተማሪዎች መካከል አራት ተማሪዎች መጥተዋል። የዕለቱ ትምህርት "የአፍ ነገር" የተሰኘው ምንባብና ልዩ ልዩ ጥያቄዎችና ተግባራት ተካተው ቀርበዋል። ከምንባቡ በፊት የቀረቡት ሁለት የመወያያ ጥያቄዎች ዓላማም ተማሪዎቹ በቀጥታ ወደ ምንባቡና ወደ መልመጃዎቹ ከመሄዳቸው በፊት፣

- አእምሯቸውን ለትምህርቱ ዝግጁ ለማድረግ
- ዳራዊ ዕውቀታቸውን ከምንባቡ ይዘት ጋር ለማስተሳሰር
- የምንባቡ ፍሬ ሀሳብ ምን እንደሆነ አስቀድመው እንዲተነብዩ ለማድረግ ታስበው የተዘጋጁ ናቸው። በዚህ መሠረት ተማሪዎች ያላቸውን ሃሳብ በጽሑፍ አስፈሩ።

በመቀጠል በአምስት ደቂቃ ውስጥ "የአፍ ነገር" የተሰኘውን የተውኔት ቅንጫቢ ጽሑፍ ለሁሉም ተማሪዎች ታድሎ ቀጣዩ የትግበራ ሂደት ተገልጾላቸዋል። በመቀጠል በ10 ደቂቃ ውስጥ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን በግላቸው ከጥያቄው ቀጥሎ ባለው ክፍት ቦታ ላይ ከሰሩ በኋላ መልሳቸውን በቀኛቸው ከተቀመጠ/ች ተማሪ ጋር በመቀያየር እንዲበበው አስተያየታቸውን በጽሑፍ እንዲሰጡ ተደረገ።

ይህ እንደተጠናቀቀ ለአሥራ አምስት ደቂቃ ያህል ምንባቡን በሚያነቡበት ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በመግለጽ ለምሳሌ፦ ከበድ ከበድ ያሉ ቃላትና ሀረጋትን በማስታወሻቸው እንዲጽፉ፣ በጽሑፉ ውስጥ የተካተቱትን ፈሊጦችና ምሳሌያዊ አነጋገሮች በማስታወሻቸው ለይተው እየፃፉ ምንነታቸውንና ፋይዳቸውን ለመገንዘብ

እንዲሞክሩና የመሳሰሉትን በመንገር ምንባቡን በጽሞና እንዲያነቡት ተደረገ። ሁሉም ማጠናቀቃቸውን በማረጋገጥ የመመሪያ ሁለትን አምስት ጥያቄዎች ከመስራታቸው በፊት ስለ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ስለ ፈሊጦች ምንነትና ባህሪያት ማስረጃ በመስጠት ማብራሪያ እየተሰጠ ተወያየንበት። በመቀጠል በሃያ ደቂቃ ውስጥ ከምንባቡ ለወጡት ፈሊጦች የያዟቸውን መልዕክቶች የሚወክሉ ዓረፍተ ነገሮች በመመስረት ፍቻቸውን ጥንድ በመሆን ከተወያዩበት በኋላ ምላሻቸውን በግል ጽፈዋል። በመቀጠል ከጎናቸው ካሉት ጥንዶች ጋር አራት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የሰጡትን መልስ በየተራ እያነበቡ ተወያይተዋል። በ15 ደቂቃ ውስጥ ከውይይቱ ባገኙት ማሻሻያ መሠረት መልሱን እንደገና በተናጠል እንዲጽፉ ተደረገ። አምስት ተማሪዎች የፃፉትን በማንበብ ለክፍሉ አሰምተዋል። እያንዳንዱን ተግባር በተመደበለት ጊዜ መከናወኑን፣ ተማሪዎች የተሰጣቸውን የተናጠልና የቡድን ሥራ ሁሉም በተግባር መስራታቸውን በአጥኚው ክትትል ተደርጓል።

ተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን በውህደት እንዲማሩ ሲደረግ የግል፣ የጥንድና የቡድን ተግባራት መልሶችን በመከታተልና ተዛማጅ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም ተማሪዎች ለውጥ ማሳየታቸውን ለማረጋገጥ ተሞክሯል። ለዚህም የተወሰደው እርምጃ ከክንውኑ ውስጥ የተወሰኑትን ሂደቶች በቪዲዮ መቅረጽና የመልስ ወረቀቶችን ለቀጣዩ ክፍለ ጊዜ እንደሚመልስላቸው በመግለጽ ሰብስቦ ማየት ስለነበር ተግባሩን የሰሩበት የመልስ ወረቀት ተሰብስቧል። በዕለቱ ትምህርት ተማሪዎች ያደርጉት የነበረው ተሳትፎ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ የተሰጠውን ተግባር ያላከናወነ ተማሪ አልነበረም። በቪዲዮ የተቀረጸው መረጃም ይህን ያረጋግጣል።

በመጨረሻም በአምስት ደቂቃ ውስጥ በምሳሌያዊ አነጋገሮችና በፈሊጦች መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት የተፃፈ መረጃ አንብበው ወይም ሰው ጠይቀው በጽሑፍ አዘጋጅተው እንዲመጡ የቤት ሥራ ተሰጥቷቸዋል። ስለ ዕለቱ ትምህርት አሰጣጥ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡም ተደርጓል። ስለዚህ በሰጡት አስተያየት የትምህርት አሰጣጡን ዘዴና የትምህርቱን ይዘት እንደወደዱት በመግለጽ፣ ሁሉም ተማሪዎች ወደፊት እንደማይቀሩ ቃል በመግባትና ስምምነት ላይ በመድረስ የዕለቱን ትምህርት ተጠናቋል።

## አባሪ አሥራ አንድ

በሙከራ ቡድን ለተካተቱ የ10ኛ "ሀ" ክፍል ተማሪዎች የተሰጠው የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት መግለጫ

| ተ.ቁ | የፈተና መለያ ኮድ | የአራሚ ሀ ውጤት | የአራሚ ለ ውጤት | የአራሚ ሐ ውጤት | አማካይ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 01-ሀ | 18 | 14 | 24 | 18.66 |
| 2 | 02-ሀ | 56 | 60 | 79 | 65 |
| 3* | 03-ሀ | 69 | 70 | 73 | 70.66 |
| 4 | 04-ሀ | 44 | 50 | 40 | 44.66 |
| 5 | 05-ሀ | 35 | 40 | 33 | 36 |
| 6 | 06-ሀ | 19 | 16 | 11 | 15.33 |
| 7 | 07-ሀ | 36 | 47 | 41 | 41.33 |
| 8 | 08-ሀ | 45 | 51 | 40 | 45.33 |
| 9 | 09-ሀ | 11 | 8 | 15 | 11.33 |
| 10 | 10-ሀ | 65 | 52 | 54 | 57 |
| 11 | 11-ሀ | 20 | 24 | 16 | 20 |
| 12* | 12-ሀ | 57 | 64 | 63 | 61.33 |
| 13 | 13-ሀ | 60 | 50 | 55 | 55 |
| 14 | 14-ሀ | 45 | 62 | 58 | 55 |
| 15* | 15-ሀ | 35 | 45 | 43 | 41 |
| 16 | 16-ሀ | 22 | 08 | 15 | 15 |
| 17 | 17-ሀ | 42 | 38 | 43 | 41 |
| 18 | 18-ሀ | 21 | 05 | 11 | 12.33 |
| 19 | 19-ሀ | 24 | 15 | 18 | 19 |
| 20 | 20-ሀ | 38 | 40 | 47 | 41.66 |
| 21 | 21-ሀ | 45 | 61 | 52 | 52.66 |
| 22 | 22-ሀ | 27 | 41 | 30 | 32.66 |
| 23 | 23-ሀ | 45 | 40 | 48 | 44.33 |
| 24 | 24-ሀ | 29 | 28 | 31 | 29.33 |
| 25 | 25-ሀ | 20 | 23 | 22 | 21.66 |
| 26 | 26-ሀ | 24 | 18 | 17 | 19.66 |
| 27 | 27-ሀ | 29 | 25 | 29 | 27.66 |
| 28 | 28-ሀ | 30 | 24 | 24 | 26 |
| 29 | 29-ሀ | 60 | 50 | 56 | 55.33 |
| 30 | 30-ሀ | 29 | 19 | 27 | 25 |
| 31 | 31-ሀ | 26 | 17 | 24 | 22.33 |
| 32 | 32-ሀ | 40 | 44 | 45 | 43 |
| 33 | 33-ሀ | 32 | 26 | 30 | 29.33 |

## አባሪ አሥራ ሁለት

በሙከራ ቡድን ለተካተቱ የ10ኛ "ሀ" ክፍል ተማሪዎች የተሰጠው የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መግለጫ

| ተ.ቁ | የፈተና መለያ ኮድ | የአራሚ ሀ ውጤት | የአራሚ ለ ውጤት | የአራሚ ሐ ውጤት | አማካይ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 01-1 | 16 | 19 | 10 | 15 |
| 2 | 02-1 | 85 | 98 | 95 | 92.66 |
| 3* | 03-1 | 94 | 96 | 93 | 94.33 |
| 4 | 04-1 | 73 | 81 | 75 | 76.33 |
| 5 | 05-1 | 58 | 69 | 72 | 66.33 |
| 6 | 06-1 | 30 | 29 | 23 | 27.33 |
| 7 | 07-1 | 75 | 80 | 76 | 77 |
| 8 | 08-1 | 80 | 79 | 83 | 80.66 |
| 9 | 09-1 | 18 | 25 | 28 | 23.66 |
| 10 | 10-1 | 87 | 89 | 92 | 89.33 |
| 11 | 11-1 | 31 | 32 | 32 | 31.66 |
| 12* | 12-1 | 93 | 97 | 98 | 96 |
| 13 | 13-1 | 78 | 91 | 83 | 84 |
| 14 | 14-1 | 84 | 89 | 90 | 87.66 |
| 15* | 15-1 | 60 | 74 | 70 | 68 |
| 16 | 16-1 | 25 | 32 | 27 | 28 |
| 17 | 17-1 | 82 | 72 | 73 | 75.66 |
| 18 | 18-1 | 32 | 29 | 26 | 29 |
| 19 | 19-1 | 30 | 41 | 31 | 34 |
| 20 | 20-1 | 67 | 72 | 70 | 69.66 |
| 21 | 21-1 | 86 | 90 | 83 | 86.33 |
| 22 | 22-1 | 66 | 74 | 69 | 69.66 |
| 23 | 23-1 | 79 | 81 | 77 | 79 |
| 24 | 24-1 | 60 | 67 | 62 | 63 |
| 25 | 25-1 | 44 | 39 | 30 | 37.66 |
| 26 | 26-1 | 30 | 32 | 33 | 31.66 |
| 27 | 27-1 | 55 | 66 | 60 | 60.33 |
| 28 | 28-1 | 70 | 55 | 55 | 60 |
| 29 | 29-1 | 87 | 80 | 89 | 85.33 |
| 30 | 30-1 | 49 | 55 | 52 | 52 |
| 31 | 31-1 | 50 | 57 | 40 | 49 |
| 32 | 32-1 | 75 | 78 | 81 | 78 |
| 33 | 33-1 | 60 | 60 | 58 | 59.33 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 34 | 34-ሀ | 45 | 46 | 64 | 51.66 |
| 35 | 35-ሀ | 67 | 45 | 55 | 55.66 |
| 36* | 36-ሀ | 11 | 05 | 07 | 07.66 |
| 37* | 37-ሀ | 02 | 05 | 03 | 03.33 |
| 38 | 38-ሀ | 37 | 38 | 29 | 34.66 |
| 39 | 39-ሀ | 45 | 55 | 69 | 56.33 |
| 40 | 40-ሀ | 67 | 56 | 57 | 60 |
| 41 | 41-ሀ | 63 | 41 | 46 | 50 |
| 42* | 42-ሀ | 35 | 48 | 43 | 42 |
| 43 | 43-ሀ | 25 | 19 | 21 | 21.66 |
| 44 | 44-ሀ | 25 | 28 | 26 | 26.33 |
| 45 | 45-ሀ | 58 | 50 | 54 | 54 |
| 46 | 46-ሀ | 56 | 66 | 59 | 60.33 |
| 47 | 47-ሀ | 60 | 45 | 42 | 49 |
| 48 | 48-ሀ | 05 | 08 | 07 | 06.66 |
| 49 | 49-ሀ | 11 | 16 | 13 | 13.33 |
| 50 | 50-ሀ | 39 | 25 | 35 | 33 |
| 51 | 51-ሀ | 40 | 47 | 42 | 43 |
| 52 | 52-ሀ | 26 | 19 | 28 | 24.33 |
| አማካይ ውጤት | | 36.83 | 35.33 | 36.79 | 36.31 |

$\bar{X}$ =አማካይ ውጤት 36.31

$S^2$ =የአማካይ መደበኛ ልይይት 17.43

n=የናሙና አባላት ብዛት n-1= 51

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 34 | 34-1 | 80 | 84 | 83 | 82.33 |
| 35 | 35-1 | 90 | 80 | 91 | 87 |
| 36* | 36-1 | 22 | 25 | 21 | 22.66 |
| 37* | 37-1 | 09 | 12 | 11 | 10.66 |
| 38 | 38-1 | 67 | 65 | 64 | 65.33 |
| 39 | 39-1 | 87 | 89 | 92 | 89.33 |
| 40 | 40-1 | 88 | 89 | 93 | 90 |
| 41 | 41-1 | 80 | 82 | 81 | 81 |
| 42* | 42-1 | 60 | 74 | 62 | 65.33 |
| 43 | 43-1 | 39 | 48 | 45 | 44 |
| 44 | 44-1 | 65 | 60 | 53 | 59.33 |
| 45 | 45-1 | 95 | 95 | 92 | 94 |
| 46 | 46-1 | 90 | 89 | 92 | 90.33 |
| 47 | 47-1 | 78 | 85 | 80 | 81 |
| 48 | 48-1 | 13 | 17 | 06 | 12 |
| 49 | 49-1 | 08 | 10 | 12 | 10 |
| 50 | 50-1 | 68 | 70 | 64 | 67.33 |
| 51 | 51-1 | 67 | 75 | 78 | 73.33 |
| 52 | 52-1 | 43 | 50 | 49 | 47.66 |
| አማካይ ውጤት | | 60.73 | 63.97 | 61.63 | 62.11 |

$\bar{X}$ =አማካይ ውጤት 62.11

$S^2$ =የአማካይ መደበኛ ልይይት 25.70

n =የናሙና አባላት ብዛት n-1= 51

*ማሳሰቢያ፡-*

ከፍተኛ ውጤት ካስመዘገቡት 3* እና 12*፣ መካከለኛ ውጤት ካስመዘገቡት 15* እና 42*፣ ዝቅተኛ ውጤት ካስመዘገቡት ደግሞ 36* እና 37* ተራ ቁጥሮች በእጣ ተመርጠው ቅድመና ድህረ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ተማሪዎች ናቸው::

107

# አባሪ አሥራ ሦስት

በጥብቅ ቡድን ለተካተቱ የ10ኛ "E" ክፍል ተማሪዎች የተሰጠው የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት መግለጫ

| ተ.ቁ | የፈተና መለያ ኮድ | የአራሚ ሀ ውጤት | የአራሚ ለ ውጤት | የአራሚ ሐ ውጤት | አማካይ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 01-ለ | 54 | 64 | 55 | 57.66 |
| 2 | 02-ለ | 59 | 67 | 70 | 65.33 |
| 3 | 03-ለ | 19 | 14 | 20 | 17.66 |
| 4 | 04-ለ | 05 | 02 | 07 | 04.66 |
| 5 | 05-ለ | 35 | 46 | 38 | 39.66 |
| 6 | 06-ለ | 38 | 50 | 30 | 39.33 |
| 7 | 07-ለ | 22 | 26 | 25 | 24.33 |
| 8 | 08-ለ | 27 | 37 | 32 | 32 |
| 9 | 09-ለ | 10 | 06 | 10 | 08.66 |
| 10 | 10-ለ | 33 | 20 | 27 | 26.66 |
| 11 | 11-ለ | 22 | 23 | 25 | 23.33 |
| 12 | 12-ለ | 51 | 57 | 49 | 52.33 |
| 13 | 13-ለ | 60 | 56 | 55 | 57 |
| 14 | 14-ለ | 50 | 62 | 55 | 55.66 |
| 15 | 15-ለ | 24 | 26 | 20 | 23.33 |
| 16 | 16-ለ | 50 | 58 | 52 | 53.33 |
| 17 | 17-ለ | 25 | 20 | 25 | 23.33 |
| 18 | 18-ለ | 49 | 57 | 46 | 50.66 |
| 19 | 19-ለ | 39 | 30 | 34 | 34.33 |
| 20 | 20-ለ | 54 | 49 | 51 | 51.33 |
| 21 | 21-ለ | 22 | 13 | 11 | 15.33 |
| 22 | 22-ለ | 10 | 07 | 09 | 08.66 |
| 23 | 23-ለ | 50 | 58 | 54 | 54 |
| 24 | 24-ለ | 47 | 57 | 55 | 53 |
| 25 | 25-ለ | 53 | 55 | 49 | 52.33 |
| 26 | 26-ለ | 20 | 19 | 17 | 18.66 |
| 27 | 27-ለ | 18 | 26 | 19 | 21 |
| 28 | 28-ለ | 11 | 10 | 14 | 11.66 |
| 29 | 29-ለ | 05 | 04 | 10 | 06.33 |
| 30 | 30-ለ | 13 | 10 | 13 | 12 |
| 31 | 31-ለ | 24 | 16 | 20 | 20 |
| 32 | 32-ለ | 25 | 35 | 27 | 29 |
| 33 | 33-ለ | 66 | 76 | 81 | 74.33 |

# አባሪ አሥራ አራት

በጥብቅ ቡድን ለተካተቱ የ10ኛ "E" ክፍል ተማሪዎች የተሰጠው የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መግለጫ

| ተ.ቁ | የፈተና መለያ ኮድ | የአራሚ ሀ ውጤት | የአራሚ ለ ውጤት | የአራሚ ሐ ውጤት | አማካይ ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 01-2 | 63 | 63 | 76 | 67.33 |
| 2 | 02-2 | 73 | 80 | 76 | 76.33 |
| 3 | 03-2 | 15 | 21 | 14 | 16.66 |
| 4 | 04-2 | 10 | 16 | 03 | 09.66 |
| 5 | 05-2 | 40 | 46 | 45 | 43.66 |
| 6 | 06-2 | 41 | 44 | 52 | 45.66 |
| 7 | 07-2 | 20 | 25 | 29 | 24.66 |
| 8 | 08-2 | 37 | 40 | 40 | 39 |
| 9 | 09-2 | 11 | 15 | 09 | 11.66 |
| 10 | 10-2 | 25 | 35 | 20 | 26.66 |
| 11 | 11-2 | 17 | 25 | 14 | 18.66 |
| 12 | 12-2 | 55 | 64 | 51 | 56.66 |
| 13 | 13-2 | 50 | 47 | 57 | 51.33 |
| 14 | 14-2 | 47 | 54 | 53 | 51.33 |
| 15 | 15-2 | 12 | 21 | 17 | 16.66 |
| 16 | 16-2 | 54 | 60 | 51 | 55 |
| 17 | 17-2 | 18 | 30 | 14 | 20.66 |
| 18 | 18-2 | 40 | 47 | 41 | 42.66 |
| 19 | 19-2 | 31 | 40 | 38 | 36.33 |
| 20 | 20-2 | 45 | 42 | 49 | 45.33 |
| 21 | 21-2 | 08 | 16 | 14 | 12.66 |
| 22 | 22-2 | 02 | 04 | 01 | 02.33 |
| 23 | 23-2 | 55 | 47 | 49 | 50.33 |
| 24 | 24-2 | 40 | 45 | 44 | 43 |
| 25 | 25-2 | 43 | 50 | 49 | 47.33 |
| 26 | 26-2 | 21 | 27 | 16 | 21.33 |
| 27 | 27-2 | 23 | 27 | 17 | 22.33 |
| 28 | 28-2 | 19 | 11 | 14 | 14.66 |
| 29 | 29-2 | 09 | 07 | 03 | 06.33 |
| 30 | 30-2 | 10 | 21 | 12 | 14.33 |
| 31 | 31-2 | 17 | 27 | 17 | 20.33 |
| 32 | 32-2 | 25 | 32 | 27 | 28 |
| 33 | 33-2 | 56 | 68 | 81 | 71.66 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 34 | 34-ለ | 30 | 40 | 28 | 32.66 |
| 35 | 35-ለ | 45 | 67 | 60 | 57.33 |
| 36 | 36-ለ | 56 | 67 | 53 | 58.66 |
| 37 | 37-ለ | 56 | 49 | 52 | 52.33 |
| 38 | 38-ለ | 27 | 17 | 26 | 23.33 |
| 39 | 39-ለ | 28 | 24 | 26 | 26 |
| 40 | 40-ለ | 53 | 50 | 52 | 51.66 |
| 41 | 41-ለ | 62 | 44 | 48 | 51.33 |
| 42 | 42-ለ | 16 | 08 | 13 | 12.33 |
| 43 | 43-ለ | 60 | 66 | 58 | 61.33 |
| 44 | 44-ለ | 59 | 69 | 62 | 63.33 |
| 45 | 45-ለ | 29 | 33 | 29 | 30.33 |
| 46 | 46-ለ | 30 | 36 | 32 | 32.66 |
| 47 | 47-ለ | 29 | 39 | 29 | 32.33 |
| 48 | 48-ለ | 21 | 24 | 25 | 23.33 |
| 49 | 49-ለ | 60 | 71 | 61 | 64 |
| 50 | 50-ለ | 06 | 06 | 09 | 07 |
| 51 | 51-ለ | 12 | 03 | 06 | 07 |
| 52 | 52-ለ | 04 | 02 | 05 | 03.66 |
| አማካይ ውጤት | | 34.10 | 35.96 | 34.21 | 34.75 |

$\overline{X}$ = አማካይ ውጤት 34.75

$S^2$ = የአማካይ መደበኛ ልይይት 19.79

n = የናሙና አባላት ብዛት n -1= 51

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 34 | 34-2 | 28 | 17 | 22 | 22.33 |
| 35 | 35-2 | 58 | 67 | 65 | 63.33 |
| 36 | 36-2 | 60 | 65 | 66 | 63.66 |
| 37 | 37-2 | 40 | 48 | 46 | 44.66 |
| 38 | 38-2 | 20 | 25 | 24 | 23 |
| 39 | 39-2 | 28 | 34 | 19 | 27 |
| 40 | 40-2 | 43 | 43 | 56 | 47.33 |
| 41 | 41-2 | 61 | 52 | 50 | 54.33 |
| 42 | 42-2 | 17 | 21 | 16 | 18 |
| 43 | 43-2 | 60 | 66 | 70 | 65.33 |
| 44 | 44-2 | 62 | 74 | 71 | 69 |
| 45 | 45-2 | 38 | 45 | 37 | 40 |
| 46 | 46-2 | 34 | 39 | 26 | 33 |
| 47 | 47-2 | 30 | 33 | 29 | 30.66 |
| 48 | 48-2 | 34 | 27 | 27 | 29.33 |
| 49 | 49-2 | 67 | 70 | 77 | 71.33 |
| 50 | 50-2 | 09 | 13 | 07 | 09.66 |
| 51 | 51-2 | 50 | 50 | 60 | 53.33 |
| 52 | 52-2 | 10 | 09 | 07 | 08.66 |
| አማካይ ውጤት | | 34.44 | 38.35 | 35.92 | 36.23 |

$\overline{X}$ = አማካይ ውጤት 36.23

$S^2$ = የአማካይ መደበኛ ልይይት 20.11

n = የናሙና አባላት ብዛት n -1= 51

109

# አባሪ አሥራ አምስት

## ጥናቱን ለማካሄድ ከጥናቱ ተሳታፊዎች ጋር የፈቃደኝነት ስምምነት መፈራረሚያ ፎርም

የተማሪው ስም.................................... ፆታ ..... እድሜ ..... ክፍል .......

ጥናቱን የሚያካሂደው ሰው......................................................................

የጥናቱ ርዕስ፡- የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ለማረጋገጥ የተደረገ ሙካዊ ጥናት

የጥናቱ ተሳታፊዎች፡- የወረታ አጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት ማሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ "H" ክፍል ተማሪያች ናቸው።

ከሁሉ አስቀድሜ ከጥቅምት ወር 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ህዳር ወር 2003 ዓ.ም ድረስ በሚካሄደው በዚህ የሙከራ ጥናት ተሳታፊ ለመሆን ፈቃደኛ በመሆንዎ ምስጋናየን እያቀረብኩ፣ ይህ ፎርም የጥናቱን መሠረታዊ ዓላማዎች፣ እንደ ተሳታፊ የእርስዎን አስተዋጽኦና በሙከራው የጥናቱ ጊዜያት ሊከበርልዎ የሚገቡትን መብቶችዎን በዝርዝር የያዘ ነው።

እርስዎ በፈቃደኝነት ለመሳተፍ በወሰኑት ጥናት ላይ በሚሳተፉበት ወቅት የሚከተሉትን አስተዋጽኦዎች እንዲያከናውኑ ይጠበቃል።

1. በአጥኝው የሚቀርቡትን ቅድመና ድህረ ፈተናዎች በተፈቀደው ጊዜ ውስጥ ሰርተው በማስረከብ የመተባበር፣
2. በአጥኝው የሚቀርቡትን ቅድመና ድህረ ቃለ መጠይቅ ተገቢውን ምላሽ በመስጠት የመተባበር፣
3. ለአንድ ወር በሳምንት ሁለት ቀን የሚሰጠውን ትምህርት በሚገባና በንቃት የመከታተልና የሚሰጡትን ተግባራት በመስራት የመተባበር፣

የጥናቱ ዓላማዎች፡-

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን አዋህዶ በማስተማር ክሂሎቹን በማጎልበት ረገድ የሚኖረውን ሚና ለማረጋገጥ ታስቦ ለሚደረገው ሙከራዊ ጥናት መረጃ ማሰባሰብ ነው።

ጥናቱን በማከናወን ሂደት ከዚህ የሚከተሉትን ለማሟላት ዝግጁነቴን አረጋግጣለሁ።

1. ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብም ሆነ የጥናቱን ጽሑፍ በማዘጋጀት ሂደት ለእርስዎ ደህንነት ሲባል የእርስዎን ስምና ሌሎች መለያዎችን በመለያ ኮድ የምጠቀም መሆኑን፤
2. በቃለ መጠይቅና በምልከታ ወቅት ድምፅዎንና ምስልዎን ለመቀረጽ ፈቃደኛ በመሆንዎ ለዚህ ጥናት ጥቅም ብቻ ከማዋል በዘለለ ለማንም አሳልፌ የማላስተላልፍ ሲሆን፣ ሚስጥርዎን ሙሉ በሙሉ የምጠብቅ መሆኑን፤
3. በጥናቱ ወቅት እርስዎ የሰጡትን መረጃ ዋናው የጥናቱ ጽሑፍ ከመዘጋጀቱ በፊት የትርጉሙን ትክክለኛነትና እርስዎ የሰጧቸውን ምላሽና አስተያየቶች በትክክል መስፈራቸውንና መተርጎማቸውን አስተያየትዎን እንዲሰጡበት የማቀርብልዎ መሆኑን፤
4. በጥናትና ምርምር ሥነ ምግባር የተደነገጉትን ደንቦች ለማሟላት ዝግጁነቴን አረጋግጣለሁ።

የምሰጠው መረጃ በቪዲዮ ካሜራና በፎቶ ካሜራ እንዲቀረፅ፡

እፈቅዳለሁ ---------------------------- አልፈቅድም ---------------------------------

ከላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ፡

ተስማምቻለሁ ---------------------------- አልተስማማሁም ---------------------------------

የጥናቱ ተሳታፊ ስም------------------------------ ፊርማ ---------- ቀን -------------

ከላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ፡

ተስማምቻለሁ ---------------------------- አልተስማማሁም ---------------------------------

የአጥኚው ስም ---------------------------------- ፊርማ ---------- ቀን ---------------



የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በልምምድ ትምህርቱ ወቅት







የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የቅድመ ትምህርት ፈተናውን እየተፈተኑ





# ዲክላራስዮን

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የእኔ ሥራ መሆኑንና ለጥናቱ የተጠቀምኩባቸው ድርሳናት ዋቢነታቸው በትክክል የተጠቀሰ መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ።

ስም ________________

ፊርማ ________________

ቀን 22/07/2003